#DEFYHATENOW

የማህበራዊ ሚድያ የጥላቻ ንግግር ቅነሳ

ኢትዮጵያ

የመስክ መመሪያ

የበረራ እትም 2020 መመሪያ

https://defyhatenow.org
info@defyhatenow.org

© 2020 r0g_agency for open culture and critical transformation gGmbH Berlin

Field Guide Architect & Game Concept: Jodi Rose
Ethiopia Initiative Coordinator: Blen Gebrehiwot Desta
r0g_agency Project Manager: Stephen Kovats
Field Guide Editors: Jodi Rose, Blen Gebrehiwot Desta , Stephen Kovats, Kendi Gikunda
Ethiopia Field Guide Design: Cara Schwartz
Ethiopia Field Guide Amharic Version Design: Yemsrach Yetneberk
Ethiopia Field Guide Illustrations, A2 Posters & Game Design: Yemsrach Yetneberk
Trauma Healing Guide: Sharlotte Ainebyoona Kigezo
Article Authors, Trainers and Content Contributors: Adrian Shahbaz & Allie Funk (Freedom House), Dr. Adem K Abebe (LL.D), Blen Gebrehiwot Desta , Brett Solomon (Access Now), Fadia Elgharib, Hirut Dawit, Kim Otor, Lena Coco Kovats, Nelson Kwaje, Susan Benesch (Dangerous Speech Project), YaliChecks
Translations: Beruketaweet Fekadu and Astewai Amdeselassie

#defyhatenow Ethiopia Social Media Hate Speech Mitigation Field Guide is licensed under a Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International License.

Ethiopia edition 2020 of the #defyhatenow Social Media Hate Speech Mitigation Field Guide by r0g agency gGmbH is produced under commission by GIZ – Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit GmbH within the framework of the 'Cross-Border Collaboration Programme in Western Ethiopia and Eastern Sudan' with funding from the German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development and the European Union Trust Fund for Africa.

GIZ Partners: Gerhard Mai (Programme Manager) and Maike van Ueuem (Head of Component)

print ISBN: 9783981989557
ebook ISBN: 9783981989564

Ethiopia Pilot Edition December 2020

#defyhatenow
@defyhatenow
https://www.facebook.com/defyhatenow/
https://twitter.com/defyhatenow

የማህበራዊ ሚድያ የጥላቻ ንግግር ቅነሳ የመስክ መመሪያ ኢትዮጵያ

#ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ #HATEFREEETHIOPIA

ከ 2014 ጀምሮ #defyhatenow በደቡብ ሱዳን ማህበራዊ ሚዲያ ተኮር በሆነ መንገድ የጥላቻ ንግግርና አመፅ ማነሳሳትን ለመቀነስ የሚያግዙ ስልጠናዎችን በመስጠት ወጣት እና የሲቪል ማህበራት ቡድኖችን በሚዲያ አጠቃቀም ክህሎት እና በሰላም ግንባታ ላይ እንዲሳተፉ እያደረገ ይገኛል። #defyhatenow የዜግነት ጋዜጠኝነትን ፣ ማህበረሰባዊ ውይይትን እና ስብሰባዎችን ፣ ባህላዊና ጥበባዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም የፖሊሲ ስትራቴጂ እና በይነመረብ ላይ የሚደረጉ የሚዲያ ዘመቻዎችን ያጠቃልላል፡፡ ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች የተገኘው ውጤት በይፋ ከሚገኙ ጠቃሚ መሳሪያዎች፣ ሙያዊና የእውቀት ምንጮች ጋር በመሆን ሁሉን አቀፍ የሆነ የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር ቅነሳ የመስክ መመሪያ ተዘጋጅቶአል:: #defyhatenow ወደ አማርኛ ሲተረጎም #ጥላቻንአሁንይቃወሙ ማለት ነው።

#defyhatenow በእዚህ ሂደት ዉስጥ እና የመስክ መመሪያውን በበርካታ ሃገራት ላይ በማሳተም ሂደት ግጭቶችን ለመከላከል በሚዲያ የሚነሱ የጥላቻ ንግግሮች ግንዛቤን መፍጠር፣ ሚዲያ አጠቃቀም ክህሎትን መደገፍ፣ የስደት እና የመፈናቀል ጉዳዮችን በመንካት የተለያዩ ዘዴዎች በመከተል እንዲሁም ግልፅ ቴክኖሎጂን መሰረት ባደረገ መንገድ ወጣቶችን ፣ የማህበረሰብ መሪዎችን ፣ ጋዜጠኞችንና ሌሎች ተጽዕኖ ፈጣሪ የሰላም ግንባታ አብዢዎች እርምጃዎች መሰረት በመሆን ያገለግላል።

#defyhatenow የኢትዮጵያ የመስክ መመሪያ ጥቅል በኢትየጵያ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ የሰላም ግንባታ ጥረቶችን ለመዳሰስ እና ለመደገፍ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ እትሞች ተዘጋጅተዋል። የመስክ መመሪያው የታተመው r0g_Agency እና GIZ- Deutsche Gesellschaft für International Zusammenarbeit በመተባበር "የምእራብ ኢትዮጵያ-ደቡብ ሱዳን አገር አቋራጭ ትብብር" ፕሮጀክት መዋቅር ስር በመላው ኢትዮጵያ እንደግብአትነት እንዲያገለግል ታልሞ ነው። በደቡብ ሱዳን መሰረቱን ያደረገው DEFYHATENOW እና የአሶሳ ፖሊቴክኒክ የቴክኒክና ሞያ ኮሌጅ አጋርነት የተዘጋጀዉ ይህ የመስክ መመሪያ በሚዲያ አጠቃም ክህሎት ላይ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ያጠናክራል እንዲሁም የጥላቻ ንግግርና አመፅ ማነሳሳትን ለመከላከል ማህበራዊ ሚዲያን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ጠቃሚ መረጃዎችና ምሳሌዎችን ያቀርባል።

የማህበራዊ ሚድያ ስፍራዎችን ለግጭት መሳሪያ ለሆኑ ሰዎች ከመተው ይልቅ የአዎንታዊ ተፅእኖ ፈጣሪዎችን ተግባር በማጉላት እንዲሁም የሰላም ግንባታ ድምፆችን ለማስተጋባት ይህ የእርስዎ መስክ መመሪያ በበይነመረብ ላይ መተሳሰብና መቻቻል ላይ አብሮ ለመስራት የሚያግዙ መሳሪያዎች ስብስብ ነው።

#defyhatenow የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግርን ፣ የግጭት ዘይቤዎችን በበይነመረብ አመፅ ማነሳሳትን ለመከላከል የሚያስችል ግንዛቤ ለማስጨበጥና እውቀትን ለማጎልበት ያለመ ነው።

#defyhatenow የጎዳና ቲያትር ጁባ ደቡብ ሱዳን [በግራ የሚታየው ምስል]
#defyhatenow መስከ መመሪያ @Hagana በዓል [በቀኝ የሚታየው ምስል]

የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር መከላከያ የመስክ መመሪያ አጠቃቀም

#defyhatenow የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር ቅነሳ የመስክ መመሪያ በአለም ዙሪያ ለሰላም ግንባታ በማህበረሰብ ዉስጥ እና በበይነመረብ ዘመቻዎች ወቅት የሚዉሉ መሳሪያዎችን እና ስልቶችን ያቀርባል፡፡ የመስክ መመሪያዉ የኢትዮጵያን ሀገራዊ አዉድ የሚያሳዩ ፎቶዎችን፣ የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ ሁኔታ እና አሰራር ያቀርባል፡፡ የተዘጋጀዉም የመስክ መመሪያ ከከተማ ርቀዉ ሚገኙ ማህበረሰቦች ዉስጥ ፣ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ወይም ማሰልጠኛ ማዕከላት ዉስጥ ለመጠቀም ነዉ፡፡ የመስክ መመሪያዉ ግንዛቤ ለመጨመር ሌላ የመልስ ትርክት ለማዳበር እና የበይነመረብ ጥላቻ ንግግሮች ጋር የተያያዙ ጥቃቶችን ለመቀነስ መልመጃዎችን፣ ፖስተሮችን፣ካርዶችን፣ ዲጂታል መሳርያዎችን እና መጫዎቻዎችን ያካተቱ የስልጠና መሳርያዎች እና የወርክሾፕ ምንጮችን ያካተተ ነዉ፡፡

“ጥቃትን ማነሳሳት በጣም የተወሰነ ነዉ ስለዚህም ለማስወገድ ስትራቴጂክ የሆነ እርምጃ እና የማህበረሰብ መሪዎች እና የዜጎችን ቀጥተኛ እርምጃ ይጠይቃል፡፡ የጥላቻ ንግግር ለማነሳሳት መሰረት ሊሆን ቢችልም ተናጋሪዎች ጋር ለመሳተፍ፣ የአነጋገሩን ቃና ለማለስለስ፣ የአመለካከት ለውጥን ለማምጣት ግለሰብ የራሱን ስነ ዘዴ መጠቀም ይችላል፡፡ ለአደገኛ የበይነመረብ ንግግሮችን ምላሽ ለመስጠት እና ለበገሀዱ አለም ጥቃቶች አስተዋፆ ሚያደርጉን ለመቀነስ እንደ ማህበረሰብ ምላሽ ለመስጠት የቡድን ስትራቴጅዎች አስፈላጊ ናቸዉ፡፡” (Stephen Kovats, r0g_agency, Berlin).

በመስክ መመሪያ ውስጥ ያሉት መሳርያዎች የተዘጋጁት እና የተጠናከሩት በ#defyhatenow ተነሳሽነት እና ከ2015-2020 በአጋር ድርጅቶች እና ኔትወርኮች ከታተሙ መሳሪያዎች ከተወሰዱ ክፍሎች ነዉ፡፡

ይዘቶች

01 ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት 05

02 ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ 19

03 የማህበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ 31

04 የሲቪልማህበራት፡ የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ 41

05 ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ 53

06 ማንነት እና አውድ 59

07 ጥበብ ለሰላም፡ #አርትቪዝም #ARTIVISM 65

08 ከሰቀቀን መልሶ ማገገም(TRAUMA HEALING) 73

ከ 01-08 ላሉት ምዕራፎች ለሥልጠና ለማገዝ የተዘጋጀ

ለአመቻቾች ማስታወሻ 83

የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች 87-127

እዉቅና 128

1

ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት

01 ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት
ይዘቶች

የጥላቻ ንግግርን እንዴት መለየት ይቻላል ?

የጥላቻ ንግግር ህጎች፣ መመሪያዎች እና ትርጓሜዎች

የጥላቻ ንግግር እና ጥቃት በማህበራዊ ሚዲያ

የጥላቻ ንግግር መመሪያ

ኮሚኒቲ ስታንዳርድ (ማኅበረሰባዊ አግባብ) እና የጥላቻ ንግግር ፖሊሲ

የጥላቻ ንግግርን እንዴት ማመልከት ይቻላል

ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት በኢትዮጵያ

መልመጃ፣ ፍቺዎች እና ትርጉም

ሕግ እና ደንቦች ስለ ጥላቻ ንግግር በኢትዮጵያ

ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት እና የጥላቻ ንግግር ህጎች

ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና ጥላቻን ማነሳሳት ፡ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች (OHCHR) ራባት የተግባር መርሃግብር

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 1

ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት

የጥላቻ ንግግርን እንዴት መለየት ይቻላል ?

> “
> የጥላቻ ንግግር የቡድን አባልነትን መሠረት አድርጎ አንድ ሰዉን የሚያቃልል ወይም የሚያዋረድ ንግግር ነው፡፡ የጥላቻ ንግግር እንደ ምስሎች ፣ ተውኔቶች ፣ ዘፈኖች ፣ እንዲሁም ማንኛውንም ዓይነት የጥላቻ አገላለፅን ሊያካትት ይችላል፡፡ የጥላቻ ንግግር ትርጓሜዎች ፅንሰ-ሀሳብ የጭፍን ጥላቻን እና የአለመቻቻልን ሊያካትት ይችላል፡፡
> ”

ምንጭ፡ DW Hate Speech FAQ https://p.dw.com/p/1I9ku

የአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት ከአውሮፓ የሚኒስተሮች ኮሚቴ ምክር ቤት በወሰደው ትርጓሜ መሰረት 'የጥላቻ ንግግርን' እንደ ሁሉም ዓይነት አገላለፆች “የዘር ጥላቻ፣ ዘረኝነትን፣ ጸረ-አይሁድነትን ወይም ማንኛውም አይነት በአለመቻቻል ላይ የተመሰረተ ጥላቻ፣ በአለመቻቻል የሚገለጽ አደገኛ ብሔርተኝነት እና ብሄር ተኮርነት፣በቁጥር አናሳ የማህበረሰብ ክፍሎችን፣ ስደተኞችን፣ እንዲሁም በስደት የመጡ ሰዎችን ማግለል እንዲሁም ጠላትነት” የሚያሰራጩ፣ ሚቀሰቅሱ፣ ሚያራምዱ፣ ሚያፀድቁ አድርጎ ይቆጥራቸዋል፡፡

የጥላቻ ንግግር ህጎች፣ መመሪያዎች እና ትርጓሜዎች

የጥላቻ ንግግር ህጎች ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ የመጡ በአንጻሩ የቅርብ ጊዜ ክስተቶች ናቸው። ከነዚህ ህጎች በስተጀርባ ያለው አላማ ለእልቂቱ መነሻ የነበሩ የፀረ-አይሁድ እና የዘረኝነት ፕሮፓጋንዳዎችን ለመግታት ነበር። ጀርመን ፣ ፖላንድ ፣ ሀንጋሪና ኦስትሪያ የጥላቻ ንግግር ህጎችን ከአስርት አመታት በፊት አውጥተዋል። ሌሎች ብዙ ሀገራትም ይህንን ምሳሌ ተከትለዋል ። ለምሳሌ በኬኒያ ህግ አንድ ግለሰብ “የብሔር ጥላቻን” የሚቀሰቅስ ድርጊት ከፈጸመ እንደ እንደ ህገ ወጥ ይቆጠራል። የፈረንሳይ ህግ ገፋ አድርጎ ጎሳን፣ ዘርን፣ ብሔርን፣ ሃይማኖትን፣ ጾታን፣ ወሲባዊ ዝንባሌን ፣ አካል ጉዳትን አስመልክቶ አድሎን ፣ጥላቻን ወይም ጉዳትን የማናሳሳት ይዘት ያላቸው መልእክቶችን በህግ ይከለክላል።

የተ.መ.ድ ስምምነት የሆነዉ ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት መንግስታት የጥላች ንግግርን እንዲከላከሉ ጥሪ ያቀርባል። የዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 20(2) እንደሚገልፀዉ “ማንኛውም መድሎን፣ ጠላትነትን ወይም ጥቃትን ሚያነሳሳ የብሔርተኝነት ፣ የዘር፣ ወይም ሃይማኖት ጥላቻን ማበረታታት በህግ መከልከል ይኖርበታል”፡፡

የደቡብ አፍሪካ የማሰራጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚሽን ‘የጥላቻ ንግግርን’ ማንኛውም በዘር፣ብሔር ወይም ጎሳን፣ የቆዳን ቀለምን፣ ጾታዊ ዝንባሌን ፣ እድሜን፣ ጾታን፣ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳትን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የሚያበረታታ ወይም የሚያሞግስ” ወይም የጦርነት ፕሮፓጋንዳ ፣ አመጽ ማነሳሳት ወይም በዘር ፣ በጎሳ ፣ በጾታ ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ጥላቻ የሚፈጥር እና ጉዳት ለማድረስ ሚያነሳሳ ቅስቀሳ”፡፡

ምንጭ፡ DW Hate Speech explained https://p.dw.com/p/1I9ku

የጥላቻ ንግግር እና ጥቃት በማህበራዊ ሚዲያ

የበይነመረብ የጥላቻ ንግግር ምንድን ነው?

> “የጥላቻ ንግግር ብዙውን ጊዜ በበይነመረብ ላይ በተለይም በማህበራዊ ሚድያዎች ላይ ይታያል። እያንዳንዱ ማህበራዊ ሚድያዎች የየራሳቸዉ የሆነ የጥላቻ ንግግር ትርጉም አላቸዉ፡፡ ጥላቻ ንግግርን ለመቋቋም ሚጠቀምዋቸዉ መንገዶችም እየተሻሻሉ ነው፡፡”

የጥላቻ ንግግር መመሪያ

ፌስቡክ
https://www.facebook.com/communitystandards#hate-speech

“ፌስቡክ በዘር፣ በጎሳ፣ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሽታን መሰረት አድርጎ ሰዎችን የሚያጠቃ ይዘት ያለው የጥላቻ ንግግርን ያስወግዳል። በተጠቀሱት ርዕሶች ዙሪያ ቀልድ፣ ምፀት ወይም ማህበራዊ ትችትን ፌስቡክ ይፈቅዳል ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ወይም ሌሎችን ስለ ጥላቻ ንግግር ለማስተማር አስበው የሌሎችን የጥላቻ ንግግሮችን ለሌሎች ያጋራሉ። ለምን እንደዚህ ያለ ይዘት ያለውን ነገር እንዳጋሩ በበለጠ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዘን አላማቸውን በግልጽ እንዲጠቅሱ እንጠይቃለን። የሚያስፈራሩ ቋንቋ ሪፖርቶችን የህዝብና ግለሰብን ደህንነት እነዳይጎዱ ለመለይት በጥንቃቄ እንገመግማለን፡” በግለሰቦች ላይ አካላዊ ጉዳት ሚያደርሱ ተዓማኒነት ያላቸው ማስፈራሪያዎችን እናነሳለን”፡፡

ዩትዩብ
https://support.google.com/youtube/answer/2801939

በዩትዩብ ላይ የጥላቻ ንግግር አይፈቀድም። የመናገር ነፃነትን እንዲሁም ያልተለመዱ አይነት አመለካከቶችን በነፃነት የመግለፅ መብትን እናበረታታለን የጥላቻ ንግግርን ግን አንፈቅድም። የጥላቻ ንግግር ጥቃትን የሚያበረታታ ይዘት ያለዉ ወይም የቡድኖችን ወይም የግልሰቦችን ጾታ፣ ዘር፣ መደብ፣ ብሔር፣ የስደት ሁኔታ፣ ሀይማኖት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ጾታዊ ማንነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ የጦር ተመላሽነትን መሰረት ያደረገ ጥላቻ ጥላቻን ማነሳሳትን ተቀዳሚ አላማ ያደረገን ይዘት ያጠቃልላል፡፡

ዋትስአፕ
https://www.WhatsApp.com/legal?eea=0#terms-of-service

የዋትስአፕ የአገልግሎት አሰጣጥ ዉል ሀሰተኛ የሆኑ ህትመት እና ህገወጥ፣ ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ጥላቻ የተሞላበትና በዘር ወይም በጎሳ ስሜትን የሚጎዱ በሆኑ ባህርያት መሳተፍን ይከለክላል፡፡

አገልግሎቶቻችንን ለህጋዊ፣ ፈቃድና ተቀባይነት ላለው አላማ ብቻ የሚጠቀሙት መሆን ይኖርበታል።አገልግሎቶቻችንን በሚከተሉት መንገዶች መጠቀም (ወይም ሌሎችን እንዲጠቀሙ ማገዝ) አይቻልም (ሀ) ህገወጥ፣ ፀያፍ ፣ ስምን የሚያጎድፍ ፣ ማስፈራራት፣ ዛቻ ፣ ትንኮሳ ፣ ጥላቻ ፣ የአንድ ብሔርን ስሜት የሚጎዱ ወይም ህገወጥ የሆኑ አልያም አግባብነት የሌላቸዉ ተግባራትን እንዲፈፀሙ ማበረታታት (ለ) ሃሰተኛ መረጃዎን፣ አሳሳች መግለጫዎችን ማሳተም (ሐ) ሌላ ሰውን ማስመሰል ወይም መስሎ የመታየት ተግባራትን ማበረታታት፡፡

ትዊተር
https://support.twitter.com/articles/18311

“በጥላቻ የተሞሉ ድርጊቶች: በዘር፣በጎሳ፣በብሔር፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በጾታ፣ በጾታዊ ማንነት በሀይማኖት፣ በእድሜ፣ በጾታዊ ማንነት በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሽታን መሰረት በማድረግ ሰዎችን በቀጥታ ማስፈራራት ወይም ማጥቃት አልያም ጥቃትን ማበረታታትን አይችሉም ። የጥቃት ዛቻዎች (ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ): የጥቃት ዛቻዎችን ጥቃትን ማበረታታት ወይም መፈፀም እንዲሁም ሽብርን መፈጸም ወይም ሽብርተኝነትን ማበረታታት አይችሉም”፡፡

ኢሞ
https://imo.im/policies/community_guidelines.html

ኢሞ ደህንነት
ሽብርተኝነት / ፅንፈኝነት፡ እባኮትን የሽብርተኞች መሪዎች ፎቶግራፎች እና መግለጫዎች፣ ከፅንፈኞች እገታ ሚገናኙ የሚዲያ ይዘቶች፤ ደም መፋሰስ ይዘት ያላቸዉ ጥቃቶች እና የመሳሰሉትን አይነት ይዘት የሚያጠቃልሉ ሽብርተኝነትን ወይም ጽንፈኝነትን ሚያበረታቱ ይዘት ያላቸው ሚዲያዎች አያዘጋጁ አያሰራጩ፡፡ ከተገለጹት ጋር ግንኙነት ያለው ይዘት ይወገዳል እንዲሁም በማስረጃ ከተረጋገጠ የተገልጋዩ አካዉንት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሊታገድ ይችላል።

ወንጀልን ማዘጋጀት / ማስተዋወቅ፡ አገልግሎታችንን ጥቃትን፣ ስርቆትን፣ ማጭበርበርን ወዘተ የሚያጠቃልል ነገርግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደበ ማንኛውም የወንጀል ድርጊቶችን ለማበረታታትና ለመደገፍ መጠቀም የለቦትም። ከተገለጹት ጋር ግንኙነት ያለው ይዘት የሚወገድ ይሆናል እንዲሁም በማስረጃ ከተረጋገጠ የተገልጋዩ አካዉንት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሊታገድ ይችላል።

የጥላቻ ንግግር፡ ኢሞ ተጠቃሚዎቹ ከተለያየ የአለም ክፍሎች ከመምጣታቸው አንጻር ብዝሀነትን ያበረታታል።ሁሉም የማህበረሰብ አባል ከተለያየ አካባቢዎች ከመጡ ሰዎች ጋር እርስ በእርስ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያበረታታል። እባኮትን ማንም ላይ በዘር፣በጎሳ፣በብሔር፣ በጾታ፣ በጾታዊ ማንነት፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በሽታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይፈጽሙ። ከተገለጹት ጋር ግንኙነት ያለው ይዘት ይወገዳል እንዲሁም በማስረጃ ከተረጋገጠ የተገልጋዩ አካዉንት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሊታገድ ይችላል።

ኢሞ እውነተኛነት
ሌላ ሰውን ማስመሰል ወይም መስሎ መታየት፡ የኢሞ ተጠቃሚዎች ሰዎችን ለማታለል ወይም ለማጭበርበር አልመው ሌሎች ግለሰቦችን፣ የንግድ ምልክቶችን ወይም ድርጅቶችን ማስመሰል ወይም መስሎ መታየትን ይከለክላል። ሌሎች ተጠቃሚዎችን ታዋቂ ሰዎችን ወይም የኢሞ ሀላፊዎችን በማስመሰል ተጠቃሚዎች ገንዘብ እንዲያስተላልፉ ወይም ሌላ ተጠቃሚን ብድርን እንዲከፍሉ ማድረግ ወዘተን ያጠቃልላል ነገር ግን በነዚህ ብቻ አልተገደበም ። በማስረጃ ከተረጋገጠም የተገልጋይነ አካዉንት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሊታገድ ይችላሉ።

አብዛኛው ጎጂ ይዘትም በጋራ መመሪያ አማካይነት እና ማህበረሰብ አባላት መካከል ግንኙነት በመፍጠር ማስወገድ ይቻላል። ለምሳሌ ደምቦችን የሚጥስ ይዘት ያለው መልእክት በመወያያ ቡድኖች ላይ የሚልኩ ተጠቃሚዎች ካጋጠሞ ተጠቃሚው/ዋ መልክቱን መላክ እንዲያቆሙ ማሳመን ወይም የቡድኑን አስተዳዳሪ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ። የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈፀም እየተደራጁ መሆኑን ካሰቡ ተገቢ ማስረጃ ይዘው ባቅራቢያዎ ለሚገኝ የህግ አስከባሪ አካል በሰአቱ ያመልክቱ።

እባኮትን የሚተባበር በስምምነት የሚኖር እውነተኛ ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመገንባት ይተባበሩን።

ቴሌግራም
https://telegram.org/tos
ቴሌግራምን ሲቀላቀሉ የግላዊነት ፖሊሲን ተቀብለዋል የሚከተሉትን ላለማድረግ ተስማምተዋል

- አገልግሎቶቻችንን ተጠቅመው የማይፈለጉ መልእክቶችን ላለመላክ ወይም ተጠቃሚዎችን ላለማጭበርበር
- በግልጽ በሚታዩ የቴሊግራም ቻናሎች፣ቦቶች እና ወዘተ ላይ አመጽን ላለማበረታታት
- በግልጽ በሚታዩ የቴሊግራም ቻናሎች፣ቦቶች እና ወዘተ ላይ ህገወጥ የወሲባዊ ይዘት ያላቸዉን ላለመለጠፍ

የቴሌግራም ያለአግባብ አጠቃም ሪፖርት
https://telegram.org/privacy
በ abuse@telegram.org ወይም በ dmca@telegram.org ድረገጾች ላይ ለህዝብ ይፋ የሆኑ ይዘቶችን ህጋዊነትን በተመለከተ ቅሬታዎች በሚደርሱን ጊዜ አስፈላጊ ህጋዊ ማጣራቶች ከተካሄዱ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ከእይታ እንዲወርድ ሊደረግ ይችላል።

እባክዎትን ያስተውሉ ይህ በአንድ ሃገር ላይ ብቻ የተወሰኑ ሃሳብን የመግለጽ መብት ገደቦችን አይመለከትም። ለምሳሌ በአንዳንድ ሀገራት ላይ መንግስትን መተቸት ህገወጥ ቢሆን ቴሌግራም እንደዚህ ባሉ በፖለቲካዊ ምክንያትቶች የተነሳሱ ሳንሱሮች ላይ አይሳተፍም። ይህ የተመሰረተንበትን መርህ ይፃረራል። የአሸባሪዎችን (ምሳሌ፡ ከ ISIS ጋር የተገናኘ) ቦቶችና የማህበራዊ ሚድያ ገፆችን ብሎክ ምናደርግ ቢሆንም በሰላማዊ መንገድ አማራጭ አመለካከቶችን የሚገልፅን ማንኛውንም ሰው አንገድብም።

ኮሚኒቲ ስታንዳርድ (ማኅበረሰባዊ አግባብ) እና የጥላቻ ንግግር ፖሊሲ

https://defyhatenow.org/did-you-know-that-facebook-and-twitter-have-policies-against-hate-speech/

የጥላቻ ንግግርን እንዴት ማመልከት ይቻላል?

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ቅሬታዎችን ስለሚያስተናግዱበት መንገድ ሲተቹ ቆይተዋል። ተጠቃሚዎች ለሚያቀርቡአቸዉ ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ አይሰጡም። እንዲሁም የበይነመረብ ላይ ያለአግባብ አጠቃቀም ሪፖርቶችን ለማስተናገድ ይዘገያሉ። ሆኖም የጥላቻ ንግግርን ለመቆጣጠርና ለመከላከል አዳዲስ መንገዶችን በመገምገም ላይ ይገኛሉ። እያንዳንዱን የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ለአዳዲስ ሪፖርት መሳርያዎች እና መመርያዎች ይከታተሉ።



https://defyhatenow.org/how-to-report-hate-speech-2/

ጥላቻ ንግግርን እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የሚያሳይ ቪዲዮ በፒስ ቴክ ላብ (PeaceTech Lab) / **ፍላሽ** (USB Stick)**ላይም ይመልከቱ።**

የጥላቻ ንግግርን በፌስብክ ሪፖርት አድርጉ
https://youtu.be/_kRNx1WHAm0



የጥላቻ ንግግርን በዋትስአፕ ሪፖርት አድርጉ
https://youtu.be/1PlHuMl0ndQ

አንድን ሰው ዋትስአፕ ላይ እንዴት ማገድ ይቻላል
https://faq.WhatsApp.com/en/iphone/20950271/?category=5245250

የጥላቻ ንግግርን በትዊተር ላይ ሪፖርት አድርጉ
https://youtu.be/tLwgoTgbf8E

የጥላቻ ንግግርን በዩትዩብ ላይ ሪፖርት አድርጉ
https://support.google.com/youtube/answer/2802027

የጥላቻ ንግግር መስፈርትን የሚጥስ ይዘት ካገኙ እንዲመረመር ለዩትዩብ ሪፖርት ያድርጉ። የማህበረሰብ መመሪያችን ሲጣሱ እንዴት ሪፖርት እነደሚደረግ የሚገልፀውን መመሪያዎችን ከላይ በሚገኘው ማስፈንጠሪያ ማግኘት ይቻላል ወይም ቪዲዮውን ይመልከቱ።

https://youtu.be/45suVEYFCyc

ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት በኢትዮጵያ

ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት በኢትዮጵያ
https://www.peacetechlab.org/hate-speech

PeaceTech Lab ላብ የከፉ ግጭቶችን ለመቀነስ ቴክኖሎጂ፣ ሚዲያን እና ዳታን በመጠቀም ለሰላም ግንባታ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማፋጠን እንዲሁም ለማሳደግ ይሰራል። PeaceTech Lab ላብ የበይነመረብ የጥላቻ ንግግሮች እና በገሃዱ አለም ላይ ከሚከሰቱ አመፆች ጋር ያለውን ግንኙነት በበለጠ ለመረዳት ጥናት እያካሄደ ይገኛል። እ.ኤ.አ በ2021 የሚታተመው የኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግር መዝገበ ቃላት አመፅ አነሳሽ የሆኑ ቃላትን በመለየት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ባሻገር የጥላቻ ንግግር ለመከላከል ለሚታገሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ዋነኛ ግብአት በመሆን ለማገልገል ያልማል።

መልመጃ፡ ፍቺዎች እና ትርጉም

የቃላትን ፍቺና በትርጓሜያቸው ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት አስቡ።

"ቅር የተሰኘዉ ቡድን
አባል ብሆን ምን
ይሰማኛል?"

ራስዎን ይጠይቁ

በበይነመረብ ሆነ በገሃዱ አለም ላይ ከሰዎች ጋር በሚኖረን መስተጋብር የምንጠቀማቸው ቃላት በጥንቃቄ መምረጥ አስፈላጊ ነው። በበይነመረብ ላይ አስተያየቶችን ወይም ቀልዶችን ከመፃፎ ፣ ከመለጠፎ እንዲሁም መግለጫዎችን ከማጋራቶ በፊት የሰዎችን ስሜት ሊጎዳ ስለሚችል ስለተጠቀሙት ቃላት ማሰብ ይመከራል።

የሚጠቀሙት ቃላት የሚኖራቸውን ተፅእኖ ያመዛዝኑ። ጊዜ ወስደው ፅሁፎን፣ አባባሎን ያንብቡ። ካስፈለገ እረፍት ይውሰዱና ሲረጋጉ ይመለሱ።

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

- የጥላቻ ንግግር የሆኑ ቃላትን እና አላማዎቻቸዉን መረዳት።
- ምን ማለት እንደሆነ አንድ ሰው ባለማወቅ ሊያሰራጭ እንደሚችል።
- በበይነመረብ ሆነ በገሃዱ አለም ላይ ስለምንጠቀማቸውን ቃላት ማሰላሰል አስፈላጊነት።
- በበይነመረብ ሆነ በገሃዱ አለም ላይ ጥንቃቄ የማረግና በመቻቻልና ሌሎችን በመረዳት ላይ መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን ራስን የመጠየቅ አስፈላጊነት።

ሕግ እና ደንቦች ስለ ጥላቻ ንግግር በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያን የጥላቻ ንግግር ህግ መረዳት እና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን መጠበቅ
By Dr. Adem K Abebe (LL.D)

ከእንግሊዝኛ ፅሁፍ ወደ አማርኛ የተተረጎመ

መግብያ

እ.ኤ.አ መጋቢት 2020 የኢትዮጵያ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አነጋጋሪዉን የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1185/2020 አፀደቀ፡፡ አዋጁ የመጣዉ መንግስት በፍጥነት በማሰራጫ ጣቢያዎች፣ በማህበራዊ እና ህትመት ሚዲያ ከተሰራጩ ንግግሮች እና ሐሰተኛ መረጃዎች ጋር ያገናኛቸዉ ግድያዎችን ያስከተሉ ተከታታይ የሆኑ የብሔር ግጭቶች በኋላ ነዉ፡፡

አንዳንድ ግዜ ማህበራዊ አለመግባባትን ብሎም ጥቃትን የሚያስከትልን የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን መቆጣጠር አስፈላጊ እና ትክክል ነዉ፡፡ ወደ ወንጀል ህግ መሄዱ ህጉ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት በማቀዝቀዝ እና ህዝባዊ ዉይይቶችን በማፈን ተፅእኖ ይኖረዋል የሚል ስጋት ፈጥሯል፡፡ ይህ ፍርሀትም መንግስት የህግ ስርአትን አላግባብ መጠቀም፣ ፖሊስን እና አቃቤ ህግ ቢሮዎችን የፖለቲካ መጠቀምያ የማድረግ ታሪክን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በመነሳታቸዉ ያልተገቡ አይሆኑም፡፡

ይህ አጭር ማብራሪያ የኢትዮጵያን አዋጅ ትክክለኛነት ወይም ጥቅሙን እና ጉዳቱን ለመገምገም ያለመ አይደለም፡፡ ይልቁን ስለ አዋጁ ማህበረሰባዊ

ግንዛቤን በመፍጠር ግለሰቦች በነፃነት ሃሳባቸዉን የመግለፅ መብታቸዉን በነፃነት እንዲተገብሩ በአወጁ የተቀመጡ ክልከላዎችን እነዲረዱ አስተዋፆ ለማበርከት የፈለገ ነዉ፡፡ አንባቢያን በአዋጁ የአማርኛ እና እንግሊዘኛ ክፍል ላይ የተወሰነ ልዩነት እንዳለ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ይህ አጭር ማብራሪያም በአማርኛዉ አዋጅ ክፍል መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡

አዋጁን እወቁ

ስለአዋጁ ግልፅ የሆነ አረዳድ በህግ አስከባሪ አካላት ዳኞች እና ሰፊዉ ማህበረሰብ ዉስጥ መፍጠር ህጉን ለማፈን ሚዘረጋዉን መረብ እንዳይሰፋ ለማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህ አጭር ማብራሪያ ተራው ህዝብ ህጉን በተመለከተ ለማንቃት ብቻ ሳይሆን፡ ለህግ እስከባሪ አካላት፣ የሚዲያ እና የበይነመረብ መድረክ መሪዎችንም ጭምር ይረዳል፡፡

- የተከለከለዉ ምንድነዉ ቅጣቶቹስ፤
- የማስረጃ ሀላፊነት እና
- ተቀባይነት ያላቸዉ እና የሌላቸዉ መከላከያዎች።

የጥላቻ ንግግርን እና ሐሰተኛ መረጃ ከመተርጎማችን በፊት ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት መርህ መሆኑን ይህ መብት ሚገደብባቸዉ ደሞ ልዩ ሁኔታዎች መሆናቸዉን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት የጥላቻ ንግግሮች እና የሐሰተኛ መረጃ ወንጀሎችን በጥብቅ መረዳት ያስፈልጋል፤ ከምክንያተዊነት በላይ የማስረጃ ሀላፊነትም መንግስት ላይ ይወድቃል፡፡

በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የጥላቻ ንግግር ምንድነዉ?

በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች አብረዉ ሲሆኑ የጥላቻ ንግግር ይሆናሉ፡፡

1. **ሆን ብሎ ጥላቻን፣ መድልዎን ወይም ዓመፅን ማነሳሳት** (የእንግሊዘኛዉ ክፍል ማበረታታት ይላል ከሆን ብሎ ማነሳሳት አንፃር ያነሰ ክብደት አለዉ)።
2. አንድን ግለሰብ ወይም የሚታወቅ ቡድንን **በብሔር፣ ሀይማኖት፣ ዘር፣ ጾታ እና አካል ጉዳተኝነት** መሰረት በማድርግ ያነጣጠረ።

በዚህ መሰረትም የጥላቻ ንግግር ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር ነዉ፤ ዓመፅን ማስከተሉ እንደ መስፈርት አልተቀመጠም፡፡

- በአዋጁ መሰረት ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ሁኔታዎች ከተሟሉ የጥላቻ ንግግር ተፈፅሟል ማለት ነዉ፣ ንግግሩ ህዝባዊ አመፅን ወይም ጥቃት ዒላማ ያደረገዉ ቡድን ላይ ቢያስከትልም ባያስከትልም።

ማስታወሻ፥ የጥላቻ አገላለፆች ታርካዊ ግንኙነቶች ላይ ስለሚመሰረቱ በልምድ ጥቅም ላይ የሚዉሉ ክብርን ሚያጎድፉ ቃላቶች እና አገላለፆችን ማወቅ ህጉን በሚገባ ለመረዳት እና ለመተግበር ወሳኝነት አለዉ:: በዚህ ረገድ PeaceTech Lab (ፒስቴክ ላብ) የጥላቻ ንግግሮችን የያዘ መዝገበ ቃላት ለኢትዮጵያ እያዘጋጀ ነዉ::

ሐሰተኛ መረጃ ምንድነዉ?

ሐሰተኛ መረጃ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ይገናኛል፥

- ግለሰቡ **ሐሰት መሆኑን እያወቀ** ወይም በመሰረታዊ ማጣራት ሀሰት መሆኑ ሚታወቅ እና
- ህዝባዊ ረብሻ፣ አመፅ፣ ጥቃት ወይም ግጭት **የማስከተል ዕድሉ ከፍተኛ ሲሆን ነው።**

በዚህ መሰረት ከጥላቻ ንግግር በተለየ ሐሰተኛ መረጃ ረብሻ ወይም ጥቃትን የማስከተል እድሉ የሐሰተኛ መረጃ ወንጀል ትርጉሜ አካል ነዉ::

ማሳሰብያ፥ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ መንግስትን እና የመንግስት ሀላፊዎችን መተቸትን አይከለክልም::

የጥላቻ ንግግር ወይም ሐሰተኛ መረጃ ወንጀል ሚሆነዉ መቼ ነዉ?

አዋጁ የጥላቻ ንግግርን ወይም ሐሰተኛ መረጃን ዝም ብሎ አይቀጣም፥

- የጥላቻ ንግግሮችን ወይም ሀሰተኛ መረጃዎችን **ለብዙዎች ማሰራጨት** ቅጣት ያስከትላል::
- መልዕክቱ ለምን ያህል ሰዎች መሰራጨት እነዳለበት ህጉ ግልፅ አይደለም ነገር ግን ከቅርብ ጓደኞች እና ቤተሰቦች ዉጪ መጋራት ሊያስፈልግ ይችላል::
- እንደ ጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ የተቀጠሩ ይዘቶችን **ላይክ ማድረግ** (Liking) ወይም **ታግ ማድረግ** (tagging) እንደ ማሰራጨት ስለማይቆጠር ሚያስቀጣ አይደለም::

የጥላቻ ንግግሮች እና ሐሰተኛ መረጃዎች እንዴት ይሰራጫሉ?

ቁም ነገሩ የጥላቻ ንግግር ወይም ሐሰተኛ መረጃ የተሰራጨበት መንገድ አይደለም፡ የሚከተሉትንም ሊያካትት ይችላል፥

- በአካል፤ ምሳሌ ትልቅ ስብሰባ ዉስጥ፣
- በቴሌቭዝን ወይም በሬድዮ፣
- እንደ ፌስቡክ ባሉ ማህበራዊ ሚዲያዎች፣
- እንደ ቴሌግራም ባሉ የመልዕክት መፃፍያ ወይም መደወያ መተግበርያዎች፣
- እንዲሁም ማንኛውም አይነት የበይነመረብ መድረኮች እንደ በይነመረብ ህትመቶች እና የግል ድረገፆች::

ማሳሰብያ፥ አዋጁ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ ይዘት ያላቸዉን መረጃዎችን ወይም ንግግሮችን ዝግጅትን ሳይሆን ለብዙዎች ማሰራጨትን ነዉ ሚከለክለዉ:: ስለዚህ መረጃዉን ያሰራጨዉ ሲቀጣ ያዘጋጀዉ ላይቀጣ ይችላል ማለት ነዉ::

ቅጣቶቹ ምንድን ናቸዉ?

በፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ ሰዉ ከፍተኛ ቅጣት ይጠብቀዋል::
የጥላቻ ንግግር ቅጣት እስከ ሁለት ኣመት እስራት ወይም 100,000 ብር የገንዘብ ቅጣት ሊደርስ ይችላል::
ሐሰተኛ መረጃ ቅጣት እስከ አንድ አመት እስራት ወይም 50,000 ብር የገንዘብ ቅጣት ሊደርስ ይችላል::

የማህበራዊ አዉድ አስፈላጊነት

የጥላቻ ንግግር እና ሀሰተኛ መረጃ ክልከላዎች የማህበራዊ እንድነትን እና መረጋጋትን መረበሽን ለመካላከል ያለሙ ናቸዉ:: የጥላቻ ንግግር ወይም ሐሰተኛ መረጃ ምንድን ናቸዉ ሚለዉ በቡድኖች መካከል ያለ ታሪካዊ ግንኙነት እና ትርክት ላይ ይመሰረታል::

- በመርህ ደርጃ ሐሰተኛ መረጃን የመረጃዉን ማጣቀሻ ትክክለኛነት በመፈተሽ ማረጋገጥ ቢቻልም ታሪካዊ ሁነቶች አከራካሪ በሆኑበት አዉድ ዉስጥ ሐሰተኛ መረጃን መተርጎም አወዛጋቢ ይሆናል::
- የጥላቻ ንግግር ላይ ኢላማ የተደረገዉ ቡድን መልዕክቱን እንደ አድሎአዊ ወይም የጥላቻ አድርጎ መረዳት ላይ ስለሚመሰረት ማረጋገጥ ከባድ ነዉ::

ህግ አስከባሪ ተቋማት ዉስጥ ያሉ ሰራተኞች ፖሊሶች፣ አቃቤ ህጎች እና ዳኞች የህብረተሰቡ አካል ናቸዉ እና ለቡድን ትርክቶች ተጋላጭ ናቸዉ:: ይህም ለህጎች ወጥነት የጎደለዉ አተገባበር ከፍተኛ አድል ይፈጥራል:: ወጥነት የጎደለዉ እና መራጭ የሆነ የህግ አተገባበር አዋጁ ሊያጠነክረዉ የሚፈልገዉን ማህበራዊ አንድነት እና መረጋጋትን መልሶ አደጋ ላይ ይጥላል::

የጥላቻ ንግግርን እና ሐሰተኛ መረጃን ወንጀል ከማረግ ባሻገር

ግለሰቦች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብታቸዉን በሀላፊነት እና በጥንቃቄ መተግበር ቢኖርባቸዉም የጥላቻ ንግግርን እና ሐሰተኛ መረጃን ለመከላከል የረዥም ግዜ ስኬት ከወንጀል ህግ ዉጪ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ረገድ ብዙ ግብዓቶች መዋል ያለባቸዉ የዲጂታል ክሕሎት ግንባታ ላይ እና የቡድኖች እርስ በእርስ ትዉዉቅ እና ተግባቦት ላይ ነዉ:: የመጨረሻ ግቡም የጥላቻ ንግግርን እና ሐሰተኛ መረጃን ወንጀል ማረግን አላስፈላጊ ማድረግ ነዉ::

በእርግጥ አዋጁ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ላይ የህዝብ ግንዛቤን የማሳደግ እና ሐሰተኛ መረጃን ለመዋጋት የሚድያ ክህሎት ዘመቻዎችን የማዘጋጀት እና ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የጥላቻ ንግግሮችን ለመዋጋት የህዝብ ግንዛቤን ሚያሳድጉ ዘመቻዎችን የማዘጋጀት ሀላፊነት ሰጥቶአል:: ይህ የተሟላ የሚሆነዉ የማህበራዊ ሚድያ አገልግሎት ሰጪዎች የሐሰተኛ መረጃዎችን እና የጥላቻ ንግግሮችን ለመግታት እና ለመከላከል በ 24 ሰዓታት ውስጥ ማሳወቂያዎች በደረሱ ጊዜ ሐሰተኛ መረጃን ወይም የጥላቻ ንግግሮችን ለማስወገድ ሀላፊነት ሲወስዱ ነዉ:: :

ከእኛ ጋር ይወያዩ

- ስለ ጥላቻ ንግግሮች እና ሐሰተኛ መረጃዎች አዋጅ ሰምተዉ ወይም አንብበዉ ያዉቃሉ?
- የአዋጁን ይዘት እንዴት ይረዱታል?
- ከአዋጁ ጋር ያሎት ልምድ ምንድነዉ? አንተ/ቺ ወይም የምታዉቃቸዉ ሰዎች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነታቸዉን በአዋጁ ምክንያት ገድበዋል?
- አዋጁ መሻሻል ወይም መቀየር አለበት ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?

ምንጭ: https://defyhatenow.org/understanding-ethiopias-hate-speech-law-protecting-freedom-of-expression/

ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት እና የጥላቻ ንግግር ህጎች

> "የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድኖች የጥላቻ ንግግር ህጎች አፈፃፀም የሚያሳስብበት ምክንያት እንዳለ ይገልፃሉ ፣ በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ላይ በዜጎች የሚሰነዘሩ ትችቶችን ለማፈን እና የጋዜጠኞችን እና የማህበረሰብ አንቂዎችን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነትን ለማገድ ሊያገለግል ይችላል::"

ነፃነት በድረገፅ ላይ 2019 : የማህበራዊ ሚድያ ቀዉስ
https://freedomhouse.org/report-types/freedom-net
Adrian Shahbaz & Allie Funk, Freedom House

በመላው አለም ላይ በፍጥነት የተስፋፋው የዲጂታል መሳሪያዎች እና ስልቶች አምባገነናዊ ገዥነት የበይነመረብ ነጻነት ላይ ከፍተኛ አደጋ እየጣለ ይገኛል። ጨቋኝ አገዛዞች፣ አምባገነናዊ ምኞቶች ያላቸው ተመራጮች እና ጨካኝ ደጋፊዎች ቁጥጥር ያልተደረገለትን የማህበረሰብ ሚዲያ መድረኮች በመበዝበዝ ለፖለቲካ መዛባት እና ማህበረሰብን መቆጣጠሪያ መሳሪያነት ቀይረዋቸዋል።

“የማህበራዊ ሚዲያዎች ለህዝባዊ ውይይቶች እንደ መድረክ እያገለገሉ ቢሆንም ዜጎችን በመሰረታዊ ነፃነቶቻቸው ላይ ከዚህ በፊት ታይቶ ለማይታወቅ አፈና እንዲጋለጡ አድርጓል።”

ማህበራዊ ሚዲያ ማንኛውም ሰዎችን፣ ህዝባዊ ቡድኖች እና ጋዜጠኞችን በትንሽ ወይም ያለምንም ወጪ ሰፊ የሆነ ታዳሚ ለመድረስ ያስችላቸዋል።በተመሳሳይ እጅግ ጠቃሚ እና ርካሽ መድረክን ለውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ ላሉ ሀይሎች በተመሳሳይ ለመጥፎ ተጽዕኖ ሥራዎች ለመጠቀም እድል ይከፍታል ፡፡ በብዙ ሀገሮች የሕዝባዊነት እና የቀኝ አክራሪነት መጨመር የበይነመረብ የወንጀል ቡድኖች እድገት ትክክለኛ ተጠቃሚዎች እና አጭበርባሪ መለያዎችን ይጨምራል። እነዚህም የወንጀል ቡድኖች በተመሳሳይ ፍላጎቶች ዙሪያ ተከታዮችን ይገነባሉ፣ የፖለቲካ መልእክቶቻቸውን በሃሰተኛ ወይም በሚያስቆጡ ይዘቶች ይሰራሉ፣ በመከተልም በብዙ መድረኮች ስርጭቱን ያስተባብራሉ።

ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እና ጥላቻን ማነሳሳት ፡ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች (OHCHR) ራባት የተግባር መርሃግብር

https://player.vimeo.com/video/458350308

የራባት የተግባር መርሃግብር አድሎን ለመቀሰቅስ ፣ ለጠላትነት ወይም ለአመፅ መሰረት የሚሆኑ የብሄር፣ የዘር ወይም ሃይማኖት ጥላቻ መደገፍን ክልከላዎች ከተለያዩ OHCHR ሙያዊ ወርክሾፕዎች ድምዳሜዎችን እና አስተያየቶችን ተሰባስበዋል።

ሃሳብን በነጻነት የመግልጽ ላይ የሚደረጉ ክልከላዎች ከፍተኛ መስፈርት መሟላት

በአለም ዙሪያ ሁለት ፅንፎች ይገኛሉ፡በአንድ በኩል ‘እውነተኛ’ የቅስቀሳ ጉዳዮች ለፍርድ አይቀርቡም ሆኖም በሌላ በኩል ሰላማዊ ትችት የሚያቀርቡ ‘ጥላቻ ሰባኪዎች’ ተብለው ይከሰሳሉ። የራባት የድርጊት መርሃግብር ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ እና የጥላቻ ቅስቀሳ አተረጎጎም ላይ ከፍተኛ መስፈርት የማድረግ ሃሳብን ያቀርባል።

የራባት የተግባር መርሃግብር መስፈርት ስድስት ክፍሎች ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፥

አውድ፡ የአገላለፁ አዉድ

ተናጋሪ፡ ተናጋሪው በህበረተሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ ወይም ደረጃ

ዓላማ፡ አድማጮችን ዒላማ የተደረገዉ ቡድን ላይ ማነሳሳት

ይዘት እና ቅርጽ፡ የአገላለፁ ይዘት እና ቅርጽ

የንግግር ተግባር መጠን፡ የስርጭቱ መጠን

የመሆን ዕድል፡ አይቀሬነትን ጨምሮ

'ጥላቻ' እና 'ጠላትነት' ማለት አንድ ዒላማ በተደረገ ቡድን ላይ ሃይለኛና ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የሚገለፅ አሳፋሪ፣ ውርደትና ጠላትነት የተሞላ ስሜት ማለት ነው።

'ቅስቀሳ' የሚለው ቃል ሆን ተብሎ በይፋ የሚደረግ አንድን ቡድን ዒላማ ያደረገ ጥላቻን የማበረታታት ዓላማ ያለው ተግባር በሚል ልንረዳው እንችላለን፤ እና

'ማነሳሳት' ማለት በብሔር፣ በዘር ወይም በሃይማኖታዊ ቡድኖች ላይ ያነጣጠሩና የአድልዎ፣ የጠላትነት ወይም ለጥቃትና ለአመፅ የቀረበ ስጋትን የሚፈጥሩ መልእክቶች ናቸው።

https://www.ohchr.org/EN/Issues/FreedomOpinion/Articles19-20/Pages/Index.aspx

2

ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ



02 ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ

ይዘቶች

ሰላም በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን

ሰላም ለሁሉም፣ የታክሲ ሹፌሩ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ሰላምን እየሰበከ

ዲጂታል መብቶች የሰብአዊ መብቶች ናቸው

ዲጂታል መብት ምን ማለት ነው?

የጥላቻ ንግግርን በኢትዮጵያ መቃወም

መልመጃ፣ በበይነመረብ እና በማህበረሰባችሁ ውስጥ ስላለ የጥላቻ ንግግር ተወያዩ

ተግባር ተኮር ጥናት፣ አበባ ንግግር ዘመቻ (FLOWER SPEECH CAMPAIGN)

#ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ የሰላም አምባሳደሮች (#HATEFREEETHIOPIA)

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 2

ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ

?

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

ማህበራዊ ሚድያ ለሰላም ግንባታ እንዴት ጥቅም ላይ ሊዉል ይችላል?

ዲጂታል እና ሰብአዊ መብቶች ምንድናቸው?

በበይነመረብ ላይ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት ለምን አስፈለገ?

ሰላም በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን

By Fadia Elgharib

በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን ስለ ሰላም ስናስብ የግጭቶችን አቅጣጫ ለመቀየር ማንኛውም ዜጋ ምን ያህል ማድረግ እንደሚችል/እንደምትችል እንዲሁም ያለውን/ያላትን አቅም መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

በቀላሉ ስልኮትን ብቻ በመጠቀም ጭቆናን መቃወም ፣ በችግር ወቅት የበጎ አድራጎት የነፍስ ማዳን ተልእኮዎችን እንዲሁም ለውጥን መርዳት ይችላሉ(i.e Arab Spring)። ይሄንን ሁሉ ራሶን ችለው ወይም በትንሽ ድጋፍ ማድረግ የሚችሉት ነው።. በዚህ ረገድ ሰላም የመንግስት ባለስልጣናት በፓርላማ ውስጥ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጠረጴዛ ዙሪያ የሚወያዩበት ርዕስ ብቻ አይደለም።

እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ አንድ የማህበረሰብ ክፍል በአቅማችን ሰላም የእያንዳንዳችን ሀላፊነት ነው። ይሄንን ስንገነዘብ በዚህ ይበልጡን እየተወሳሰበ ባለው አለም ውስጥ እንደ ጦማሪያን ፣ አስተማሪዎች ወይም ዜጎች ሰላምን ለመፍጠርና ለማስከበር ያለንን ሚና እንድንቃኝ ያስገድደናል። ሰላምን ለመፍጠርም ሆነ ለማፋለስ ማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ መፍጠር እንደሚችል የተረጋገጠ መሳሪያ ነው። ስለዚህ በብልሀት መጠቀም የኛ ሃላፊነት ነው።

ሰላም ግንባታ የሚለው ስያሜ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብንጠቀመውም “ሰላም” የሚለው ቃል ትርጉም እና ከ#defyhatenow አውድ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ጊዜ ወስደን መፈተሽ ይኖርብናል።

ሰላም ፈጣሪነት በበይነመረብ እና በገሀዱ አለም

በበይነመረብ ላይ የሚጻፉ መልእክቶችና ታሪኮች በገሃዱ አለም ላይ ያላቸውን ትክክኛ ተፅእኖ ማወቅ ከባድ ቢሆንም በመስክ መመሪያው ላይ የተነሱት ምሳሌዎች ዲጂታል እና ዲጂታል ያልሆኑ መገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ያለማችን ክፍሎች ላይ ግጭትና ሁከትን ለመቀስቀስ የተጫወቱትን

ሚና ያሳያል። የበይነመረቡ አለም በገሃዱ አለም ላይ ያሉ ነባራዊ ውጥረቶች ያላቸውን ተደራሽነት ለመጨመርና እና ለማስፋፋትም እንደሚያገለግል ያስተውሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበራዊ ሚዲያ ፣ ብሎግም ሆነ ሌላ የሚድያ ዘርፍ ማህበራዊ ለውጥን በተቃራኒ አቅጣጫ ሰላምን ለመፍጠር ተጽእኖ የማድረግ አቅም አለው። ዲጂታል መሳሪያዎች ከአለም ማህበረሰብ ጋር በቀላሉ ለመገናኘት ስለሚያግዙን ይህንን በባህላዊ ክንውኖች ፣ ታሪኮችን በማካፈል እና በሰላም መልእክቶች በመሙላት ማህበራዊ ለውጥን ለማምጣት ጉልበት እና እንቅስቃሴን ሊያስተሳስር ይችላል።

የበይነመረብ እንቅስቃሴ በገሃዱ አለም የሚደረጉ ድጋፎችን/ግንዛቤ መፍጠሪያዎችን ኩነቶችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎን ያጠናክራል።

ሰላም ማስከበር እና ሰላም ግንባታ

ሰላም የሚለው ቃል ከጦርነት አውድ ጋር ይስተሳሰራል እንዲሁም በዋናነት የጦርነት አለመኖር ወይም የግጭት አለመኖር ሁኔታን ማስጠበቅ ማለት እንደሆነ አድርገን እንረዳዋለን። ይህ የሰላም እይታ ለሰላም ግንባታ በጣም ወሳኝ የሆኑ የማህበራዊ ህብረት አካሎችን ማካተት ይቀረዋል።

የሰላም ግንባታ እና የሰላም ማስከበር ከሰላም ጋር በተያያዘ የሚነሱ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው። የሰላም ማስከበር ሰላምን ማስጠበቅ በተለይም በአንድ አካባቢ ላይ "ያሉ ታጣቂ ሀይሎች መካከል ያለ ግጭትን መከላከል ማለት ነው። (Collins, 2003)

በሌላ በኩል ሰላም ግንባታ ግጭቶችን ወደ ዘላቂ እና ሰላማዊ ግንኙነቶች ለመቀየር የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ሂደቶች ፣ ስነ ዘዴ ዎች እና ደረጃዎች የሚያመነጭ ፣ የሚደግፍ እና የሚያካትት ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ ነው። (Lederach, 1997).

ቃሉ መደበኛ የሰላም ስምምነቶችን የሚቀድሙና የሚከተሉ ሰፋፊ ተግባራትን ያካትታል፡፡Galtung (1998) የሰላም ግንባታን የሚያብራራው ጦርነቶችን ሚያስከትሉ ምክንያቶችን የሚያስወግዱ እና በጦርነት መሰል ሁኔታዎች ውስጥ አማራጮችን የሚያቀርቡ ራስን የሚደግፉ መዋቅሮችን የመፍጠር ሂደት ብሎ ነው፡፡

ልክ ጤናማ አካል የራሱ ፀረ እንግዳ አካላት የመፍጠር ችሎታ እንዳለው እና ጊዜያዊ የመድኃኒት አስተዳደር እንደማያስፈልገው እንደነዚህ ያሉ አሠራሮች በኅብረተሰቡ መዋቅሮች ውስጥ ተገንብተው ሥርዓቱ ራሱ የሚጠቀምበት ሆነዉ መገኘት አለባቸው፡፡ (Galtung, 1998; Lynch & Galtung, 2010 p6.)

"ሰላምን መቅረብ ወይም መጠበቅ እንጂ በፍፁምነት ማግኘት አይቻልም" ተብሎ ይታሰባል፡፡

ሰላምን መከታተል ተገቢ ነው፡፡ምክንያቱም "ሰላም ሰዎች ከግጭት ጋር አብረው እንዲኖሩ እና ለግጭቶች ሁከተኛ ያልሆነ ወይም አመፅ የሌለበት ምላሽ ነዉ፡፡ ሰላም "ለደም አፋሳሽ" መንገዶች አማራጮችን ያገኛል፡፡"

እነዚህ አማራጭ መንገዶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ የማህበረሰብ ሁከት የሌለበት ምላሽ በተለይም በሽምግልና እና በውይይት፣ በህብረተሰብ ውስጥ ለተለያዩ ቡድኖች ርህራሄ እና መቻቻል መገንባት፣ በመላ ህብረተሰብ ውስጥ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የግንኙነት መረቦችን ለመገንባት እና ለማቆየት በህብረተሰብ መካከል የመተማመን እና የመግባባት ትስስርን ማጠናከር፡፡

ሰላም ለሁሉም፡ የታክሲ ሹፌሩ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ሰላምን እየሰበከ

"የታክሲ ሹፌሩ ሰይፉ አማኑኤል - በተጨናነቁ የአዲስ አበባ መንገዶች መካከል ላይ በመቆም የሚያስተላልፋቸው መልእክቶች ።"

"ምንም እንኳን ሁሉም ነገር ቢኖርህም ሰላም ከሌለ ዋጋ የለውም። በየቀኑ ቢያንስ ለሶስት ሰዎች ስለ ሰላም ግንዛቤ ብሰጥ ደስተኛ ነኝ። እዚህ ስቆም አንዳንድ ሰዎች ይቀልዳሉ አንዳንዶች ደግሞ ይሳደባሉ። በቀን ከ30-40 ደቂቃ በማጥፋቴ እንዳባከንኩ አልቆጥርም። በቀን ከማሳልፈው ተግባራት ይልቅ እነዚህ 40 ደቂቃዎች ለእኔ እጅግ የበለጠ ደስታን ይሰጡኛል።"

https://www.facebook.com/watch/?v=281645119469519

ምንጭ፡ BBC Africa, The taxi driver preaching peace on the streets of Addis Ababa

ዲጂታል መብቶች የሰብአዊ መብቶች ናቸው

መረጃ ማግኘት

ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት

የግላዊነት መብት

የዲጂታል መብት ተግሮቶች

- የዲጂታል የበላይ ገዢነት - ክትትል/ስለላ፣ የበይነመረብ መዘጋት፣ ሳንሱር፣
- ባለቤትነታቸው የግል ኮርፖሬሽን የሆኑ የማህበራዊ ትስስሮች በነፃ የበይነመረብ አገልግሎት ማቅረብ፣
- የፕሬስ ነጻነት ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶች፣ በጋዜጠኞች እና በዜጎች ላይ የሚደርስ ትንኮሳ፣
- ደህንነት ለሴቶች እና ለሴት ልጆች በበይነመረብ ላይ፣ የሳይበር-ጥቃት እና ጾታዊ ትንኮሳ፣
- መረጃዎቻችንን ግላዊ ሚስጥሮችን በንግድ ድርጅቶች እና በመንግስት አላግባብ ጥቅም ላይ መዋል።

ሰብአዊ መብቶች በዲጂታል አለም

የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ ለሰብአዊ መብት እንቅስቃሴዎች የማእዘን ድንጋይ በመሆን ወደ አለም አቀፍዊ እኩልነት፣ ፍትህ እና የሰው ልጅ ክብር ግንዛቤ ይመራናል። ነገር ግን ለብዙዎቻችን ይህ ተስፋ እውን አልሆነም።

የጋራ የሰብአዊ መብት መዋቅራችን እየተቀየረ ከሚገኘው ማህበረሰባችን ጋር ያለማቋረጥ እየተለወጠ ይገኛል። መብቶቻችን በዲጂታል አለም ውስጥ መጠበቅ እንዳለባቸውና በነጻነት ሃሳብን ከመግለፅ እስከ የመማርና የመስራት መብቶች እንዲሁም በጠቅላላ ሌሎች መብቶቻችንን እንድንጠቀም ለማስቻል የመረጃ መረብ ተደራሽነት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል።

ይህ መዋቅር በዋናነት ከአዋጁ ጋር ብዙ ስኬቶች ቢኖሩትም አሁን ላለንበት የዲጂታል ዘመን የገሃዱ አለም ተግዳሮቶች ምላሽ ለመስጠት እየታገለ ይገኛል። በአለም ዙሪያ የሰብአዊ መብቶችን ለመደገፍ ቃል የገባው ቴክኖሎጂ በአምባገነን መንግስታት ቁጥጥር አማካኝነት ለብዝበዛ እና ያለአግባብ መጠቀሚያ እየሆነ ይገኛል። በበለጠ መብቶችን የሚያከብር መጪ ጊዜን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

> “በዚህ በዲጂታል መናጋት ዘመን የሰብአዊ መብቶችን አሁን እና በቅርቡ ለማስጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ተግዳሮቶች እና ዕድሎች ምንድናቸው?”

ለዲጂታል ዘመን የሰብአዊ መብት ጥበቃዎችን ስናስብ በሁሉም ቦታ በሚገኝ የመረጃ አሰባሰብ የግል ሚስጢር የመጠበቅ መብታችን ምን ማለት ነዉ? ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ ሰዎች የሚጋሩአቸዉ የበይነመረብ ቦታዎች በግል ድርጅቶች ቁጥጥር ስር ሲሆኑ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ነፃነት ጋር እንዴት ይጣጣማሉ? ያልተፈቀደ ዳሰሳን ለማገድ ከተዘጋጁት ሲስተሞች ጀርባ ለተጠመዱት የመረጃ ተደራሽነት ምን ማለት ነው? በአልጎሪዝም ዘመን የኛ መብት ምንድነዉ ነው?

መብቶቻችንን የመለማመድ እና የማጣጣም አቅማችን በዲጂታል መሳሪያዎች ላይ የተመረኮዘ ነዉ፡፡ እስካሁን የበይነመረብ አገልግሎት ያላገኙ ወይም በኃይል ከበይነመረብ የታገዱ ሰዎች ምን ይሆናሉ?

ምንጭ፡ Excerpt from Access Now.
Brett Solomon@solomonbrett
https://www.accessnow.org/un-human-rights-digital-disruption/

ዲጂታል መብት ምን ማለት ነው?

ብዙዎች ዲጂታል መብቶችን ከሰው ልጅ፣ ከኮምፒውተር፣ ከመረጃ መረብ እና ፣ ከመሳሪያዎች ጋር ያለውን ትስስር ላይ ትኩረት በማድረግ ያብራሩታል። አንዳንዶች ደግሞ የባለቤትነት መብት ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት ይሰጣሉ።

ህይወታችን ይበልጡን ዲጂታል እየሆነ በሄደ መጠን እነዚህ አቋሞች እና ትርጓሜዎች ትክክለኛ ይመስላሉ? መረጃዎቻችን በመንግስታትና በኮርፖሬሽኖች እየተሰበሰቡ ይገኛሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች መካከል በነጻነት ሃሳባችንን የመግለጽ መብቶች፣ የመሰብሰብ ነጻነት እና የመሳሰሉት መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶቻችን ተያይዘዋል። በዲጂታል መብቶች እና በሰብአዊ መብቶች መካከል የነበረው ልዩነት ከጊዜ በኋላ እየደበዘዘ መጥቷል።

ዲጂታል መብቶች በዲጂታል ስፍራዎች ውስጥ ተፈጻሚ ሚሆኑ የሰብአዊ መብቶች ናቸዉ፡፡ የሰብአዊ መብቶች በአካል በተገነቡ ቦታዎች መሠረተ ልማቶች እና መሳሪያዎች እና በበይነመረብ በተገነቡ ማንነቶቻችን እና ማህበረሰቦቻችን ሁሉ ቦታዎች ላይ።

ዲጂታል መብቶች ሰብአዊ መብቶች ከሆኑ ለምንድን የተለያየ ስያሜ እንጠቀማለን? “ዲጂታል መብቶች” የሚለው ስያሜ መሰረታዊ መብቶቻቸ እና ነጻነታችንን የምንተገብርበትን ቦታ ለማመላከት ያገለግላል። ዲጂታል መብቶቻችን ስጋት ላይ ስለሆኑ ይህ አስፈላጊ ነው።

ኢ.ኤ.አ በ 1995 ሂላሪ ክሊንተን በቤዢንግ በተካሄደው በሴቶች ኮንግረስ ላይ “ሰብአዊ መብት የሴቶች መብቶች ናቸው” እንዲሁም የሴቶች መብት ሰብአዊ መብቶች ናቸው” ሲሉ መግለጻቸው አስፈላጊ እንደነበረው እንዲሁም ፕሬዚዳንት ኦባማ ኢ.ኤ.አ በ2016 ዓ.ም የLGBTQ መብቶች ሰብአዊ መብቶች ስለመሆናቸው በአፅንኦት እንደተናገሩ ሁላችንም የዲጂታል መብቶች ሰብአዊ መብቶች መሆናቸውን እና መጠበቅ እንደሚገባቸው ልንገነዘብ ይገባል።

ምንጭ፡ IntLawGrrls
https://ilg2.org/2019/02/27/digital-rights-are-all-human-rights-not-just-civil-and-political/

የጥላቻ ንግግርን በኢትዮጵያ መቃወም

@EthiopiaCheck
ኢትዮጵያ ቼክ የኢንተርኒዉስ ፕሮጀክት ነው። እዉነታን ሚያጣራዉ የምርመራ ዴስክ የሚዲያ እና ማህበራዊ ሚዲያ ሪፖርቶችን ይከታተላል ተገቢ ምላሾችን ያዘጋጃል፡፡

ትዊተር፡ https://twitter.com/ethiopiacheck?lang=en
ፌስቡክ፡ https://www.facebook.com/EthiopiaCheck/

ይህ የእውነታ ማጣርያ የማኅበራዊ ሚዲያ ገጽ ሐሰተኛ ዜናዎችን በማረጋገጥ የታወቀ ነው፡፡
https://www.facebook.com/journalisteliasmeseret

የመብቶችና ዴሞክራሲ እድገት ማዕከል (CARD)
የመብቶችና ዴሞክራሲ እድገት ማዕከል (CARD) ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን የማየት ራእይ ያለው እና የዴሞክራሲ መርሆችን በማስተጋባት ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጫወታ ህግ እንዲሆን የማድረግ ተልዕኮ ያለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። CARD ዲሞክራሲያዊ የማድረግ ሂደቱን ለማገዝ መብቶች ላይ ያተኮረ መንገድ የሚከተል ድርጅት ነው። እንዲሁም ስርነቀል ወጣቶችን እና ሴቶችን በማብቃት የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ ለማድረግ ትልቅ ፍላጎት ያለው ድርጅት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በበይነመረብ ሚዲያ ላይ የሚታየው የጥላቻ ንግግር እና ሃሰተኛ መረጃ ቀን ከቀን እየጨመረ ነው። CARD የጥላቻ ንግግርን መዋጋት እና ዜጎች በሚዲያ ላይ ያላቸውን

ግንዛቤ መጨመር አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል። ስለዚህ CARD የበይነመረብ ተጠቃሚዎች የጥላቻ ንግግርን እና ሃሰተኛ መረጃን ለማስቀም የሚያግዛቸውን መመሪያ በሶስት የሃገር ውስጥ ቋንቋዎች አዘጋጅቷል። መመሪያውን በአማርኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በኦሮምኛ እና በትግረኛ ይገኛል።
https://www.facebook.com/CARDEthiopia
https://www.cardeth.org/
https://www.cardeth.org/anti-fake-news-hate-speech-guideline/

ኢትዮ ቼክ ላብ (EthioCheck Lab)

ኢትዮ ቼክ ላብ የመሪ ሚዲያ ኢንስቲትዩት እና ዶይቼ ቬለ (DW Akademie) አካዳሚ የጋራ ተነሳሽነት ነው፡፡ ለኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን አቅም ግንባታ እና ተቆማዊ ልማት ላይ ይሰራል በተለይም በመገናኛ ብዙሃን ውስጥ የእውነታ ማጣሪያ ዴስኮች ፣ ክፍሎች ወይም መዋቅሮችን በመደገፍ ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በአይስአዲስ (iceaddis) የተጀመረ እና ከአፍሪካ ኮድ (code for Africa) ጋር ተከታታይ አካባቢያዊ ልዉዉጥ በሰው-ተኮር የንድፍ አሠራር ውጤቶች ላይ እየጨመረ የመጣውን የተዛባ መረጃ እና አሳሳች መረጃ ችግር ለመፍታት ፕሮጀክቱም በጀመርን ፌዴራል ኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር (BMZ) ድጋፍ የተሰራ ነዉ፡፡
https://mersamedia.org/
https://www.dw.com/en/dw-akademie/africa/s-12135

ዴስትኒ ኢትዮጵያ (Destiny Ethiopia)

የዴስትኒ ኢትዮጵያ (Destiny Ethiopia) አሁን ላለው የፖለቲካ ሁኔታዎች ምላሽ ለመስጠት የተጀመረ ሃገር በቀል ተነሳሽነት ነው። የዴስትኒ ኢትዮጵያ (Destiny Ethiopia) ቡድን ከተለያዩ ሃገራት ልምድ በመቅሰም ኢትዮጵያ ያለችበትን የተገታ ሁኔታ በመስበር አማራጮችን እየፈለጉ ይገኛሉ። ከተለያዩ የህይወት መስመሮች የመጡ 50 አባላት ያሉት የወደፊት ተስፋ ቡድን በሚቀጥሉት 20 አመታት ውስጥ ለኢትዮጵያ 4 የተለያዩ ተስፋዎችን ለማዘጋጀት በ6 ወር ጊዜ ውስጥ በሚስጥራዊነት ተሰባስበዋል።

አራቱ የወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ኢትዮጵያዊያን ለእነዚህ ተግዳሮቶች ምላሽ ሊሰጡበት የሚችሉበት መንገዶችን ያሳያሉ። የመጀመሪያው ሁኔታ ‘ሠባራ ወንበር’ ምላሻችን ‘ተጨባጭ’ ነዉ በአሁኑ ወቅት ባለው አቅም ውስጥ በጥንቃቄ መስራት ነገር ግን ለተግዳሮቶቹ የሚበቃ አይደለም። ሁለተኛው ሁኔታ አፄ በጉልበቱ ሃገሪቷ ላይ ያሉት ተግዳሮቶች ጠንካራ በመሆናቸው ጠንካራ መፍትሄዎችን ይሻሉ ከሚለው አስተሳሰብ በመነሳት ምላሻችን አምባገነን እና ተቆጣጣሪ ነው። ሶስተኛው ሁኔታ የፉክክር ቤት ምላሻችን ያልተሟላ ነው ምክኒያቱም የተለያዩ ቡድኖች እያንዳንዳቸው በበለጠ ነፃነት እርምጃ ይወስዳሉ ይህ የበለጠ መከፋፈልን ይፈጥራል። አራተኛው ሁኔታ ንጋት ምላሻችን ቀስ በቀስ ያለማቋረጥ ተቋማዊ አቅምን በመገንባት ዲሞክራሲያዊ ሽግግርን ለማከናወን ያስችለናል።

የሰላምና ልማት ማዕከል (PDC)

የሰላምና የልማት ማእከል በኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ ላይ ግጭት መከላከል ፣ ግጭት አፈታት ፣ ሰላም ግንባታ እና ልማት ላይ የሚሰራ ራሱን የቻለ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። PDC ለሰላም ግንባታ ፣ ለሽምግልና ፣ ግጭትን ለመከላከልና መፍትሄ ለመፈለግ ፣ ለሰላም ትምህርት ፣ የሌሎች የጋራ መከባበርን ለመቀበል ፣ የባህልና የሃይማኖቶች ውይይት እና እርቅ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።
https://pdcethiopia.org/

ኔትወርክ የጥላቻ ንግግር ለመቃወም (Network Against Hate Speech)

የጥላቻ ንግግሮችን እና ጥቃትን ሚያነሳሱ ፅሁፎችን የሚያሰራጩ ሰዎች ለልጥፎቻቸዉ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ሚሰራ ተነሳሽነት ነው ፡፡ የፌስቡክ የማህበረሰብ መመሪያዎችን ማህበረሰባዊ አግባብነት እንከተላለን፡፡ እኛ የጥላቻ ንግግሮችን እና በየትኛውም ደረጃ ማንኛውንም ዓይነት ጥቃት የምንቃወም ኢትዮጵያውያን ነን፡፡
https://www.facebook.com/networkagainsthatespeech/

እውነት ቼክ (Ewnet Check)

https://ewnet.et/

Medium: https://medium.com/ewnet-check
ቴሌግራም ቻናል: https://t.me/EwnetCheck

የቴሌግራም ቡድኖች / ቻናሎች ምሳሌዎች
https://web.telegram.org/#/im?p=@tikvahethiopia
https://web.telegram.org/#/im?p=@kelelaguides

መልመጃ፣ በበይነመረብ እና በማህበረሰባችሁ ውስጥ ስላለ የጥላቻ ንግግር ተወያዩ

የጥላቻ ንግግር ዒላማዎች እነማን ናቸው?

በአጠቃላይ በማህበረሰብ ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

በበይነመረብ ላይ የጥላቻ ንግግሮችን እንዴት መከላከል እንችላለን?

- የጥላቻ ንግግር ተጠቂ የሆኑ ሰዎችን እንዴት ሊጎዳ ይችላል?
- እነዚህ የጥላቻ ንግግር ምሳሌዎች ራሳቸውን የተጠቂው ማህበረሰብ አባል ለሚያደርጉ ሰዎች ምን ያስከትላል?
- በሬዲዮ፣ በአካል ወይም በበይነመረብ ላይ የጥላቻ ንግግር ወይም አደገኛ ንግግር በሚሰሙበት ጊዜ ምን ይሰማዎታል?
- በማህበረሰብዎ፣ በቤተሰብዎ ወይም በትምህርት ቤትዎ ውስጥ የጥላቻ ንግግር እንዳይስፋፋ ለማስቆም ምን ማድረግ ይችላሉ?

ተግባር ተኮር ጥናት፡ አበባ ንግግር ዘመቻ (FLOWER SPEECH CAMPAIGN)

https://beautifulrising.org/tool/flower-speech-campaign

እ.ኤ.አ በ 2014 በማይነማር ውስጥ እየጨመረ ለመጣው የፀረ-ሙስሊም ጥቃቶች ምላሽ ለመስጠት Panzagar #አበባ ንግግር ዘመቻ(#FlowerSpeech) የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል ተጀመረ። የዘመቻው ቁልፍ ምስል የሆኑት አበቦች በማይነማር ሰላምን ያመላክታሉ። ዘመቻው የቡድሂስት የእምነት መመሪያ 'እውነተኛ ንግግር' ወይም የዘለፋ ፣ የሚከፋፍል ወይም ጎጂ ንግግሮችን በማስወገድ የስነምግባር ደምብና ስረዓትን በመጥቀስ በቡድሂስት ፅንፈኞች መካከል የነበረ የጥላቻ ንግግርን መቃወም ችሏል (መርህ፡ ማህበረሰቦን ይወቁ)።

የቡድሂስት መሰረታዊ የእምነት መመሪያ የስነምግባር ደምብና ስርዓት ለማመላከት ባህላዊ አበባዎች በአፍ መያዝ ለአነጣጠረው ታዳሚ እንዲሁም በሌሎች ባህሎች ዘንድ መልእክቱን የተለመደ እና ቀላል እንዲሁም አሳማኝ አድርጎታል። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለንን ንቁ ተሳትፎ እና ህዝባዊ ኩነቶች ፣ ሙዚቃ እና የሚለጠፉ መልእክቶች በማጣመር ዘመቻው ሰዎች እንዲሳተፉ በጣም ቀላል ያደርግላቸዋል (መርህ: የተለያዩ የመግቢያ ቦታዎችን ፍጠር) እንዲሁም ንቁ ያልነበሩ ደጋፊዎች ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ያደርጋል (ስነ ዘዴ : የአጋሮች ምድብ ትንታኔ)።

በመጨረሻም የዘመቻውን መልእክት ወደ ቀላል ፣ ሃያል እና ባህል ሚያስተጋባ ምስል በማድረግ መልእክቱ ለሚያየዉ ማንም ሰው በግልፅ እና በቀጥታ የሚገባው እንዲሆን በዘመቻው አረጋግጧል (Theory: Memes)። ፓንዛጋር ለሁሉም የጥላቻ ንግግሮች መፍትሄ አልሆነም ይልቁኑ ደጋፊዎች የጥላቻ ንግግር ሲያጋጥማቸዉ በቀላል መንገድ ምላሽ መስጠት እና ማምከን የሚያስችል መሳሪያ ሆኗል።

የፓንዛጋር ዘመቻን የመራው ጦማሪ እና የማህበረሰብ አነቃቂ የሆነው Nay Phone Latt "መፈክራችን ለመጠንቀቅ ነዉ እነጂ ዝም ለማለት አይደለም" ብሏል። "ሃሳባችንን የመግለጽ ነፃነታችንን አሁን አግኝተናልና መታፈን አንፈልግም"።

https://www.washingtonpost.com/national/religion/using-flower-speech-and-new-facebook-tools-myanmar-fights-online-hate-speech/2014/12/24/3bff458c-8ba9-11e4-ace9-47de1af4c3eb_story.html

#ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ የሰላም አምባሳደሮች
#HATEFREEETHIOPIA

#ThinkB4UClick

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሰላም አምባሳደር ለመሆን የሚረዱ መመሪያዎች

- [x] ማንኛውም መረጃ ከማውጣቴ በፊት አረጋግጣለሁ
- [x] አንድነትን ሚፈጥሩ ንግግሮችን ብቻ አደርጋለሁ
- [x] ከመጫኔ በፊት አስተውላለሁ
- [x] ከመለጠፌ በፊት እመረምራለሁ
- [x] ለድርጊቶቼ ሃላፊነትን እወስዳለሁ

3

የማኅበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ

03 የማህበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ

ይዘቶች

የጥላቻ ንግግር እና አደገኛ ንግግር

አደገኛ ንግግር ፣ ተግባራዊ መመሪያ

የአደገኛ ንግግር ፅንሰ ሃሳብ እና ትንተና

መልመጃ፣ የጥላቻ ንግግር እና አደገኛ ንግግር ግንዛቤ

የዲጂታል ሚድያ ግንዛቤ

ፈርስት ድራፍት (FIRST DRAFT) **በበይነመረብ ላይ የሚገኝ መረጃ ማረጋገጫ መሰረታዊ መመሪያዎች**

የማረጋገጥ ስልጠና [ቪዲዮ]

የተዛባ መረጃ (DISINFORMATION) **በሚድያ እና በማህበራዊ ሚዲያ**

ጥያቄዎች ለቡድን ውይይት

#እዉነታዎችዋጋአላቸዉ (#FACTSMATTER)

መልመጃ ፡ #እውነታዎችዋጋአላቸው (#FACTSMATTER)

#ለሰላምእርምጃይውሰዱ (#ACT4PEACE)

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 3

የማህበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ

?

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

አደገኛ ንግግር እና የጥላቻ ንግግር ምንድን ናቸዉ?

የዲጂታል ሚዲያ ግንዛቤ ለምን ያስፈልጋል?

የተዛባ መረጃን እንዴት ማቆም እንችላለን?

የጥላቻ ንግግር እና አደገኛ ንግግር

> “አደገኛ ንግግር (ለምሳሌ ንግግር ፣ ጽሑፍ ወይም ምስል) ታዳሚዎቹ በሌላ ቡድን አባላት ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩበትን ወይም የሚደግፉበትን እድል ከፍ ሊያደርግ የሚችል ማንኛውም ዓይነት አገላለጽ ነው፡፡”

አደገኛ ንግግር ፡ ተግባራዊ መመሪያ

by Susan Benesch, Cathy Buerger, Tonei Glavinic, and Sean Manion December, 2018
https://dangerousspeech.org/guide/

የጥላቻ ንግግር አደገኛ ንግግር የሚሆነው መቼ ነው?

አደገኛ ንግግር ታዳሚዎችን ጥቃትን እንዲያበረታቱ ወይም ተሳታፊ እንዲሆኑ በማንቀሳቀስ የብዙሃን አመፅን ለማስነሳት የሚችል መልእክት ነው።

ምስል፡ Peter Durand CC-BY-SA

የጥላቻ ንግግር ፕሮጀክትን የሚመሩት በአሜሪካ በዋሺንግተን የሚገኝ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ መምህር የሆኑት ሱዛን ቤኔሽ በጥላቻ ንግግር እና በአደገኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት ሲያብራሩ (ፅሁፍ፣ ምስላዊ እንዲሁም ንግግር ሊሆን ይችላል) በአብዛኛው የት ተባለ ፣ ማን ተናገረው እንዲሁም ለማን የሚሉት ላይ መሰረት ያደርጋል።

በተለይ የሚከተሉት ላይ:

- በከፍተኛ ደረጃ ተሰሚነት ያላቸው እንዲሁም እጅግ አሳማኝ የሆኑ ተናጋሪዎችን።
- ተናጋሪው በሚያሰርፀው ቅሬታ ወይም ፍራቻ ምክንያት የሃይል እርምጃዎችን የመውሰድ ዕድላቸው ከፍተኛ የሆኑ ተከታዮች።
- የንግግሩ ታሪካዊ እና ህብረተሰባዊ አውድ በተለይም ታዳሚዎች ዘንድ እንደ አመፅ ጥሪ ሊረዱት የሚችሉ ከሆነ። እንዲሁም ለቅሬታዎች ወይም ከዚህ ቀደም በተለይም በሚያስቆጣ ንግግር አማካኝነት ለተነሱ አመፆች መፍትሄ ለማግኘት የሚያስችል አሰራር ያለመኖር እንዲሁም በቡድኖች መካከል ለረጅም ጊዜ የቆየ የስልጣን ወይም የሀብት ፉክክር ከነበረ ትልቅ ሚናን ይጫወታል።
- ዜናው ወይም መረጃው የተሰራጨበት መንገድ ብቸኛ ወይም ቀዳሚ የዜና ምንጭ ወይም እንደ ታዋቂ የማህበራዊ ሚዲያ ገፅ ያሉ ተደማጭነት ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ከሆነ።

አደገኛ ንግግርን እንዴት መቃወም ይቻላል

በበይነመረብ ላይ በትዊት፣ በፌስቡክ ልጥፎች ወይም በአስተያየቶች መልክ አደገኛ ንግግሮችን ማግኘት የተለመደ ነው። Susan Benesch "Considerations for Successful Counterspeech" በሚለው ፅሁፏ ላይ ለአደገኛ ንግግሮች መልስ በምንሰጥበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን ምክር ታቀርባለች።

- ተናጋሪውን/ዋን በተጠቂዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በእራሳቸው ላይ ስለሚከተለው ችግር ማስጠንቀቅ። ይፋዊ ልጥፎች በመሰረቱ ቋሚ በመሆናቸው የአሁን እንዲሁም የወደፊት አሰሪያቸው፣ ጓደኞቻቸ እና ቤተሰቦቻቸው ሊያዩት እንደሚችሉ እና ይህም ከስራቸው ወይም ከሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሊያሳጣቸው እንደሚችል መግለጽ።
- ብዙ ሰዎች ራሳቸውን በዚህ መልኩ እንደማያዩ በመግለፅ ንግግሩ ለምን አስከፊ ፣ ዘረኛ ፣ ሴቶችን የሚያጥላላ ወዘተ እንደሆነ ማስረዳት።
- በአክብሮት አነጋገሮን ለመቀየር መሞከር (ለምሳሌ እኔም 'ሀ' ነኝ ግን) ወይም በማስተሳሰር (ለምሳሌ የተናገሩት እንደ 'ለ' እኔን አሳዝንኖኛል)።

- መልእክቱን ለማቅለል ቀልድን ይጠቀሙ። ቤኒሽ የበይነመረብ ተጠቃሚዎች የፕላስቲክ ዳክዬ ጭንቅላት ምስሎችን በ አይኤስአይኤስ (ISIS) አባላት ላይ በመደረብ ለመሳለቅ እንዲሁም አስፈሪ እንዳልሆኑ ለማስመሰል ያደረጉትን ጥረት ትጠቅሳለች፡፡

ተናጋሪው አስተያየቱ ስህተት መሆኑን አምኖ/ና ይቅርታ ይጠይቃል/ትጠይቃለች ብሎ ማሰብ ትልቅ ተስፋ ማድረግ ነው። የስኬቱ ምልክት ሊሆን የሚችለው ተናጋሪው ንግግሩን ከለወጠ ወይም የማህበራዊ ሚዲያ መጠቀምያዉን ከሰረዘ ነው።

ብዙውን ጊዜ ለአደገኛ ንግግር በጣም ጥሩ ምላሽ የሚሆነው ተጨማሪ ንግግር ነው። መልሶ ጠንካራና ትህትና የተላበሰ ክርክርን ካነሳሳ ሀሰትን ለማስወገድ እና ሌሎች ጥቃት ቅስቀሳን እንዲቃወሙ ሊያበረታታ ይችላል።

ምንጭ: Excerpt from Yali Checks: Young African Leaders Initiative
https://yali.state.gov/what-constitutes-dangerous-speech-and-what-can-you-do-about-it/

የአደገኛ ንግግር ፅንሰ ሃሳብ እና ትንተና

ቪዲዮ (ፍላሽ) ላይ ይመልከቱ

Susan Benesch introduces the concept and analysis of Dangerous Speech
https://dangerousspeech.org/what-is-ds/

የአደገኛ ንግግር ፕሮጀክት እ.ኤ.አ ጥር 24, 2018 ዓ.ም
የባለቤትነት መብት 2020 አደገኛ ንግግር ፕሮጀክት
Dangerous Speech Project, January 24, 2018
© Copyright 2020 Dangerous Speech Project

መልመጃ፣ የጥላቻ ንግግር እና አደገኛ ንግግር ግንዛቤ

አንድን ንግግር አደገኛ ንግግር ወይም አመፅን የሚያነሳሳ የሚያደርገው ምንድን ነው?
ግልጽ የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ የሚያቀርብ ከሆነ- ሁልጊዜ የጥላቻ ንግግርን አያጠቃልም።

የጥላቻ ንግግር ምሳሌዎቹን አውድ እና አላማ ላይ ተወያዩ።

- [የአመቻቾች ማስታወሻ ላይ ያሉ A2 ፖስተር እና መልመጃዎችን ተመልከቱ]

1. **የተለያየ አይነት የጥላቻ ንግግር ወይም አደገኛ ንግግርን የሚያሳየውን ምስል ይመልከቱ።**

2. **በግሎ ይህን መሰል ሁኔታዎች ካጋጠሞ ለቡድኑ ምሳሌዎችን መርጠው ያጋሩ።**
   - ሰዎች አመፅን የሚቀሰቅስ የጥላቻ ወይም አደገኛ ንግግርን በበይነመረብ ላይ ሲያጋሩ ተመልክተዋል?

3. **ይህንን ማቴርያል እና ፖስተር በመጠቀም የተለያዩ የጥላቻ ንግግር አይነቶች ላይ ተወያዩ።**
   - የጥላቻ ንግግር ከአደገኛ ንግግር እንዴት እንደሚለይ ተወያዩ።
   - የአደገኛ ንግግር ክፍፍሎች ምን ምን ናቸው? እንዴት ለይተው ማወቅ ይችላሉ?

የዲጂታል ሚድያ ግንዛቤ

ማህበራዊ ሚዲያን እውቀት ላይ በተመሰረተ አመለካከት ለመጠቀም የሚድያ እና የመረጃ ግንዛቤ በጣም አስፈላጊ ነው። የሚከተሉት መመሪያዎችና ማስታወሻዎች የታተሙት First Draft News ፣ UNESCO እና ትዊተር ነው። ጥልቅ ግንዛቤ ካላቸው አንባቢዎች እና ጋዜጠኞች ጋር በመሆን የተዛባ መረጃን መዋቅርን ለማፍረስ እና የአለምን ሚድያን ለማሰስ የሚረዱ ተግባራዊ መሳሪያዎች እና ክህሎቶችን ያቀርባል።

ፈርስት ድራፍት (First Draft) ጋዜጠኞችን ብቻ ሳይሆን የተዛባ መረጃ መስፋፋትን ለማስቆም የሚረዱ በንቃት የሚሳተፉ አንባቢ ዜጎች ለማረጋገጥ የሚጠቅሙባቸው መሳሪያዎች እና ክህሎቶች ስልጠና መስፈርት ነው። በዘገባ ላይ ያሉትን ለመርዳት የተቋቋመው አለም አቀፋዊ ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ፣ የማንኛውም ፓርቲ ደጋፊ ያልሆነ ድርጅት የሆነውፈርስት ድራፍት (First Draft) ጥናቶች መረጃ ላይ መሰረት ያደረገ ተግባራዊ መመሪያ እና ስልጠና ያቀርባል። በአለም ዙሪያ ከሚገኙ አጋሮች ጋር በመሆን ክህሎቶችን ፣ መሳሪያዎች እና ስነ ዘዴ ዎች ያለማቋረጥ ይፈተሻሉ እንዲሁም ያሻሽላሉ።

መሰረታዊ መመሪያዎች የመረጃ መዛባትን መረዳት

የምንኖረዉ በመረጃ መዛባት ዘመን ነው። የዲጂታል ዘመን ተስፋ በአንድድ መጫን ወይም ማንሸራተት ማንኛውንም የምንፈልገውን መረጃ በቀላሉ ማግኘት የምንችል በከፍተኛ ደረጃ የተሳሰረ ማህበረሰብ ውስጥ መኖር አዎንታዊ ለውጦች ብቻ ይዞ እንደሚመጣ እንድናምን አበረታቶናል።ነገርግን ይህ ፍፁም የሆነ ራእይ የመረጃ ምህዳራችን በአሁኑ ሰዓት በአደገኛ ሁኔታ መበከሉን እንዲሁም ከማስተሳሰር ይልቅ እየከፋፈለን እንደሆነ ወደ መቀበል ሁኔታ ተለውጧል።

ፈርስት ድራፍት (First Draft) የመረጃ መዛባትን ለመረዳት መሰረታዊ መመሪያዎች ላይ 7 የተሳሳተ እንዲሁም የተዛባ መረጃ አይነቶች መዋቅርን በዝርዝር ያስረዳል። የመረጃ መዛባት በአለም ዙሪያ በምርጫዎች እና የሰበር ዜና ኩነቶች ላይ ምን ያህል ጎጂ እንደነበረ ምሳሌዎች ያሳስባሉ።

ምንጭ፣ ፈርስት ድራፍት (First Draft) የዜና መረጃ መዛባትን መረዳት (PDF) 2019
https://firstdraftnews.org/wp-content/uploads/2019/10/Information_Disorder_Digital_ AW.pdf?x32994

መሰረታዊ መመሪያዎች፡ በበይነመረብ ላይ የሚገኝ መረጃ ማረጋገጫ

በበይነመረብ ላይ የሚገኙ መረጃዎችን ማረጋገጥ አስቸጋሪ ሊመስል ይችላል ነገር ግን ከባድ አይደለም።

ማረጋገጥ ላይ ጥሩ/የተሻለ ለመሆን ብዙውን ጊዜ የሚጠይቀው ድግግሞሽ ፣ ፅናት እና የዲጂታል የምርመራ መሳሪያዎች መጠቀም ከትንሽ ፈጠራ ጋር ነው። በአሁኑ ወቅት ብዙ የማረጋገጫ ስነ ዘዴ ዎች እና መሳሪያዎች ይገኛሉ። ይህ ለማረጋገጥ አጭር መመሪያ ነው። መሰረታዊ ሃሳቦችን ፣ ጠቃሚ ምክሮች እና ስነ ዘዴ ዎችን እንዲሁም ሊደረጉ የሚገባቸው ተግባራት ዝርዝርን ያጠቃልላል። በዋነኝነት አምስቱን የማጣራት ምሰሶዎች ያስተዋውቃችኋል።እንዲሁም እያንዳንዱን እንዴት እንደምንጋፈጥ እንደ ማጣቀሻ ያገለግላል።

የማረጋገጥ ስልጠና [ቪዲዮ]

ለሚዲያ ማጣራት ፈጣን ጅማሮ
https://firstdraftnews.org/en/education/course/verification-quick-start/1/

የማረጋገጥ ስልጠና ለጋዜጠኞች
https://firstdraftnews.org/en/education/course/verification-curriculum/1/lesson-1-intro-wardle

5 መሰረታዊ የእይታ ማረጋገጫዎች

ባለቤትነት
ዋናውን ይዘት (original content) እየተመለከቱ ነው?

ምንጭ
ዋናውን ይዘት የዘገበው ማን ነው?

ቀን
ይዘቱ የተዘገበው መቼ ነበር?

ቦታ
ይዘቱ የተዘገበው የት ነበር?

ተነሳሽነት
ይዘቱ የተዘገበው ለምን ነበር?

ማረጋገጫ

ምንጭ፡ፈርስት ድራፍት (First Draft) በበይነመረብ ላይ ለሚገኝ መረጃ ማረጋገጫ መሰረታዊ መመሪያዎች (PDF) 2019
https://firstdraftnews.org/wp-content/uploads/2019/10/Verifying_Online_Information_Digital_AW.pdf?x32994

ፈጣን ማጣቀሻ መመሪያ (በበይነመረብ)
https://firstdraftnews.org/latest/verifying-online-information-the-absolute-essentials

የተዛባ መረጃ (DISINFORMATION) በሚድያ እና በማህበራዊ ሚዲያ

https://defyhatenow.org/media-social-media-disinformation-2/

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

የተዛባ መረጃ ምንድነዉ?

ጉዳት እንዴት ያስከትላል?

ከሐሰተኛ ይዘት ማን ይጠቀማል?

- ታሪኩ ሚዛናዊ /ገለልተኛ/አድሎአዊ ነው?
- ማህበራዊ ሚዲያ በአዘጋገቡ ላይ እንዴት ተጽእኖ ያሳድራል?
- የተሳሳተ መረጃ (misinformation) ሊሆን የሚችል ምን አሉባልታዎች ወይም ታሪኮች ሰምተዋል?
- የት ነው የሰሙት - በማህበራዊ ሚዲያ በኩል፣ በአካል፣በስልክ፣ በተለመዱ የመገናኛ ብዙሃን (የዜና ድረገዖች፣ ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን) ላይ ተዘግቦ?
- የተሳሳተ መረጃ እርሶ እና ማህበረሰብ ላይ እንዴት ተፅእኖ ያሳድራል?
- ታሪኩ እውነት ወይም ሃሰት መሆኑን በምን ይወስናሉ?
- መረጃን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምን መሳሪያዎች አሉት?
- ታሪኩ ፕሮፓጋንዳ ነው ማን ሊጠቀም ይችላል?
- ምንጩ ማን እንደሆነ ይለዩ ከዚያን በኋላ አጀንዳቸውን ወይም አላማቸውን ይጠይቁ።

#እዉነታዎችዋጋአላቸዉ #FACTSMATTER

የጥላቻ ንግግር ማነቃቂያ እና ግንዛቤ

ሚዲያን ለማሰስ የሚያስችል ክህሎት እና መሳሪያዎች ያላቸው በንቃት የሚሳተፉ እና የሚዲያ እውቀት/ግንዛቤ ያላቸው አንባቢዎች።

የተዛባ መረጃ፣ የጥላቻ ንግግር እና አመፅ ማነሳሳትን እና መስፋፋት እናቁም

- **በባህላዊ መገናኛ ብዙሃን** - ህትመት ፣ ሬዲዮ ፣ ስነምግባራዊ ጋዜጠኝነት
- **በማህበራዊ ሚዲያ በኩል** - ተሳታፊ ጦማሪ ዜነች ፣ አንባቢዎች ፣ አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች
- **በግል ቡድኖች ውስጥ** - ዋትሰፕ ፣ የፌስቡክ ቡድኖች
- **ቻናሎችና እና አቀራረብ** - ቪዲዮ ፣ የግል ቻት / ልጥፎች / ማጋራት / አስተያየት

በወርክ ሾፕ ወቅት ለእያንዳንዱ የተሳሳተ መረጃ/የተዛባ መረጃ (misinformation/disinformation) አይነቶች ምሳሌዎችን ፈልጉ፥

- ሃሰተኛ ይዘት
- የተዛባ ይዘት
- የፈጠራ ይዘት
- ከርእዮተ አለም ጋር የተዛመደ/ፕሮፖጋንዳ/ የተከፈለ
- ሆን ተብሎ ከአዉድ ዉጪ
- የተዛባ/አታላይ/ምፀት/ቀልድ

መልመጃ : #እውነታዎችዋጋአላቸው (#FACTSMATTER)

በኢትዮጵያ ዉስጥ የተሳሳተ መረጃ/የተዛባ መረጃ (misinformation/disinformation) አሉባልታ፣ ሃሰተኛ ወይም የተዛባ ይዘት፣ የውሸት/የፈጠራ ይዘት እና ፕሮፓጋንዳ ታሪኮች ምሳሌዎችን ይፈልጉ። የእነዚህ አይነት የተሳሳተ መረጃ እና አሉባልታዎች በማህበረሰብ ዉስጥ ግጭትን ለማባባስ ወይም ለመቀነስ ያላቸውን ተፅእኖ ለማሳየት በጥንቃቄ ያንብቧቸው። ታሪኩን ከይዘት እና ዝርዝር አንስቶ ፣ መስፋፋቱን እና ውጤቱን ሁሉንም ነገር ይጠይቁ።

1. **ታሪኩ ስለምንድን ነው?**
   - ☐ ታሪኩ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ሃሳቦችን ይግለጹ።
2. **የትኛው የተሳሳተ መረጃ ምድብ ነው?**
   - ☐ ይዘቱ ሐሰተኛ፣ የፈጠራ ወሬ ወይም የተጭበረበረ የሆነው በምን መንገድ ነው?
3. **የተስፋፋው እንዴት ነው?**
   - ☐ በምን ቻናሎች? ዋትሰፕ ቡድኖች ፣ ፌስቡክ ፣ ትዊተር ፣ ኢንስታግራም ወዘተ
4. **በእርሶ ፣ በማህበረሰቦ ፣ በሃገር ላይ ያለው ተፅእኖ ምን ነበር?**
   - ☐ የሰዎች ስሜታዊ ምላሽ? የመልእክቱ መሰራጨት?
   - ☐ ወደ አመፅ/በቀል/እስር መርቶታል?
5. **ታሪኩ እንዴት ነዉ የተዳሰሰዉ?**
   - ☐ የመጀመሪያው ልጥፍ ሀሰተኛ ነዉ ተብሎ ወርዶአል/ ስህተቶች ተስተካክለዋል / እንደገና ታትሟል?

#ለሰላምእርምጃይውሰዱ (#ACT4PEACE)

እያንዳንዱ ግለሰብ ማህበራዊ ሚዲያን በሃላፊነት የመጠቀም እንዲሁም የጥላቻ ንግግር እና የተሳሳተ መረጃን በበይነመረብ ላይ በሚገኙ ዘዴዎች በመጠቀም የማመልከት ሃላፊነት አለበት። እንደ #እውነታዎችዋጋአላቸው (#FactsMatter) #ለሰላምእርምጃይዉሰዱ (#Act4peace) ያሉ ዘመቻዎች እና ተነሳሽነቶች ጋር በበይነመረብም ሆነ በገሃዱ አለም ላይ ነገሮች በምንረዳበት መልኩ ሆነው እንዲገለፁ ለሁሉም የበይነመረብ መድረክ ተጠቃሚዎች እንደ ማነቃቂያ መልእክት የሆኑ የዘመቻ መንገዶች ናቸዉ። በበይነመረብ ላይ የምናደርጋቸው 'clicks' (ጠቅታዎች) ሰላምን ለመገንባት ረጅም ርቀት ሊጓዙ ይችላል።

#ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ እንድትሆን እንስራ።

4

የሲቪል ማህበራት፣ የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ

04 የሲቪልማህበራት፡ የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ

ይዘቶች

#DEFYHATENOW **የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ**

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በበይነመረብ

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከል፣ የጾታ እኩልነት እና የሴቶች መብት እንቅስቃሴዎች ምሳሌዎች

ሳይበር - ጥቃት (CYBER-BULLYING) **ለመከላከል የወጡ አፍሪካ መንግስታት ህጎች**

ምን ያህል ፍቅር አዋቂ ኖት

ሴፍ ሲስተርስ (SAFE SISTERS) **ቀላል መመርያ**

የሲቪል ማህበራት ተነሳሽነት ሚና

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 4

የሲቪልማህበራት፡ የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ

?

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

የሳይበር ጥቃት ምንድንነዉ?

ወሲባዊ ትንኮሳ ሴቶችን በበይነመረብ ላይ እንዴት ይነካል?

የሲቪል ማህበራት እርምጃ እና ትምህርት ለምን አስፈላጊ ነው?

#DEFYHATENOW የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደምብ

ብዙውን ጊዜ በይነመረብ የሚጽፉት ፣ የሚለጥፉት ሊንክ እና የሚመለከቱት የህዝብ መረጃ እና ለሁሉም ሰው የሚጋራ ነው ፡፡በአጠቃላይ የግል እና ሙያዊ አስተያየቶች መካከል ልዩነቶች አይደረጉም ፡፡ መግለጫዎች ታግ ማድረግ ወይም ሌሎች ድርጊቶች ለምሳሌ በፌስቡክ ላይ የተፃፉ አስተያየቶችን ላይክ ማድረግ ጨምሮ አውዱ ምንም ይሁን ምን የአመለካከትዎ ቀጥተኛ ነፀብራቅ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ምንም እንኳን የእርስዎ ዓላማ ባይሆኑም ከአውድ ወጥተው በእርስዎ ፣ በባልደረባዎችዎ ፣ በስራዎ ወዘተ ላይ በተቃራኒ ጥቅም ላይ ይውላሉ ፡፡

የጋራ መመሪያዎችን መቀበል እና መከተል ከተለመደው የወጡ ነገሮችን ፣ የፈጠራ ወሬዎች ወይም አሉባልታዎች የሚሰራጭበት መንገድ ለመለየት በመርዳት የጥላቻ ንግግር እና አመፅ ቅስቀሳን መከላከል ላይ የሚሰሩትን ስራ ያጠናክራል።

የማህበራዊ ሚዲያን አጠቃቀምን ‘መቆጣጠር’ የሚቻልም ሆነ የሚፈለግ ባይሆንም የእነዚህ መመሪያዎች ግንዛቤና በትክክል መተግበር የግል እና ሙያዊ ጥቅም አለው።

These guidelines are based on the “Journal of Mass Media Ethics” by Shannon A.Bowen (School of Journalism and Mass Communications, University of South Carolina, USA).

እሴት ፣ ተልእኮ እና አላማዎች

ለምን ይሄንን እንደምናደርግ በግልፅ መናገር በጣም አስፈላጊ ነው። የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻ የሚጀመረው እሴቶቻችንን እና አላማዎቻችንን በመረዳት በበይነመረብ ላይ ለማጋራት ስንዘጋጅ ነዉ። ይህ እነዚህ እሴቶችን የማያንፀባርቁ ልጥፎችን እንዳናጋራ እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ አወንታዊ ተፅእኖ ለማሳደር ምን እና መቼ እንደምናጋራ ለመምረጥ ያግዘናል።

ግቦች

- የማህበረሰብ ተሳታፊነት
- አዲስ የማህበረሰብ ክበብ/ቡድኖች እንዲሁም በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራን ለመድረስ
- #ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ (#HateFreeEtiopia) ገፅታ ግንባታ (ማህበራዊ ሚዲያ በይነመረብ እንዲሁም በገሃዱ አለም ሰዎችን ያሳትፋል)

ግልፅ ይሁኑ

ግልፅ በሆነ መንገድ መሥራት ድርጅትዎ ማህበራዊ ሚድያ ላይ አስተዋፆ ሲያደርግ ተመልካቾች ስለ ድርጅትዎ ዓላማዎች ወይም ትርጉሞች እንዳይታለሉ ሊያደርጋቸው ይችላል።

☐ ግንኙነት ሲኖር አንድን ድርጅት በመወከል ሚደረግ ንግግር ወይም እንደ ግለሰብ ሚደርግ ንግግር ተለይቶ መታወቅ አለበት።

☐ ለድርጅትዎ የማህበራዊ ሚድያ ይዘት አስተዋፆ ሚያደርጉ ሰዎች የግል ማህበራዊ ሚድያ ግንኙነቶችን እንዲለዩ መጠየቅ አለባቸዉ።

☐ የሚገለፁት አመለካከቶች ግላዊ ከሆኑ ግልፅ ይሁኑ፡፡ የራስዎ ብሎግ ወይም ሌላ የህዝብ ድረገፅ ካለዎት እንደዚህ ያለ ማስጠንቀቅያ ቢጠቀሙ ብልህነት ነው፡፡ በዚህ ድረገፅ ወይም ብሎግ ላይ የሚቀርቡት አስተያየቶች የራሴን እንጂ የተቋሜን ወይም የደንበኞቼን አቋም አያንፀባርቁም።

ግልፅ እና ወጥ ይሁኑ

ግልፅ መልክቶችን ይለጥፉ

☐ ልክቶችን ይለጥፉ ለሚለጥፉት ይዘት ሀላፊነት ይዉሰዱ፡፡ ስለሚለጥፉበት ጊዜ እና መንገድ ወጥነት ይኑርዎት ፣ ምክንያቱም ይህ ከተመልካቾች ጋር መተማመን እና መግባባት እንዲኖር ያስችልዎታል ይህም ለጠንካራ ግንኙነት ቁልፍ ነዉ።

ምንጭ እና ዳታ ያረጋግጡ

ሁል ግዜ ተዓማኒ ይሁኑ

☐ የተሳሳተ መረጃ አይጠቀሙ።

☐ አሉባልታዎችን አያጋሩ ወይም አያስተላልፉ ወይም ግምትን አይድገሙ።

እዉነታዎችን ያረጋግጡ

ሚለጥፉት መረጃ ላይ እዉነታዎችን ያረጋግጡ

☐ መጀመርያ መረጃዎችን እና አሉባልታዎችን ያረጋግጡ ከዛ የልጥፎን ይዘት ከመለጠፍዎ በፊት በምክንያታዊነት ይመዝኑ።

☐ አለመግባባትን ወይም የተሳሳተ ትርጓሜን ለመከላከል መልዕክቶችን ከሁሉም አመለካከቶች አንፃር ለመመርመር ይሞክሩ።

ትክክለኛ ይሁኑ

ልጥፎች ትክክለኛነታቸዉ እና እውነታዎቻቸዉ የተረጋገጡ እና ማረጋገጫ መስጠት የሚያስችሉ መሆን አለባቸው።

☐ ስህተት ከሰሩ በፍጥነት ማስተካከሎን ያረጋግጡ። ቢያጠፉትም የቀድሞዉን አስተያየት መጥቀስ አስፈላጊ ነዉ የሆነ ሰዉ በምስል ቀርፆ ሊያስቀምጠዉ ስለሚችል።

ሚዛናዊ እና አክባሪ ይሁኑ

በድርጅትዎ፣ በባልደረባዎ፣ በተፎካካሪዎ እና ሌሎች አካላት ላይ ተንኮል አዘል ፣ አሳሳች ወይም ኢፍትሃዊ ይዘት በጭራሽ አይለጥፉ፡፡

☐ ለማንም ግለሰብ የንግድ ምልክት ወይም ጎሳ ፀያፍ ስም አጥፊ ፣ ዛቻ፣ አድሎአዊ አይነት ይዘት ያለዉ ልጥፍ አይለጥፉ። ለሌላ ሰዉ በቀጥታ ማይሉትን አስተያየት አይለጥፉ። ከመለጠፍዎ በፊት ሌሎች ሰዎች እንዴት ምላሽ ሊሰጡ እንደሚችሉ ያስቡ። ኢ-ፍትሃዊ ነው ብለው

ለሚያስቡአቸዉ እትሞች አስተያየት ከሰጡ ሁል ጊዜ ትክክለኛ እና ሙያዊ ይሁኑ ፡፡ አዉነተኛ፣ ገንቢ እና አክባሪ መሆንን ያስታውሱ።

ሙያዊ ስነምግባር ያልዎት ይሁኑ

ሁልግዜ ሙያዊ ስርአት በተከተለ እና ገንቢ በሆነ መንገድ ይስሩ ከመለጠፎ በፊት ያገናዝቡ።

- ☐ የንግግሮት ቃና ጨዋነት ያለዉ እና የሌሎችን አስተሳሰብ አክባሪ ይሁኑ በተለይ ዉይይቶች እየከረሩ ሲሄዱ፡፡
- ☐ ለሌሎች ሰዎች ግላዊ ሚስጥር ተገቢ ግምት ይሰጡ፡፡

መልካም ይሁኑ

መልካምነትን ያበረታቱ ትስስርን ተሳትፎን እና ማህበረሰብን ለመገንባት ይረዳልና ።

- ☐ ይህን አመክንዮ በመከተል በሚለጥፉት እያንዳንዱ ልጥፍ አላማዎን ያስቡ፡፡ ዓላማዎም የድርጅቱን ፍልስፍና እና የማህበራዊ ሚዲያ ግቦችን እንዲሁም በቀላል የማይለዋወጡ ሰላማዊ እና መልካም ዓላማዎችን የሚያንፀባርቁ መሆን ይገባቸዋል ፡፡

ብልህ ይሁኑ

የንግድ ምልክት የተደረገባቸው ስሞችን ፣ መፈክሮችን እና የቅጂ መብት ያላቸው ይዘቶችን ጨምሮ የሌሎች ሰዎችን አእምሮአዊ ንብረቶች ያክብሩ።

- ☐ ሁሉም የበይነመረብ ይዘቶች የቅጂ መብት እንዳላቸዉ ያስቡ፡፡
- ☐ የቅጂ መብት ያላቸዉን ነገሮች ለመለጠፍ ፍቃድ እንዳልዎት ያረጋግጡ፡፡ አስፈላጊ ሲሆን ለስራዉ ቅጂ መብት ባለቤት እዉቅና ይስጡ፡፡ መቼም ቢሆን የሌላ ሰዉ ስራን እንደራስዎ አይጠቀሙ፡፡
- ☐ ማህበራዊ ሚድያ ላይ ሲያትሙ ሁሉንም ህጎች እና ደንቦች ያክብሩ ዳግም-የቅጂ መብት ፣ አይፒ ፣ ግላዊነት እና አይፈለጌ መልእክት፡፡

#defyhatenow Social Media Channels
Twitter: @defyhatenow + @defyhatenowEA
Facebook: defyhatenow
https://defyhatenow.org

ማህበራዊ ሚዲያ በሃላፊነት መጠቀሚያ መመሪያዎች

የማህበረሰባዊ ሚዲያ ይዘት መመሪያ

እያንዳንዱ ትዊት ፣ ልጥፍ ወይም ምላሽ መሆን ያለበት

- ☑ ለበይነመረብ ማህበረሰብ አዎንታዊ እና ትሁት
- ☑ ለመረዳት ቀላል እና የማያስቸግር
- ☑ በጥያቄዎች ወይም ለእርምጃ ጥሪ በማቅረብ ተሳትፎን ማበረታታት እና ማሳተፍ
- ☑ ከፖለቲካ የፀዳ / ከፖለቲኛ ገለልተኛ
- ☑ ተገቢ ቋንቋ ፣ ሰዋሰው ፣ እና አቀራረብ (የአነጋገር ዘዬ ችግር የለውም ነገርግን ሰዎች ላይረዱት ይችላሉ)
- ☑ ለእይታ የሚጋብዝ (ምስል ፣ ጥቅስ ወይም ቪዲዮ)
- ☑ ምንጮችን እና አነጋጋሪ ርእሶችን ለማጉላት ሀሽታጎችን (#)፣ የተጠቃሚ ስሞችን (@ስም) እና ታጎችን ይጠቀሙ

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በበይነመረብ

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች የማህበረሰብ አንቂዎች ድምፃቸውን ለማሰማት ፣ በፖሊሲ ውይይት ላይ የሥርዓተ-ጾታ ክፍተትን ለማቃለል እና የተለመዱ የሚዲያ አዉታሮች የማይሰጧቸውን ኔትወርኮችን ሚፈጥሩበት እና የሚበረታቱበት መድረክ ሆንዋል፡፡

የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች የስረአተ ጾታ እኩልነት ጉዳዮችን እንደ በፆታ ላይ የተመሠረተ መድልዎ ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ግልፅ ውይይትን በማበረታታት መፍትሄ ለመፈለግ ወሳኝ ሚና ሊኖራቸው ቢችልም በሌላ በኩል ደግሞ፡ ሴቶች ላይ የሚደርስ የበይነበረብ ጾታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት፡ ለምሳሌ ተጎጂን ማዋረድ ፣ ማስፈራራት ፣ እንዲሁም የተዛቡ አመለካከቶች፣ አድልዎዎች እና ቅድመ-ፍረጃዎች በእነዚህ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ትርጉም ያለው የህዝብ ውይይት እንዳይኖር እንቅፋት ይሆናሉ።

በተጨማሪም የበይነመረብ ውስን ተደራሽነት እና በመንግስት በተደጋጋሚ መዘጋት የዜጎችን ድምጽ ሳንሱር ሳይደረግ በበይነመረብ ላይ ለመወያይት እና ለመከራከር እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ የበይነመረብ መሠረተ ልማት ለመገንባት ሌላ ፈታኝ ሁኔታ ጨምሮአል፡፡ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ብዙ የሲቪል ማኅበራትን፣ የሰብአዊ መብት ተሞጋቾች እና የፌሚኒስት ማህበረሰብ አንቂዎች በበይነመረብ ተደራሽነት ፣ አጠቃቀም እና ውክልና አንፃር ያለባቸዉን ተግዳሮት እና በመሬት ላይ ያለውን ጭቆና እንደገና አጉልቶ አሳይትዋል፡፡

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከል፣ የጾታ እኩልነት እና የሴቶች መብት እንቅስቃሴዎች ምሳሌዎች

The Yellow Movement AAU

The Yellow movement በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች እና በአስተማሪያቸው የተጀመረች ተነሳሽነት ነች። እ.ኤ.አ በ 2011 ዓ.ም ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት እና ሴቶችን የማብቃት ጉዳዮች ላይ ዘላቂ የሆነ ውይይቶችን ለመፍጠር አልማ የተቋቋመች ናት። በብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በተማሪዎች የሚመሩ ክበቦች የተለመዱ ቢሆኑም ይህች ተነሳሽነት በሃገር ውስጥ በአይነቱ ቀዳሚ ናት። ይህች ተነሳሽነት ከ 35 የሚበልጡ ወንዶች እና ሴቶች አባላት እንዲሁም በበይነመረብ እንዲሁም ከበይነመረብ ውጪ ላይ ከቡድኑ ጋር የሚሳተፉ ብዙ በጎፈቃደኞች አሉአት።

Yellow Movement ተማሪዎች በጊቢያቸው፣ በከተማቸው እና በሃገራቸው ውስጥ ሊያዩት የሚፈልጉትን ለውጥ እንዲፈጠር እራሳቸው እርምጃ እንዲወስዱ ታነሳሳለች። Yellow Movement ስለ እድል እና መብት እኩልነት እንዲሁም ሴቶች እና ሴት ልጆች በተሻለ መንገድ የሚታዩበት ሁኔታ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ቋሚ ውይይቶችን እና ዘመቻዎችን ታካሂዳለች። ከሚያካሂዷቸው ዘመቻዎች መካከል #የጷጉሜንቅናቄ አንደኛው ሲሆን በየአመቱ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር በ13ኛው ወር ላይ ይካሄዳል ፣ በየአመቱ ኖቬምበር 25 የሚጀምረው የ#16ቀናትዘመቻ የአለም አቀፍ አመታዊ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን በመቃወም የሚደረገውን የ16 ቀናት ዘመቻን በመቀላቀል የሚደረገው ዘመቻ ይጠቀሳሉ። Yellow Movement በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች (አዲስ አበባ ፣ ሀዋሳ፣ መቐለ) በንቃት ትሰራለች።

ፌስቡክ፡ **https://www.facebook.com/TheYellowMovementAau/?ref=page_internal**
ኢንስታግራም፡ **https://www.instagram.com/theyellowmovementaau/**



ምንጭ፥ The Yellow Movement ፌስቡክ ገጽ፤ #የጷጉሜንቅናቄ እና የአመታዊ አለም አቀፍ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መቃወም የ#16ቀናትዘመቻ

ይኾኖ (Yikono)

ይኾኖ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የሚቃወም እና ለሴቶች እና ለሴት ልጆች መብት እኩልነትን የሚደግፍ በትግራይ ክልል ወስጥ የሚገኝ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ነው። ‘ይኾኖ’ የሚለው ቃል ትርጎሜውም ይብቃ ማለት ነው። ይኾኖ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረው በመቐለ ከተማ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ በመጥራት ነበር። በሰልፉ ላይ ብዙ ሴቶች የሚደርስባቸውን የተለያዩ አይነት ጥቃቶች ለማሳየት ተሳትፈዋል። ይኾኖ ቡድን ከመቐለ ከተማ ነዋሪዎች ጋር ስለሴቶች ጥቃት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለመ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶችንም አዘጋጅተዋል።

ፌስቡክ፥ https://www.facebook.com/GBVYikono/?ref=page_internal

ምንጭ፥ #ይኾኖ ፌስቡክ ገጽ፤ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ተቃውሞ ሰልፍ

ከለላ መመሪያዎች

ከለላ ከህዝብዊ ውይይቶችና ግንዛቤ የተዘነጉ ማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚረዱ የተለያዩ መሳሪያዎችን እና ይዘቶችን የምትሰራ ነፃ የዲጂታል መድረክ ናት። ከለላ የተመሰረተችው በልጆች ፣ ወላጆች ፣ አሳዳጊ ፣ እና አስተማሪዎች መካከል ያለውን የግንኙነት መሰናክሎችን መፍትሄ ለመሻት ያሰበው የ #እኔም (#metoo) አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ በተጀመረበት ወቅት ነበር። ከለላ መድረክ የተመሰረተችው የመገናኛ ብዙሃንና የስረአተ-ጾታ ባለሞያ በሆነችው ሰላም ሙሴ ነበር። የከለላ አንድ አይነት ራእይ በሚጋሩ እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትንና የሴቶች መብት ጉዳዮች መፍትሄ ለማግኘት የሚጥሩ ብዙ በበጎፈቃደኛ ባለሞያዎች ትደገፋለች።

ይህ ተነሳሽነት የተጀመረው ሰላም በግል የፌስቡክ ገጿ ላይ የጓደኞቿን በልጅነታቸው ስለደረሰባቸው የጾታዊ ጥቃት ታሪኮች እና በተለይም በአዋቂነት ህይወታቸው ላይ እንዴት ተፅእኖ እንዳሳደረ ባጋራችበት ወቅት ነበረ። እነዚህን ታሪኮች ተከትሎ ከበርካታ ሴቶች የግል ታሪክ ያዘሉ መልእክቶች በውስጥ መስመር በኩል ለሰላም ደርሰዋታል። እንዲሁም አንዳንዶች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰሚነት እና መረዳት እንደተሰማቸው ይገልጻሉ።

የዚህ ተነሳሽነት ታላቅ ውጤት ከሆኑት መካከል ቤተሰቦችን ፣ አሳዳጊዎችን እና አስተማሪዎች ስለ ህፃናት ጾታዊ ጥቃት እና መከላከያ እንዲሁም እርምጃ መዉሰጃ መንገዶች ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ ግበዓቶችን እና መሳሪያዎችን የሚያቀርበው የከለላ መመሪያ አንዱ ነው። ከለላ መመሪያ በአራት ቋንቋዎች ይገኛሉ፡ በኦሮምኛ ፣ አማርኛ ፣ ትግርኛ እንዲሁም እንግሊዘኛ ፣ አፋርኛ እና ሶማሊኛ በቅርቡ ለአገልሎት ይበቃሉ።

ድረገጽ፡ www.kelela.org
ቴሌግራም፡ https://t.me/kelelaguides
ፌስቡክ፡ https://www.facebook.com/kelelaguides



የኛ፡ "የለውጥ ድምፅ"

የኛ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ በተለያዩ መድረክ ላይ የሬዲዮ ድራማ እና ቶክሾው ፣ የቴሌቪዥን ድራማ ፣ ዲጂታል ቻናሎችን እና ሙዚቃን በመጠቀም እነዚህን ጉዳዮች ለመግታት የሚጥር የ Girl Effect's የወጣቶች ብራንድ ነው። የኛ በታሪኮች እና በሙዚቃ አማካኝነት ተግዳሮቶችን ለመግታት በመጣር ለሴት ልጆች አወንታዊ የባህሪ ለውጥን ያበረታታል።
https://global.girleffect.org/what-we-do/youth-brands/yegna/

ሳይበር - ጥቃት (CYBER-BULLYING) ለመከላከል የወጡ አፍሪካ መንግስታት ህጎች

November 16th, 2019
By Cyril Zenda

እ.ኤ.አ በ 2015 ዓ.ም ናይጀሪያ እና ታንዛኒያ ሳይበር-ጥቃት መፍትሄ ለመፈለግ ህጎችን አፅድቀዋል። ቦትስዋና እና ኡጋንዳ እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም እንዲሁም ኬንያ በ2018 ተከትለዋል። ለዛምቢያ እና ሩዋንዳ እና ሌሎች ሃገራት ህጉ በሂደት ላይ ነው።

ብዙ የአፍሪካ ባህል የሴቶች ድንግልና ላይ አፅንኦት መስጠታቸው የሳይበር ጥቃት እያደገ የመጣ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነት ሲሆን ፣ ሴቶች መሪ የመሆን አቅማቸውን ጨምሮ ለሴቶች አሳሳቢ የሆነ አደጋ እየሆነ ነው።

የአፍሪካ የብዙሃን መገናኛ ፣ የበይነመረብ እና የግንኙነቶች ባለሞያ የሆኑት ኮሊዌ ማጃማ (Koliwe Majama) ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ እንዲሁም እየተለመደ መምጣቱ በይነመረብ መጠቀምን ከስረአተ ጾታ ጉዳዮች ጋር ግንኙነት እንዳለዉ ተናግረዋል።

"የሳይበር-ደህንነት ለመንግስት እና የፋይናንስ/ቢዝነስ ዘርፍ ብቻ የሚተው ሳይሆን ሴቶች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ በሚደረገው ክርክር ውስጥ በቀዳሚነት እንዲሳተፉ የግድ አስፈላጊ ሆኗል፤ እንዲሁም በብሔራዊ እና ክልላዊ አስተዳደር ፎረሞች ጭምር" ብለዋል ማጃማ።

ምንጭ: https://www.fairplanet.org/story/hope-for-african-women-as-more-governments-make-laws-to-fight-cyber-bullying/

ሴፍ ሲስተርስ (SAFE SISTERS) ቀላል መመርያ



https://safesisters.net/

ሴፍ ሲስተርስ ለሴቶች የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ፣ ጋዜጠኞች ወይም የሚዲያ ሠራተኞች እና የማህበረሰብ አንቂዎች የተዘጋጀ በሥራቸው እና በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን የዲጂታል ደህንነት ችግሮች ተረድተው ምላሽ መስጠት እንዲችሉ የሚያሰለጥን የፌሎሺፕ ፕሮግራም ነው፡፡ ራስን በማጥናት ፣ በመሳሪያ ልምምድ ፣ በማማከር ፣ በወርክሾፖች ፣ ለአቻ በማካፈል እና በአነስተኛ ድጎማዎች ጥምረት ተጠቅሞ ሴቶች በበይነመርብ ላይ ደህንነት እንዳይገኙ የሚያግዳቸውን በጣም አንገብጋቢ የዲጂታል ተግዳሮቶችን ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሴት ተሳታፊዎችን ይደግፋል።

ቴክኖሎጂ አሳልፎ አይሰጠንም ብለዉ ሳይጨነቁ የሰብአዊ መብት ተሟጋች መሆን በጣም ከባድ ነው፡፡ ከቫይረሶች ፣ አስፈላጊ ፋይሎችን ማጣት ፣ ስለላ ፣ ጠለፋ ፣ የጥቆማ መልእክት ፣ የመለያ ጠለፋ እና ሌሎች የማይታወቁ የዲጂታል አደጋዎችን ለማስወገድ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉም ሰው ይወስዳል ብሎ መገመት አይቻልም ፡፡ በዛ ላይ ሴት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በተለየ መልኩ የሳይበር ትንኮሳ እና ጥቃት በበይነመረብ ላይ ይደርስባቸዋል፡፡ በምስራቅ አፍሪካ እነዚህን ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ችግሮች ሚገጥሟቸውን ሰዎች ተገቢውን ምክር እና ድጋፍ መስጠት የሚችል በሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ ሚሰሩ የሴት ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ሊግ ያስፈልጋል፡፡ እናም እኛ በሴፍ ሲስተርስ አማክኝነት በትክክል ለመፍጠር ተስፋ የምናደርገው ይህን ነው!

ሴፍ ሲስተርስ ቀላል መመርያ አማርኛ pdf ያውርዱ፡
https://safesisters.net/2020/10/19/safe-sisters-guide-now-in-amharic/

ሴፍ ሲስተርስ (SAFE SISTERS) ቀላል መመርያ ይዘት: ኢንተርኔውስ፣ ሴፍ ሲስተርስ ምስሎች በፖሊሲ፣ Haley Slafer እናመሰግናለን፡፡

የሲቪል ማህበራት ተነሳሽነት ሚና

የሲቪል ማህበራት ዋነኛ ሃላፊነታቸው ባይሆንም እንኳን፡ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር እና ለማበረታታት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። እንቅስቃሴዎቻቸው ከአንድ አይነት ወይም ከተለያየ ሁኔታ የሚመጡ ሰዎች መካከል መደበኛም ሆነ መደበኛ ያልሆነ መስተጋብሮችን እንዲያደርጉ ስለሚያስችል እንዲሁም አድሎን በመከላከል እና የግለሰቦችን ሀሳብን የመግለፅ መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማድረግ ለጥላቻ ንግግር ምላሽ ለመስጠት ዋነኛ መሆን ይችላሉ።

የሃገር ውስጥ ፣በክልላዊ ፣ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የሲቪል ማህበራት ተነሳሽነቶች የጥቃት እና አለመቻቻል አድራጎቶችን ለመቆጣጠር እና ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም የጥላቻ ንግግርን ለመግታት አዳዲስ መንገዶችን ከሚፈጥሩ እና ውጤታማ ከሆኑት መካከል አንዱ ናቸው።

የሲቪል ማህበራት ተነሳሽነቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚነደፉትና ተግባር ላይ የሚውሉት በአድሎ እና ጥቃት በጣም በተጎዱ ግለሰቦችና ማህበረሰብዎች አማካኝነት ነው። አዎንታዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ እና ህዝብን ለማስተማር ፣ የአድሎ ተጽእኖ እና ሁኔታን ለመቆጣጠር የተለዩ እድሎችን ያቀርባሉ። ስለዚህ ሲቪል ማህበራት ስራቸውን እንዲሰሩ የሚያስችልና ደህንነቱ የተጠበቀ ሁኔታን መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች/መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምሳሌዎች ማጣቀሻ

#ጳጉሜ ንቅናቄ ዘመቻ
ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እና እኩልነት ላይ ግንዛቤ የሚሰጥ በYellow movement የተዘጋጀ።
https://www.facebook.com/TheYellowMovementAau

ማሪያም ሰባ የምርት ውጤቶች ፋብሪካ
ማሪያም ሰባ የምርት ውጤቶች ፋብሪካ (MSPF) የተመሰረተው፡ የCNN የ2019 ዓ.ም ጀግና ተብላ የተሰየመችው ፍረወይኒ መብረሃቱ ነው። “በሴቶች የወር አበባ ላይ ላለው ባህላዊ መጥፎ አስተሳሰብ ለመቀየር በሰራችው ስራ እና የትኛዋም ሴት ልጅ በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት አትቀርም የሚለው የፍረወይኒ እምነት በአለም ደረጃ በትልቅ ሁኔታ እያስተጋባ ነው።” በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛዎቹ ሴቶች እና ሴት ልጆች የንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን ስለማያገኙ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ለሴቶች እና ሴት ልጆች በድጋሚ መጠቀም የሚያስችል የንፅህና መጠበቂያ ሞዴስ በማምረት ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት የተቋቋመ ድርጅት ነው።
http://mariamseba.com/#about-us

ከለላ መመሪያዎች
ከለላ ከህዝባዊ ውይይቶችና ግንዛቤ የተዘነጉ ማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚረዱ የተለያዩ መሳሪያዎችንና ይዘቶችን የምትሰራ ነፃ የዲጂታል መድረክ ናት።
ድህረገጽ፡ www.kelela.org
ቴሌግራም፡ https://t.me/kelelaguides

5

ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ

05 ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ

ይዘቶች

የሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ ምሳሌዎች

ሰላማዊ ቴክ (PEACETECH) **ምሳሌዎች**

#ዊኪፒዲያለሰላም (#WIKIPEDIA4PEACE)

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 5

ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ

የሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ ምሳሌዎች

#ቴክኖሎጂለሰላም #TECH4PEACE

#የሰላምቴክ (#PeaceTech) #ቴክኖሎጂለሰላም (#Tech4Peace) ሰዎች እና ማህበረሰብ ቴክኖሎጂን ግጭትን ለማነሳሳት እንደመሳሪያነት ከመጠቀም ይልቅ በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ሲጠቀሙት ለማመላከት የምንጠቀማቸው ቃላቶች እና ታጎች ናቸዉ፡፡

“የሰላም ቴክ” መነሻ ነጥብ ቴክኖሎጂ በባህሪው ጥሩም መጥፎም ፣ ሃያልም ደካማም አይደለም ፤ ቴክኖሎጂን እቅድ አውጥቶ ለመልካም ወይም ለመጥፎ ለመጠቀም እንዲሁም ወዴት እንደሚመራን ተፅእኖ ለማድረግ ስልጣን ያለው የሰዎች ውሳኔ ነው የሚል ነው።”
Berns, J. A Forum for Peace and Security in the 21st century: Build Peace Forum, March 2015.
http://buildingpeaceforum.com/site/wp-content/uploads/2015/04/PeaceTech.pdf

#ሰላምሀክካምፕ #PeaceHackCamp

የመጀመሪያው የ#ሰላምሀክካምፕ **(#PeaceHackCamp)** የተካሄደው እ.ኤ.አ በ2015 ዓ.ም በደቡብ ሱዳን ጁባ ውስጥ ሲሆን ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሰዎች እርምጃ እንዲወስዱ እና ሰላምን ለመፍጠር የሚያደርጎቸዉን የራሳቸውን ዘዴዎችን እንዲያከብሩ እንደ ነፃ እና ሕዝባዊ ክንዋኔ ሆኖ ተካሂዷል።

ሀክ ወይም ሀከር የሚለው ቃላት ፍቺ፡ ለማንኛውም አይነት ችግሮች አዲስ እና ፈጠራ የታከለበት ቀላል መፍትሄዎችን መፈለግ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሰላም በማይገኝበት ለሰላም መፍትሄ በመፈለግ የ#ሰላምሀክካምፕ **(#PeaceHackCamp)** የተለያዩ ማህበረሰቦች ለማሰባሰብ እና ሰላም ግንባታ ላይ በግልፅ ሃሳብ ለማመንጨት በር ይከፍታል እንዲሁም ይሄንን ከበይነመረብ እና ገሃዱ አለም ላይ ካሉ እንቅስቃሴዎች ጋር ያገናኛል።

የ#ሰላምሀክካምፕ**(#PeaceHackCamp)** ፅንሰ ሃሳብ ከደቡብ ሱዳን በኋላ ወደ ደቡብ አሜሪካ እና እሲያ እንዲሁም ወደ ሌሎች የአፍሪካ ክፍሎች ተስፋፍቷል። ከአፍሪካ ሌሎች ክፍሎችና በአለም አቀፍ ደረጃ ከአቻዎች ጋር ትስስር ለመፍጠር ወጣት ስራ ፈጣሪዎች ፣ ሰላም ገንቢዎች ፣ የቴክኖሎጂ እና የነፃ ባህል ደጋፊዎች ለሰላም ሀክ ፣ ኮድ ለማድረግ እና ለመተበበር መሰባሰብ ይችላሉ።

የ**#ሰላምሀክካምፕ (#PeaceHackCamp)** እናድርግ - ለኢትዮጵያ ህዝቦች ልዩ እድል!

ሃይራክ ቦክስ (HyracBox) ‘ለለዉጥ ሆት ስፖት’

የ ሃይራክ ቦክስ (HyracBox) የበይነመረብ አቅርቦት ለማግኘት አስቸጋሪ በሆነባቸው የገጠር ወይም ከበይነመረብ ስርጭት ውጪ ያሉ አካባቢዎች ላይ አሰልጣኞችና አስተባባሪዎች የሚጠቀሙት በራስፕቤሪ ፓይ (RaspberryPi) የሚሰራ ትንሽ ተንቀሳቃሽ ሰርቨር ነው። በሃይራክ ቦክስ ተጠቃሚዎች ሙሉ የ#defyhatenow ጠቅላላ ማቴርያል፣ የመስክ መመሪያ ይዘቶችን ፣ በተጨማሪም በርካታ ነፃ የማስተማሪያ ግበዓቶች ፣ ድረገፆች እና የተወሰኑ ስልጠና ክፍሎችን በማንኛውንም የተንቀሳቃሽ መሳሪያ መደበኛ ዋይፋይ በመጠቀም ማግኘት ይችላሉ።

አብዛኛውን ጊዜ በገጠራማ አካባቢዎች የበይነመረብ መዘጋት ፣ ሙያዊ መሰረተ ልማት ፣ የመረጃ ስርጭት እና አቅርቦት በይበልጥ ተግዳሮቶች እንደመሆናቸው ሃይራክ ቦክስ ኮምፒዉተር እና የሚድያ ግንዛቤ ክህሎቶችን ለማጎልበት ምቹ የሆኑ እድሎችን ያቀርባል። የ ሃይራክ ቦክስ አሰልጣኞች ማህበረሰባቸውን በመረጃ አማራጮች እና እድሎች ላይ ግንዛቤ እንዲሰጡ ያስችላል። የፕሮጀክት አስተባባሪዎች እና አጋሮች አዲስ መረጃ ሊጭኑ የሚችሉበት ፣ ቪዲዮዎች እና ሌሎች በነፃ በበይነመረብ ላይ የሚገኙ ሚዲያዎች ይህንን ጠቃሚ ይዘት በነፃ እንዲያጋሩበት የሚያስችል “ለለዉጥ ሆት ስፖት” (“Hotspot for Change”) ነው ፣ በተጨማሪም ተንቀሳቃሽ ስለሆነ የትኛውም ቦታ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ምሳሌ፥ የደቡብ ሱዳን ታሪክ እና የሃይራክ ቦክስ
https://medium.com/@hyractech/power-of-one-the-story-of-south-sudan-and-the-hyracbox-39978c6c3374

ሃይራክ ቦክስ (HyracBox)
https://www.hyracbox.com/

የሰላም ቴክ (PEACETECH) ምሳሌዎች

የዜጎች የማስረጃ ላብ ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል (Amnesty International)

"የዜጎች ማስረጃ"፡ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ሊያሳዩ የሚችሉ ምስሎችን ፣ ቪዲዮዎችን ፣ የሳተላይት ምስሎች ፣ ሰፊ የመረጃ ስብስብቦች እንዲሁም ሌሎች ማቴርያሎች በሰብዓዊ መብት መርማሪ ባለሥልጣን ያልሆኑ ግለሰቦች የተሰበሰቡ ማስረጃ ሰነዶች ናቸው።

እንደ ትዊተር ፣ ፌስቡክ እና ዩትዩብ ያሉ የማህበራዊ ሚዲያ ኔትወርክ ላይ በተደጋጋሚ የሚጋሩ እነዚህን የመሰሉ ሰነዶች በአብዛኛው ባለማስተዋል ሊታለፉ ይችሉ የነበሩ ወንጀሎችን በዝርዝር ያጋልጣሉ። የዜጎችን ማስረጃ ለመሰብሰብ የሚውል ቴክኖሎጂ እና አቅርቦት ዘወትር እየተሻሻለ ቢሆንም የተዛባ መረጃን ለማረጋገጥ ብዙ የመረጃ ምንጮች ወይም መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ።

https://www.amnesty.org/en/latest/news/2019/12/amnesty-international-updates-citizen-evidence-lab-for-cutting-edge-open-source-human-rights-investigations/

ኢንተርኒዉስ

በመላው አለም ላይ የሚገኙ ሰዎችን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ ፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ እንዲሳተፉ እና ስልጣንን ተጠያቂ እንዲያደርጉ የሚያስችል ተአማኒ ፣ ጥራት የለው ዜና እና መረጃ እንዲያገኙ የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመ አለም አቀፋዊ ድርጅት ነው። የኢንተርኒዉስ ስራዎች ሰዎች ጥሩ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ በማረጋገጥ የተዛባ መረጃዎችን በተለየዩ ግንባሮች ይከላከላል። በመላው አለም በሺዎች የሚቆጠሩ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ፣ ጋዜጣዎችን ፣ ተንቀሳቃሽ የዜና ኔትወርክ እና የበይነመረብ የዜና ድረገፆችን የሚያጠቃልሉ የሚድያ አዉታሮች እንዲለሙ ከሃገር ውስጥ አጋሮች ጋር በመሆን ድጋፍ አድርጓል።
https://internews.org/

ሴንቲኔል ፕሮጀክት፡ የጥላቻቃት (Hatebase)

የጥላቻቃት በብዙ ቋንቋዎች የተዋቀረ እና አጠቃቀም ላይ የተመሰረተ የአለም ትልቁ የጥላቻ ንግግር የበይነመረብ ማከማቻ ነው። ተመራማሪዎች የጅምላ ጭፍጨፋን በቅድሚያ ለይቶ ለማወቅ ሊጠቀሙት የሚችሉት የቃላት እና ሃረጎች ማከማቻ ለመስራት የተደረገ ሙከራ ነው።

የጥላቻቋት ሁለት ነገሮችን ያቀርባል ተጠቃሚዎች አካባቢን የሚመለከቱ እይታዎችን እንዲመዘግቡ የሚያስችል ዊኪፒዲያ መሰል ድረገጽ እና የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመከላከል የጥላቻቋት መረጃን ከሌሎች መሳሪያዎች ጋር ለማጣመር የሚያስችል ኤፒአይ(API) ነው፡፡
https://thesentinelproject.org/projects

ፒስ ቴክ ላብ (PeaceTech Lab)

ፒስ ቴክ ላብ (PeaceTech Lab) ቴክኖሎጂን ፣ ሚዲያዎችን እና መረጃዎችን በመጠቀም ግጭትን ለመቀነስ እና የሰላም ግንባታ ጥረቶችን ለማፋጠን እና ለማሳደግ ይሰራል፡፡ PeaceTech Lab በምስራቅ አፍሪካ በሚዲያ አመፅ ማነሳሳትን ለመገደብ የሚረዱ መሣሪያዎችን አዘጋጅቷል። እንዲሁም ከ#defyhatenow ጋር በመተባበር የጥላቻ ንግግሮችን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል ሪፖርቶችን እና የፒስ ቴክ ላብ (PeaceTech Lab) ማህበራዊ ሚዲያ እና ግጭት በደቡብ ሱዳን ውስጥ የጥላቻ ንግግሮች መዝገበ ቃላትን ጨምሮ አዘጋጅቶአል ፡፡
http://www.peacetechlab.org

ዋያማ ቀድሞ ማስጠንቀቅያ ሶፍትዌር

ዋያማ ቀድሞ ማስጠንቀቅያ ሶፍትዌር (ናይጄርያ) ለአካባቢዉ ማህበረሰቦች በሰው ደህንነት ላይ አሁን ባሉ ወይም በሚከሰቱ ስጋቶች ላይ ቁጥራዊ እና ጥራት ያለው መረጃን በስርዓት ለመሰብሰብ ፣ ለመተንተን እና ለማስተላለፍ ከርቀት በሚቆጣጠሯቸዉ ሰርቨሮች አማካኝነት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ፡፡ ዋያማ ለጥቃቅን ደረጃ ወይም ለማህበረሰብ ተኮር የቅድመ ማስጠንቀቂያ የታሰበ ሲሆን ዓላማው አመፅን ለመከላከል የተሳካ የቅድሚያ ምላሽን ማጎልበት ነው፡፡
http://www.earlywarningnigeria.org/

#ዊኪፒዲያለሰላም (#WIKIPEDIA4PEACE)

ዊኪፒዲያ ለምን?

#defyhatenow ተነሳሽነት ተማሪዎችን ለአለማችን የበይነመረብ አለም አቀፋዊ ኢንሳይክሎፔዲያ ለሆነው ዊኪፒዲያ ላይ እራሳቸው አስፈላጊ ነው የሚሉት ርዕስ ላይ መረጃዎችን መፃፍና አርትኦት ላይ አሰልጥኗል። ዊኪፒዲያ ላይ ብዙ ክልሎች እና ርዕሶች አሁን በበቂ ሁኔታ አልተወከሉም። ስለ ዋነኛ ከተሞች፣ ክልሎች እና ገጽታዎች እንኳን የተመዘገቡት የተወሰኑ መስመሮችን ብቻ ይይዛሉ። ዊኪፒዲያ በአብዛኛው ጥቅም ላይ ከሚውሉ እና ከሚጎበኙ ድረገፆች መካከል አንደኛው ነው። ስለ ኢትዮጵያ የተፃፉ አብዛኛው ፅሁፎች የተዘጋጁት በሌላ ሃገር ዜጎች ነው። የተለያየ አስተስሰብ ያላቸው ቡድኖችን ጋር በአንድነት ለመስራት ፣ ፅሁፍ እና የምርምር ክህሎቶችን ለማጠናከር እና ድምፆን በበይነመረብ ላይ ለማሰማት ሰላም እና ጠቃሚ የግል ክህሎቶችን የሚያጠናክሩ ሃያል መንገዶች ናቸው።

ምንጭ: Hakim George, Wikipedia for Peace, University of Bahr el-Ghazal, Wau, South Sudan, 2017

#ዊኪፒዲያለሰላም ከደቡብ ሱዳን የተገኘ ምሳሌ ፥ የዉንሊት የሰላም ኮንፈረንስ

https://en.wikipedia.org/wiki/Wunlit_Peace_Conference

#Wiki4Refugees Editathon Example from Uganda: Mapping Refugee Settlements

ኡጋንዳ ውስጥ ከሚገኙ የስደተኛ መጠለያዎች የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሰባሰብ በዊኪፔዲያ ላይ ስለ ስደተኛ መጠለያዎች ያለ መረጃን ለማጎልበት እና በአጠቃላይ ለማሻሻል ያለመ የትብብር የበይነመረብ እንቅስቃሴ ።

https://outreachdashboard.wmflabs.org/courses/Wikimedia_Community_User_Group_Uganda/Wiki4Refugees_Uganda_Editathon_(September_2020)

6

ማንነት እና አውድ

06 ማንነት እና አውድ

ይዘቶች

በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት ሚና

ጥያቄዎች ለቡድን ውይይት

የጥላቻ ፒራሚድ

#DEFYHATENOW | **ምዕራፍ** 6

ማንነት እና አውድ

በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት ሚና

በተለያዩ ቡድኖች መካከል በተለይ የተለያየ ሃይማኖት እና እምነት ባላቸው ማህበረሰቦች መካከል የሚደረግ ቀጣይነት ያለው እና ውጤታማ ውይይት በቡድኖች መካከል ያሉ ውጥረቶችን ወይም ጥርጣሬ በመቀነስ እንደ ውጤታማ የመከላከያ እርምጃ ሊያገለግል ይችላል።

በቡድን መካከል ትርጉም ያለው ግንኙነት አለመኖር፣ ማግለል እና ለሌሎች ባህል ፍላጎት አለመኖር ብዙውን ጊዜ በቡድን መካከል ለሚከሰቱ አለመግባባቶች እንዲሁም "የጥላቻ ንግግር" በጣም የተስፋፋበት ፣ ዓመፅ ፣ ጠላትነት ፣ ወይም አድልዎ የመፍጠር ዕድሉ የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ በተለይ ሊከሰት የሚችለው

- በቡድኖች መካከል ያሉ ውጥረቶች ወደ አመፅ የተቀየሩበት ታሪክ ካለ፡ ወይም፤
- ትክክለኛ የጥቃት እና አድሎ አጋጣሚዎች።

ውጤትማ ለመሆን

- ውይይቶች እውነተኛ የአስተሳሰብ ልውውጥ ሊኖራቸው ይገባል።
- ልዩነቶችን እና አለመስማማቶች ላይ ውይይቶችን እንዲደረጉ ማስቻል።
- ውይይቶች አካታች መሆን አለባቸዉ። ማህበረሰብ ከ'ባህላዊ' መሪዎች ባለፈ እንዲወከሉ መፍቀድ በተለይም የሴቶች ፣ የሴት ልጆች ፣ የወጣቶች እና የተፈናቀሉ/ አነሳ ማህበረሰብ ድምጾችን ወደ ፊትለፊት በማምጣት አካታች ሊሆኑ ይገባል።

ውይይቶች መደበኛ ያልሆኑ ልውውጦችን በማህበረሰቦች መካከል እንዲካሄዱ የሚያስችሉና አካታች መሆን ይገባቸዋል። ለምሳሌ በስፖርት ወይም ባህላዊ ልውውጦችን አውድ ወይም የጋራ የሚያሳሳቡ ተግባራዊ ጉዳዮችን መፍትሄ ለመፈለግ መተማመንና ትስስርን ለመገንባት ጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላል። በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት እና ግንኙነት ተነሳሽነቶች ከመንግስት እና ፖሊሲ ከሚቀርፁ እና ሃይማኖታዊ መሪዎች ህዝባዊ ድጋፍን ሲያገኙ ተፅእኖ ማሳደግ ይቻላል፡፡

ከመደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ "ውይይቶች" አውድ ውጭ ፣ የተለያዩ ማህበረሰቦች ተወካይ ፣ በተለይም የሃይማኖት መሪዎች እና ሌሎች የህብረተሰብ መሪዎች አለመቻቻል እና አድሎአዊነት ላይ እንዲናገሩ ብቁ ማድረግ ይገባል ፡፡ ይህ በተለይ የአለመቻቻል እና የመድልዎ ደጋፊዎች እራሳቸውን እንደ የተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ተወካይ አድርገው ወይም የተወሰኑ ማህበረሰቦችን ወክለው በሚንቀሳቀሱበት ግዜ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የሃይማኖት እና የማህበረሰብ መሪዎች እነዚህን የይገባኛል ጥያቄ ለማስተባበል ብቻ ሳይሆን ፣ በግለሰቦቹ አቋም ላይ ለመሳተፍ እና ለመሞገት እንዲሁም አሳማኝ አጸፋዊ ምላሽ ለመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

ግንዛቤ ስለ ቅድመ-ፍረጃ

በዓለም ዙሪያ ያሉ ማህበረሰብዎች የተለያዩ ጎሳዎች ፣ ሃይማኖት ወይም ብሄር ቡድኖች ያሏቸው ሀገሮችን ያቀፉ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ቡድኖች አንድ ላይ ለመኖር የማይጣጣሙ ይመስላቸዋል፡፡ ይህም በታሪካዊ ፣ በቅኝ ግዛት ወይም በቅርብ ጊዜ ክስተቶች ምክንያት ሊሆን ይችላል ፡፡ ይህ ግጭት ወደ ሚያስከትል ውጥረት ሊያመራ ይችላል፡፡

ማንነቶች ዉስብስብ እንደሆኑ ሁሉ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን መፍታት ከባድ ነዉ፡፡ በማህበረሰባችን ዉስጥ የበላይ በሆኑ ቡድኖች ኢላማ ሚደረጉ ማንነቶቻችንን እናዉቃቸዋለን፡፡ ስለሆነም በተወሰነ ደረጃ በማንነት የማንገናኛቸዉ ቡድኖች ላይ ቅደመ-ፍረጃ ይኖረናል አድልዎም እናደርጋለን፡፡ ማንነቶች የማይለዋወጡ አይደሉም በየቀኑ ምንደራደራቸዉ ነገሮች ናቸዉ፡፡

እንደ አንድ ቡድን አባል ማንነታችን የበላይ ከሆኑ ቡድን አባላት ከሆኑ ግለሰቦች ጋር ባለን መስተጋብር በግለሰብ ደረጃ ማንነታችን ጥያቄ ዉስጥ ሊገባ ይችላል ፣ ልክ እኛ የምንገኝበት ቡድን በሀገር እና አለም አቀፍ ደረጃ አደጋ ሊያጋጥመዉ እንደሚችል፡፡

ስለ ማንነት መማር እና ስለ ቅድመ-ፍረጃዎች ግንዛቤ ሚያስፈልገን ልዩነቶቻችንን እና ግጭቶችን ለመቆጣጠር እንድንችል ነዉ፡፡ የራስዎን ማንነት በመገንዘብ ፣ ይህ ማንነት ለእርስዎ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት እና የሌሎችን ማንነት እንዴት መቀበል እንዳለብዎት መማር ግጭትን ለመከላከል እና በተከሰተ ግዜም ለመቆጣጠር ከሚረዱ አስፈላጊ ክፍሎች አንዱ ነዉ፡፡

ቅድመ - ፍረጃን በተመለከተ አጠቃላይ ግምቶች (Cotton, 1993)

- ቅደመ-ፍረጃ የተማርነው ነው እንዲሁም ልንተወዉ ምንችለዉ ነገር ነዉ፡፡
- ቅደመ-ፍረጃን ለመፍታት ውጤታማ የሆነው ስነ ዘዴ በራስ ላይ ማተኮር ነው ፣ ከዚያም በቡድኖች መካከል ያሉ መመሳሰሎችን እና ልዩነቶችን መመርመር ነው።
- ስለራሳቸው ጥሩ ስሜት ያላቸው ሰዎች ሌሎችን ማዋረድ/ስም ማጥፋት አያስፈልጋቸውም።
- እውነታዎች ብቻ ወደ የተሻሉ የቡድን ግንኙነቶች አይወስዱም። ይህ የትብብር ትምህርትና ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ ያተኮረ ትምህርትን ይፈልጋል።

?

ሊታሰብባቸው ሚገቡ ጥያቄዎች

እኔ ማን ነኝ?

እራስዎን እንዴት ይለያሉ?

እኛ ማን ነን?

- ባህላዊ አመጣጠን እና አስተዳደጎን እንዴት ይገልፁታል?
- እራሶን እንዴት ይለያሉ/ይገልፃሉ (እድሜ ፣ ጎሳ ፣ ዘር ፣ ፖለቲካ ፣ ሃይማኖት ፣ ጾታ)?
- ለቤተሰቦ እና ለማህበረሰብ ቡድኖ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው እሴቶች እና ባህሎች ምን ነበሩ?
- እራስን ከአንድ የተወሰነ ቡድን አባል ማድረግ ምን ጥቅሞች እና ተግዳሮቶች አሉት?
- ከአካባቢ ፣ ከሁኔታዎች እና ልምዶች ጋር በተይያዘ የማንነቶን ዋና ዋና ገፅታዎች ይመርምሩ።
- የማንነት ድርርቦች ፡ ሰፊ እይታ ከግል እይታ ጋር ሲነፃፀር።
- የጋራ/ጎሳ/የፖለቲካ/የሃይማኖት/የሞያዊ ማንነት - በተለያዩ መስመሮች እየደበዘዙ ሄደዋል።

የጥላቻ ፒራሚድ

ፒራሚድ ከታች ወደ ላይ ውስብስብነቱ እያደገ የሚሄድ አድሎአዊ ባህሪዎችን ያሳያል። ምንም እንኳን በየደረጃው ያሉ ባህሪዎች ግለሰቦችን እና ቡድኖችን በአሉታዊ ሁኔታ ተፅእኖ የሚያደርጉ ቢሆኑም አንድ ሰው ፒራሚዱ ወደ ላይ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ባህሪያቱ በይበልጥ አስጊ የሆኑ መዘዞች አሉት። እንደ ፒራሚድ የከፍተኛው ደረጃዎች ከዝቅተኛ ደረጃዎች ድጋፍ ያሚያገኙ ናቸው። ሰዎች ወይም ተቋማት በዝቅተኛ ደረጃዎች ላይ ያሉትን ባህሪያትን ተቀባይነት ሲኖራቸው ወይም “መደበኛ” አድርገው የሚቆጥሩ ከሆነ በሚቀጥለው ደረጃ ያሉ ባህሪዎች የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። ለዘር ማጥፋት ጥላቻ ከየት አንደመጣ ለሚጠይቁ የዓለም ማህበረሰብ ምላሽ ለመስጠት፤ የጥላቻ ፒራሚድ የዘር ማጥፋት ጥላቻ የተገነባው በፒራሚድ ዝቅተኛ ደረጃዎች ውስጥ የተገለፁ ባህሪዎችን በመቀበል መሆኑን ያሳያል።



የጥላቻ ንግግር ፒራሚድ

ምንጭ፡ CARD (የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል) የፀረ-ጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች መመሪያ

7

ጥበብ ለሰላም፤
#አርቲቪዝም
#Artivism

07 ጥበብ ለሰላም፡ #አርትቪዝም (#ARTIVISM)

ይዘቶች

ጥያቄዎች ለቡድን ውይይት

ስትራቴጂዎች ለባህላዊ ሰላም ግንባታ

#DEFYHATENOW **የማህበራዊ ሚድያ** #PEACEJAM

#DEFYHATENOW **የጥላቻ ንግግርን በጥበብ መዋጋት**

መነባነብ / ግጥም

ጥበብ እና ማህበራዊ ለዉጥ

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 7

ጥበብ ለሰላም፡ #አርትቪዝም (#ARTIVISM)

?

ሊታሰብባቸዉ ሚገቡ ጥያቄዎች

ባህል ሰላም ግንባታ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያደርጋል?

ጥበብ ለዘላቂ ሰላም ምን አስተዋፆ ሊኖረው ይችላል?

#አርቲቪዝም ለህብረተሰቡ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

- ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ለሰላም ግንባታ እንዴት አስተዋፆ ያደርጋሉ?
- የእነዚህ እቅስቃሴዎች የጋራ ነገሮች ምንድን ናቸዉ?
- ከእርስዎ የሰላም አረዳድ ጋር እንዴት ይገናኛሉ?
- ሰላም ግንባታን አዉን ማድረግ ላይ ስኬታማ ናቸዉ?
- ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን እና ሰላም ግንባታን ለማገናኘት ሀሳቦን ያስቀምጡ?

ስትራቴጂዎች ለባህላዊ ሰላም ግንባታ

በሰላም ግንባታ ፅንሰ-ሀሳብ መሰረታዊ የማህበረሰብ እርምጃዎች ዙሪያ በ#defyhatenow የተሰሩ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው:: እነዚህ ለሰላም ግንባታ የራስዎን የፈጠራ ዘዴ ለመመስረት የበለጠ ተነሳሽነት በመፍጠር ተዘርዝረዋል:: ይገልብጡአቸዉ፣ ይቀላቅሉአቸዉ ወይም ያጋርዋቸዉ ወይም ራስዎን እንቅስቃሴ ይፍጠሩ!

ማህበራዊ ሚድያ #PeaceJam

#PeaceJam ማህበረሰብ አቀፍ የሰላም ግንባታ ሁነት፣ ሂደት ወይም እንቅስቃሴ ነዉ:: ሰዎች በተለይ ወጣቶች፣ የባህል ተፅእኖ ፈጣሪዎች ሰላም እና ባህላዊ ዉይይቶች ላይ ፍላጎት ያላቸዉ ሰዎች ስለወደፊት ያላቸዉን ሃሳብ፣ ራዕይ፣ ተስፋ ይጋራሉ:: ሙዚቀኞች አዲስ ሙዚቃ ለመፍጠር ለልምምድ እንደሚገናኙ #PeaceJam በበይነመርብ ላይ ለሰላም ይገናኛሉ:: ስለዚህ #PeaceJam በተሰማሙባቸዉ ወይም አንድ አባል በጠቆመዉ መሰረት ዉዝዋዜ፣ ቲያትር፣ ሙዚቃ ወይም የተለያዩ የትብብር እርምጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: በበይነመርብ ብዙ ተሳታፊዎችን አንድ ላይ ከማሰባሰብ እንዲሁም የሰላም እና የትብብር መልክቶችን እንዲያስተላልፉ ከማነሳሳት በስተቀር ሌላ ህጎች የሉትም::

#DEFYHATENOW ማህበራዊ ሚድያ #PeaceJam እንዴት መስራት ይቻላል?

ማንኛዉም ሰዉ የራሱን #PeaceJam ዝግጅት በማዘጋጀት ወይም የራሱን የሰላም መልዕክት በበይነመረብ በማጋራት መጀመር ይችላል፡፡

ሰፋ ያለ ታዳሚዎችን ለመድረስ እና በመልዕክትዎ ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ለማሳደር የእርስዎን #PeaceJam ከማንኛውም ዓይነት ዓለም አቀፍ የሰላም ዝግጅት ጋር ያገናኙ፡፡ ለምሳሌ፡ የተባበሩት መንግስታት የአለም የሰላም ቀን መስከረም 21፣ የአለም የፕሬስ ነፃነት ቀን ግንቦት 3፣ አለምአቀፍ የሴቶች ቀን መጋቢት 8፡፡

ስለ ማህበራዊ ሚዲያ የሰላም ገጽታ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት የበይነመርብ ሰርጦችን ለአዎንታዊ ባህላዊ ለውጥ መጠቀም ክትትልን ለማገዝ የማህበራዊ ሚድያ ልጥፎች ላይ #PeaceJam #Act4Peace እና #defyhatenow ሀሽታጎችን ይጠቀሙ፡፡

የማህበራዊ ሚድያ ሀይልን ሰላምን በይነመረብ እና በገሀዱ አለም ለማስተዋወቅ በ#PeaceJam ይጠቀሙ፡፡

በኢትዮጵያ እና በዓለም ዙሪያ ያሉ ጓደኞችዎን እና ማህበረሰብዎን የሰላም አምባሳደር እንዲሆኑ ወደ #defyhatenow ፣ #PeaceJam በፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ብሎግ፣ ኢንስታግራም፣ ዋትስአፕ፣ #Peacejam ይጋብዙ፡፡

+

#DEFYHATENOW የጥላቻ ንግግርን በጥበብ መዋጋት

#ሰላምለሁሉም (#Peace4ALL) የሙዚቃ ቪድዮ

#defyhatenow #ሰላምለሁሉም (#Peace4ALL) ሙዚቃ ቪድዮ ራይኖ ካምፕ ኡጋንዳ 2017

#የሰላምመንደር (#PeaceVillage) የበይነመረብ እና በገሀዱ አለም ጥላቻ ንግግሮችን በመቃወም ለሰዎች አዎንታዊ እና ትምህርታዊ መልዕክቶችን ለመላክ ሙዚቃን ይጠቀማል፡፡ የሙዚቃ ፕሮግራሙ የተቀረፀዉ ቅደመ-ፍረጃን በደቡብ ሱዳን ለመስበር እና የእርቅ ባህልን ለማዳበር ነዉ፡፡ #ሰላምለሁሉም(#Peace4ALL) ቪዲዮ የተቀዳዉ ሉሩጃ ፣ ቴሬጎ (ሪይኖ ካምፕ) ነዉ፡፡ ዋና ዋና ዘፋኞቹ ሼሪይ ዛኒያ (ኦሮራ) ፣ ሮናልድ ሉአቴ (ሮኒ ሪድዲምዝ) እና አዳምስ ማንዴላ (ፍሪቦይ) ናቸው) በቤንችማርክ ፊልሞች ሞንታዥ ተቀረፀ (P4A የካሜራ ቀረፃዎች በ ያስ አልማን ፣ ዳይሬክቲንግ እና ኤዲቲንግ በ AB soft፡፡
https://youtu.be/DxZ-r2tM5-Y

#ከመጫንዎበፊትያስቡ (#ThinkB4UClick) ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ሲሆን አላማዉም የተሳሳቱ መረጃዎች፣ ሀሰተኛ ዜናዎች እና የጥላቻ ንግግሮችን አደገኛነት በደቡብ ሱዳን ሁኔታ ለማሳየት ነዉ፡፡ ዘመቻዉ ከህዝብ ጋር የጥላቻ ንግግር መዘዝን እና እንዴት በግልሰብ ደረጃ በሚወሰዱ እርምጃዎች ሊስተካከል እንደሚችል ዉይይት በማድረግ በይነመረብ እና በገሀዱ አለም ለዜጎች የእርስ በእርስ ግንኙነት እና ፍሬያማ እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ዉይይት ደህንነት ያላቸዉ ስፍራዎች ማድረግን አላማ ያደረገ ነዉ፡፡ አርቲስት : በፍሪቦይ እና ሼሪይ ዛኒያ፣ ግጥም : በፍሪቦይ አዳምስ ፣ ፕሮዱይሰር : በቤንችማርክ ፊልሞች፡ አሩዋ ፣ ኡጋንዳ፡፡

Artist : Free-Boy and Sherry Zania Lyrics : Free-Boy Adams
Producer : Benchmark Films, Arua, Uganda

#ከመጫንዎበፊትያስቡ #ThinkB4UClick ቪዲዮ
https://youtu.be/UMz6s_m0q_I

DEFY! ፊልም

DEFY!(ዲፋይ) አንጋፋ ፖለቲከኛ ክቡር ዴቪስ ለማህበራዊ ድረ ገፅ የተፈጠረባቸዉን አዲስ እምቅ ፍላጎት እና ማህበራዊ ድረ ገፅን ፕሮፖጋንዳ እና አሉባልታ ለማሰራጨት መጠቀም ያለዉን አደጋ የሚተርክ ልቦለድ ነዉ፡፡

ተዋንያን ሲልያኖ ዮክዌ፣ ዶከር ስቴፈን፣ ዊኒ ጆሴፍ፣ ኒኮሊ ማርያም
ፕሮዱይሰር ኤስኬፒ ሳዉዝ ሱዳን፣ ቢልፓም ስቱዲዮ ከ r0g_agency ጋር
ዳይሬክተር ኢግልይ ሀኪም ኢግልይ
ፀሀፊ ሳም ሉኩዱ
https://youtu.be/vpvslQTHBSI

መነባነብ / ግጥም

የጥላ ትእይንት በገርልስፎርአርት (Girls4Art)

https://youtu.be/XdfUbMdJPeM

መነባነብ by Lena Coco Kovats

እየጮህሽም ቢሆን
ወይ እየተንሾካሸክሽ
በፍረሀት ክንድሽን እንቀሳቅሰሽ
ወይም መታየት ሳትፈልጊ
የሚነገር ታሪክ አለሽ

በንግግር ወይ በግጥም
በተለይ አሁን

መልመጃ ምሳሌ የራስን 'ኢለቨኒ' (Elevenie) እንዴት መስራት ይቻላል by Lena Coco Kovats

በ 5 መስመሮች ላይ ባለ አስራ አንድ ቃል ግጥም ይፍጠሩ

- ☐ ማንኛዉመ ርዕስ ሊሆን ይችላል፡፡
- ☐ በመጀምርያዉ መስመር ላይ 1 ቃል፣ በሁለተኛዉ መስመር ላይ 2 ቃል፣ በሶስተኛዉ መስመር ላይ 3 ቃል፣ በአራተኛዉ መስምር ላይ 4 ቃል በአምስተኛዉ መስመር ላይ 1 ቃል ተጠቀሙ፡፡
- ☐ ከዛም ለአድማጮቻችሁ አንብቡላቸዉ፡፡

ምሳሌ - የዓለም ፍልስፍና ቀን 2019 ፣ ቡዌ ካሜሩን

የጥላ ተእይንት በገርልስፎርአርት (Girls4Art) በመነባነብ ዝግጅት ከካሜሮናዊዉ አርቲስት ማክ አሉንግ በሩብ አመት ሀገራዊ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪዎች መድረክ ለመነባነብ ጥበብ መገለጫ እና ሌሎች የፈጠራ የመድክ ላይ ተእይንቶች ጥበባት

https://www.sysyhouseoffame.org/
https://strawacademy.org/
https://www.macalunge.com/

ጥበብ እና ማህበራዊ ለዉጥ

#አናታባን (#AnaTaban)
በደቡብ ሱዳን ወጣት ፈጣሪዎች “የደከሙ” ደቡብ ሱዳናዉያንን ለመደገፍ የተጀመረ ዘመቻ እና እንቅስቃሴ፡፡
https://www.facebook.com/AnatabanSouthSudan/

በሚከተሉት እሴቶች መሰረት ለሁሉም ክፍት ነዉ

አንድነት
አናታባን ከእህቶቻችን እና ወንድሞቻችን ጋር እንቆማል በተለይም ተጋላጭ እና ተጎጂ ለሆኑ፡፡

ድፍረት
አናታባን ኢፍተሀዊነት በማጋለጥ እናምናለን፡፡

ታማኝነት
አናታባን ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን እናበረታታለን

ዜግነት
ሀገራችንን እንወዳለን ሁሉም ዜጋ ሊከበር እና ዋጋ ሊሰጠዉ ይገባል ሁላችንም ደቡብ ሱዳንን ለመገንባት በጋራ መስራት አለብን፡፡

ጥቃት የሌለበት
አናታባን ለየትኛዉም የደቡብ ሱዳን ችግር አመፅ መፍትሄ እንዳልሆነ እናምናለን ስለዚህም ለሰላማዊ እንቅስቃሴ የቆምን ነን፡፡

ከፖለቲካ ገለልተኝነት
አናታባን ነፃ እና ከየትኛዉም አይነት የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ ነዉ፡፡

#ለውጡንእንሁን #BeTheChange
የትኛዉም አይነት እራስን የሚገልፅ የፈጠራ ስራ ተራ ዜጎች እርምጃ እንዲወስዱ አንዱ ማነቃቅያ መንገድ ነው ፡፡ ቴክኖሎጂ እና ዲጂታል ሚዲያ የጥበብ እንቅስቃሴዎችን ባልታሰበ ፍጥነት እና ተደራሽነት እንዲያድጉ አድርጎአል፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎችን የሰረፁ ፣ የተዛቡ አመለካከቶችን እና ቅድመ-ፍረጃዎችን ለመለወጥ በተደጋጋሚ ለታፈኑ ድምፆች ወይም መልክታቸዉን ማስተላለፍያ መንገድ ላጡ ልንጠቀምባቸዉ እንችላለን፡፡ ይህም ሰዎች የቆዩ መሰናክሎችን የሚሰብሩበት አዲስ የበይነመረብ የጥበብ እንቅስቃሴ ፈጠራ መወለድ ምክንያት ሆኖአል፡፡ ብዙ የጥበብ እንቅስቃሴዎች ፈጠራ በተሞላባቸዉ ግንኙነቶች እና ገለፃዎች አዳዲስ እይታዎችን ለማመቻቸት ፣ ዉይይቶችን ለማዳበር እና የርህራሄ ባህልን ለመገንባት እየሰሩ ነዉ፡፡

አርቴርያል ኔትወርክ - ጥበብ ለማህበራዊ ለዉጥ
በአፍሪካ ደረጃ ሰብአዊ መብት እና ድህነት ላይ የሚሰራ የጥበብ መድረክ ነዉ፡፡ አርቴርያል ተለዋዋጭ የፓን አፍሪካ የሲቪል ማህበረሰብ አርቲስቶች ኔትወርክ ፣ ስለ ባህላዊ ጉዳይ ማህበረሰብ አንቂዎች፣ ስራ ፈጣሪዎች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ተቆማት እና በአፍሪካ የፈጠራ እና ባህላዊ ሴክተር ላይ ለጋሽ ድርጅቶችን ያካትታል፡፡
http://www.arterialnetwork.org

#የጥቁሮችህይወትዋጋአለዉ (#BlackLivesMatter)
የጥቁሮች ህይወት ዋጋ አለዉ (ብላክ ላይፍስ ማተር) ምዕራፍን መሰረት ያደረገ በአባላት የሚመራ አለማቀፍዊ ኔትወርክ ነዉ፡፡ ተልዕኮዉም አካባቢያዊ ሀይል በመገንባት መንግስት በጥቁሮች ላይ እየደረሰ ባለዉ ጥቃት ጣልቃ መግባት ነዉ፡፡ የሁሉንም ጥቁሮች ህይወት ዋጋ እንሰጣለን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ያልተመዘገቡ፣ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸዉን፣ ሴቶችን፤ እንዲሁም ኔትወርካችን በጥቁሮች የነፃነት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ የተገለሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ማዕከል ያደረገ ነዉ፡፡

የጥቁሮች ህይወት በስልት ለሞት የማይዳረግባትን አይነት አለም ለመፍጠር አየሰራን ነዉ፡፡ ሰዉ መሆናችንን፣ ለዚህ ማህበረሰብ ያበረከትንዉን አስተዋፆ፣ ገዳይ ጭቆናን ፊት ለፊት መቆቆማችን እናረጋግጣለን፡፡ የጥቁሮች ሕይወት ዋጋ እንዲሰጠዉ የተደረገዉ ጥሪ ሁሉም ማድረግ ያለበትን ለነፃነታቸዉ አየታገሉ ላሉ ጥቁሮች እንዲያበረክት ነዉ፡፡

http://blacklivesmatter.com/about/

8

ከሰቀቀን መልሶ ማገገም (TRAUMA HEALING)



08 ከሰቀቀን መልሶ ማገገም (TRAUMA HEALING) ይዘቶች

ማህበረሰብ አቀፍ ግንዛቤ ስለ ሰቀቀን እና የማገገም ሂደት

ስነልቦናዊ መቋቋምያ መገንባት

የአእምሮ ጤናን በራስ የመንከባከቢያ ቀላል መመሪያ

ራስን ለመምራት መሳሪያዎች እና ቴክኒኮች

ሰቀቀን ምንድነዉ?

የሰቀቀን ምክንያቶች

የአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ሚድያ

ሁለተኛ ደረጃ (ወይም ቀጥተኛ) ያልሆነ ሰቀቀን

ምንጮች

#DEFYHATENOW | ምዕራፍ 8

ከሰቀቀን መልሶ ማገገም (TRAUMA HEALING)

ማህበረሰብ አቀፍ ግንዛቤ ስለ ሰቀቀን እና የማገገም ሂደት

ይህ ከሰቀቀን መልሶ ማገገም መመሪያ የተዘጋጀዉ በኡጋንዳ አሩዋ አውራጃ በራይኖ መጠለያ ካምፕ ዉስጥ ይኖሩ በነበሩ ደቡብ ሱዳናዉያን ስደተኞች ተሞክሮ መሰረት ነዉ፡፡ ከመድረክ አፍሪካ (platform Africa) ጋር የምትሰራዉ የስነልቦና ባለሙያ ሻርሎት ኣይነብዮኦና ኪገዝኦ (Sharlotte Ainebyoona Kigezo), Arua District, Uganda፡፡

ምልክቶችን መለየት እና ጤናማ የመቋቋሚያ መንገዶች እንዴት መገንባት ይቻላል? አእምሮን ለመጠበቅ የቀረበዉ የአእምሮ ጤና ራስን የመንከባከብያ ቀላል መመሪያ ጤናማ የመቋቋሚያ መንገዶችን እና መቋቋሙ የሚችሉ ማህበረሰቦችን እና ግለሰቦችን ሚደግፉ ኔትወርኮች ለመደገፍ የተዘጋጀ ነዉ፡፡

የአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ሚድያ ዉይይት ዉስጥ ሰቀቀን እና ማህበራዊ ሚዲያ በማገገሚያ ሂደት ዉስጥ ተካቶአል፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የአእምሮ ጤንነት ግንዛቤን መፍጠርን እና የማገገምያ ዘይቤዎች መገንባትም ቀርበዋል፡፡

ሰቀቀን ከሚፈጥር እየተካሄደ ካለ ሁነት ጋር ባለ ግንኙነት የሚፈጠረዉ ሁለተኛ ደረጃ ሰቀቀንም ተዳሰአል፡፡

> “ አስጨናቂ እና የሚያበሳጭ ክስተቶችን ሰዎች ማስተናገዳቸው የተለመደ ነገር ነው። ከብዙ ጊዜ በፊት የተፈፀመ ድርጊት ሰዎች ዛሬ ላይ ስለ ሌሎች ሰዎች እና ስለ ሁኔታዎች ያላቸው አስተሳሰብ እና ስሜት ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል። ሰቀቀን (Trauma) ማለት አንድ ግለሰብ የሚያጋጥመው ክስተት ፤ ከዚያ በኋላም እንዴት እንደሚያስቡ እና ምን እንደሚሰማቸው፤ እንዲሁም ክስተቱ እራሱም ነው። ሁለት የተለያዩ ሰዎች ለአንድ አይነት ክስተት ተመሳሳይ አይነት ምላሽ አይኖራቸውም እንዲሁም የትኛው ትክክል የትኛው ስህተት ነው ማለት አይቻለም ”

Lynn A. Kovich
State of New Jersey: Department of Human Sciences, Trauma Assessment (July: 2015)

ስነልቦናዊ መቋቋምያ መገንባት

ስነልቦናዊ መቋቋሚያ አስከፊ፣ ሰቀቀን ሚፈጥሩ፣ አሳዛኝ፣ አደገኛ ወይም ከፍተኛ ጭንቀት ምንጭ በሆኑ ሁኔታዎች ዉስጥ ደህና ሆኖ የማለፍ ችሎታን የሚወክል ቃል ነዉ፡፡ ከ ሰቀቀን በማገገም ሂደት ዉስጥ ያለ ሰዉ ስለቀስቃሶች እና ለአእምሮ ጭንቀት ያላቸዉን አስተዋፆ ግንዛቤ ማድረግ ለትክክለኛ ስነልቦናዊ መቋቋምያ አተገባበር ወሳኝ ነዉ፡፡

ስነልቦናዊ መቋቋምያ መገንባት ከአዎንታዊ አስተሳሰብ እና እራስዎን በስሜት እና በአእምሮ የበለጠ ጠንካራ ለማድረግ እርምጃ መውሰድ ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡እነዚህ እንቅስቃሴዎች እንደ አንድ የሕክምና ስነ ዘዴ እና እንደ እረፍት ለእንክብካቤ ሰጭዎች / ወላጆች / አሰቃቂ ሁኔታ ላጋጠማቸው

ሰዎች ፣ አሰልጣኞች የአእምሮ መረጋጋት እና ጥንካሬ ለመጠበቅ ይረዳሉ ፡፡ ወደ ፈውስ ሂደት ላይ እርስዎን ለመምራት ምልክቶችን ይሰጣል፡፡

በአተነፋፈስ መረጋጋትን መልመድ

ይህ የሚደረገዉ ቀስቃሽ በሆኑ ሁነቶች ወቅት አእምሮን ዘና በሚያደርጉ የተለያዩ የአተነፋፈስ ልምምዶ እና የሚያረጋጉ ሀሳቦች ላይ በማተኮር ነዉ፡፡

ታሪኮችን በመፃፍ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ መሳተፍ

ታሪክን በፅሁፍ እና በንግግር መልክ ማካፈል ለሰቀቀን ዉጤታማ ህክምና መንገድ ነዉ ፡፡ በተለይ አሁን በብሎጎች እና ፖድካስቶች አማካኝነት ማግኘት ቀላል ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ ታሪኩን ሲያጋራ እዉቅና ማግኘት እና መሰማት በራስ መተማመንን እና ማንነትን ለመገንባት አስተዋፆ አለዉ፡፡ በቡድኖች ዉስጥ ታሪክን መንገር እንዲኖር ያድርጉ ይህ በማገገም ሂደት ውስጥ ነፃነትን ያጠናክራል፡፡

ማመዛዘን አይዘንጉ

የማሰላሰል አላማ አእምሮ ባህሪ ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ሀሳቦችን መረዳት እንዲችል ነዉ፡፡ አንድ ሰው ቆም ብሎ በማሰብ እንደገና አላማዉን እነዲተረጉም እና በሰቀቀን ከተነጠቃቸዉ የመኖር ምክንያቶች የበለጠ ምክንያት እንዲኖረዉ ነዉ፡፡

አንድን ሀሳብ ስናሰላስል ልንጠይቃቸዉ ምንችላቸዉ ቀላል ጥያቄዎች

- አንተ/ቺ ማነህ/ሽ?
- ጠዋት ሚያስነሳህ/ሽ ምንድነዉ?
- ማታ ማያስተኛህ/ሽ ምንድነዉ?
- መቼ በህይወት እንዳለህ/ሽ በጣም ይሰማሀል/ሽ?
- አላማህ/ሽ ምንድነዉ?
- አላማህ/ሽ አሁን ካለህበት/ሽበት መንገድ ጋር እንዴት ይገናኛል?
- ከአላማህ/ሽ እየገደበህ/ሽ ያለዉ ምንድነዉ?
- አላማህን/ሽን ለማሳካት ያለህ/ሽ ትልቅ ሀብት ምንድነዉ?

ራስዎን ያዳብሩ

በሚገባ የዳበረ አእምሮ ለእንቅፋቶች ጥቂት ግዜ ነዉ ያለዉ፡፡ የአእምሮ መዳበር፤ እንቅፋቶች ሲመጡ እንኳን በተቀላጠፈ መልኩ የመመቋቋምን ሂደት ይፈቅዳል፡፡ መዳበር፡ በንባብ፣ ስሜታዊ ክህሎቶችን በመማር ፣ የግል ማስታወሻ በማዘጋጀት፣ ምስጋናዎችን በመፃፍ እና ከራስ ውስጣዊ ማንነት ጋር በመገናኘት፣ በማሰላሰል፣ በአተነፋፈስ እንቅስቃሴዎች እና አካላዊ እንቅስቃሴዎች ይመጣል፡፡

ደህንነትን ማሳደግ

ጭንቀት በአእምሮአዊ እና አካላዊ ጤንነታችን ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡ አዎንታዊ የህይወት ዘዬ መከተል ሆን ብሎ ራስን መንከባከቢያ ኪት በመጠቀም ሰዉነታችንን እና አእምሮአችንን እንዲለምድ ያግዛል በተለይ ከሰቀቀን መልሶ ማገገም ላይ፡፡

+

የአእምሮ ጤናን በራስ የመንከባከቢያ ቀላል መመሪያ

በዙሪያዎ ያለውን ሰላም መጠበቅ

ጤናማ ያልሆኑ የመቋቋም ዘዴዎች ይለዩ

- ☐ ከማህበራዊ ህይወት መገለል
- ☐ ከመጠን በላይ መተኛት
- ☐ ከመጠን በላይ ጣፋጭ እና ቅባት ምግቦችን መመገብ
- ☐ መድሀኒቶችን ከመጠን በላይ መዉሰድ

☐ አደንዛዥ እፆችን(ሲጋራ፣ መጠጥ፣አፒዮይድስ) ከመጠን በላይ መጠቀም
ጭንቀትን በሌሎች ላይ በቃል ወይም ያለቃል መወጣት

ጤናማ የመቋቋም ስነ ዘዴዎች መልመድ

☐ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ
☐ በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ ዉስጥ ያሉ የስፖርት ቡድኖችን መቀላቀል
☐ የእግር ጉዞ ማድረግ
☐ በቤት ውስጥ ሥራዎች መሳተፍ

ግንኙነቶችን መመስረት እና መጠበቅ

☐ ጓደኞች እና ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ቀጠሮ መያዝ
☐ ለትምህርት ቤት ክበባት መመዝገብ
☐ በጎፍቃደኝነት ስራዎችን ከግምት ማስገባት በሚያረካ መንገድ ለዓለም መልሶ መስጠት ወደሚያስችሉ ተግባራት መመለስ

የ“ጭንቀት ማስታገሻ” ቀላል መመሪያ ያዘጋጁ

☐ ተፈጥሮአዊ በሆነ አካባቢ የእግር ጉዞ ማድረግ
☐ ሜድቴት (ጥሞና) ማድረግ
☐ ሀሳብን በቃላት ወይም በስዕል (በግጥም፣ በሙዚቃ፣ በታሪክ፣ በጥበብ) ማስቀመጥ
☐ የግል ማስታወሻ መያዝ
☐ የማንበብ ልምድ ማዳበር
☐ ጭንቀት ትንሽ ሲበዛ ሻይ ወይ ቡና ማፍላት
☐ ለመቋቋም የሚቸገሩ ከሆነ ከጓደኛዎ ወይም ከባለሙያ አማካሪዎ ጋር ይነጋገሩ

ራስን ለመምራት መሳሪያዎች እና ቴክኒኮች

የሰላም ቀመር

ለመቋቋም የሰላም ቀመር ከራስዎ ጋር ወደ ነገሮች እንዴት እየቀረቡ እንደሆነ እና ለራስዎ ያለዎትን አመለካከት በመደበኛነት ለመፈተሽ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ለማስታወስ ቀላል የሆነ ሞዴል ነው፡፡ ጊዜዎን እና ጉልበትዎን እንዴት እንደሚጠቀሙ ብልህ ምርጫዎችን እየመረጡ መሆንዎን በቀጥታ ለማረጋገጥ ነው፡፡

አስቸጋሪ ማቴሪያል ላይ ሲሰሩ ወደ ኋላ መለስ በለው እራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች የጠይቁ

ፍጥነት

☐ በምን ያህል ፍጥነት እየተንዝኩ ነዉ?
☐ ይሄን ጥንካሬ መጠበቅ እችላለሁ?
☐ ለማሰላሰል እና ለመታደስ ችሎታ የሚሆን ቦታ የት አለ?

ጉልበት

☐ የኔ የጉልበት አካሄዶቼ ምንድን ናቸዉ?
☐ ነገሮችን በቅድምያ ለማዘጋጀት ብቁ ነኝ ስለዚህ በጣም አስቸጋሪዉን ማቴርያል ምጋፈጠዉ የተሻለ ጉልበት እና ምንጮች ሲኖረኝ ነዉ?
☐ ጉልበቴ ሲቀንስ ሰዉነቴን አዳምጠዋለሁ?

መቀበል.....እና.... መለመድ

☐ አስቸጋሪ ተሞክሮ እያጋጠመኝ ከሆነ ወይም የችግር ምልክቶችን በደንብ ካልተረዳሁ እንድረዳ ሚያስፈልግ ነገር ላለመቀበል
እየታገልኩ ይሆናል?

☐ በረጅም ጊዜ የበለጠ የመቋቋም ችሎታ እንዲኖረኝ ፍላጎቶቼን ከግምት ዉስጥ ማስገባት እንዴት መላመድ እችላለሁ?

ምርጫ

☐ ሥራን ለማከናወን ሀሳቤን ለመሰብሰብ የት መምረጥ እችላለሁ?
☐ ምንን ለመተዉ መምረጥ እችላለሁ (ምናልባት ለአሁኑ ብቻ)?
☐ ለእገዛ ምን መጠየቅ እፈልጋለሁ?

ራስን ማክበር

☐ ለራሴ ምን አይነት መልእክቶችን እየሰጠሁ ነዉ?
☐ ለምሳሌ ከጭንቀት ጋር እየታገልኩ ስለሆነ ለራሴ ከባድ ግዜ እየሰጠሁ ነዉ?
☐ እያደረኩ ባለሁት ነገር ጥሩ እንደሆንኩ እና እየወደኩ ሳይሆን አጠቃላይ ጥንካሬዬን እየተንከባከብኩ እንደሆነ እራሴን ማስታወስ እችላለሁ?

አተነፋፈስ እና ሌሎች የንቁ አእምሮ መሣሪያዎች

አተነፋፈስ ላይ ማተኮር የሰዉነትን ምላሽ ለመቆጣጠር እና የመረጋጋት ስሜትን ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚረዱ መንገዶች

7-11 መተንፈስ

ሰባት እስኪቆጥሩ ወደ ዉስጥ ይተንፍሱ እና አስራአንድ እስኪቆጥሩ ወደ ዉጭ ይተንፍሱ፡፡ በቁጥጥር ዉስጥ እንዳሉ እስኪሰማዎት ይደጋግሙት፡፡

ባለሶስት ደረጃ አተነፋፈስ ከአስቸጋሪ ተግባር ወይም ስራበፊት፣ በሆላ ወይም በወቅቱ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

አይኖትን በመጨፈን ወይም ዝቅ በማድረግ እራሶትን ያዘጋጁ ፣ ሰዉነቶ ከወንበር እና መሬት ጋር ያለዉን ግንኙነት ያጢኑ፡፡ እግርዎን እና ጀርባዎን ያስተውሉ እና አስፈላጊ ወደ ሚመስልዎ ቦታ ይቀይሩ ፡፡

ደረጃ 1
አሁን ያሉበትን ስሜት ያስተዉሉ እና ስም ይስጡት፡ እንዲሁም አሁን ያሎትን ስሜቶች ያስተውሉ እና ይጥቀሱ፡፡ በሰዉነቶ እየተሰማዎት ያለ ማናቸውም ስሜቶች ማስተዋል እና እውቅና መስጠት።

ደረጃ 2
ሀሳቦትን በሙሉ አተነፋፈሶ ላይ ያድርጉ እያንዳንዱ ትንፋሽ ወደ ሰዉነቶ ሲገባ ወደ ሆዶ ሲወርድ እና ተመልሶ ሲወጣ ይከታተሉት፡፡ ለአንድ ደቂቃ ይቀጥሉ ወይም አተነፋፈሶን ይከታተሉ፡፡

ደረጃ 3
በቆዳዎ ቀዳዳ እንደሚተነፍሱ ያህል ስለ ሰዉነቶ ያሎትን ግንዛቤ ይጨምሩ፡፡

ከአተነፋፈሱ ለመዉጣት ሰዉነቶ ከወንበሩ እና እግርዎት ከመሬቱ ጋር ያለዉን ግንኙነት ያስተዉሉ፡፡ በዐይኖ ሽፋሽፍት በኩል ብርሀን እንዲጀምር ይፍቀዱ ቀስበቀስ የዉጪዉ አለም ድጋሚ እንዲገባ ይፍቀዱ፡፡

መረጋጋት

ይህ ቴክኒክ ከቁጥጥሮ በላይ ሲሰማዎ አእምሮዎ እና ሰዉነትዎ አሁን እና እዚህ በአንድነት እንዲሰሩ ይረዳዎታል፡፡ ከሚከተሉት መካከል የትኛውንም በማጣመር ይሞክሩ ፣ ለአምስት ሰከንዶች በዙሪያዎ ባሉ አምስት እቃዎች ላይ ያተኩሩ፣ ሰዉነትዎ ከወንበሮ ወይም ከመሬት ጋረ ያለዉ ንክኪ ላይ ያተኩሩ፣ ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ መጠጥ በሁለቱም እጆችዎ ይያዙና ቅዝቃዜዉ ወይም ትኩስነቱ እንዲሰማዎ ያድርጉ፣ ምግብ አበባ ወይም ሌላ ነገር ያሽትቱ፣ ፊትዎን ዉሀ ይርጩ፣ ስሞትን እድሜዎትን የት እንዳሉ በሆላ የት እንደሚሆኑ ጮክ ብለዉ ይበሉ ፣ ተነስተዉ እያንዳንዱን እርምጃ እያስተዋሉ የእግር ጉዞ ያድርጉ፣ ትኩረቶን መጀመርያ በቅርብ ቀጥሎ ርቀዉ ከዛም ከክፍል ዉጭ ያሉ ድምፆች ላይ ያድርጉ፡፡

ትኩረት መቀየር

የአእምሮዎ ደህንነት ፣ የተገናኘ ወይም የተጠበቀ ሆኖ እንዲሰማዎት የሚያደርግ ምስልን ያስቡ፡፡

ከምስሉ አሁን ወደ ሚቸገሩበት ነገር ሲቀይሩ ሂደቱን በማስተዋል ያድርጉት፡፡ እየቀየሩ ከራሶ ጋር ይነጋገሩ! ያስተዉሉ ይህ ልምዱን ለመገደብ ሳይሆን በልምዱ ላይ ቁጥጥር እንዲኖሮት ለማድረግ ነዉ፡፡

ሥራዎን በማስተዋል ለመጀመር እና ለማቆም ልምዶችን ይፍጠሩ።

ምንጭ: Excerpt from FIRST DRAFT NEWS: GUIDE TO MANAGE TRAUMA
https://firstdraftnews.org/wp-content/uploads/2017/04/vicarioustrauma.pdf?x80491
Sam Dubberley, 2017

ሰቀቀን ምንድነዉ?

የሰቀቀን ትርጉሞች

"የአንድ ሰው የአስጨናቂ ሁኔታ ተሞክሮ።"

"ከፍተኛ የስሜት ክብደት ያለባቸዉ ክስተቶች በተለይ በተጋላጭ የህይወት ግዜ ላይ የተፈጠሩ፤፤"

"በአካል የመኖር ወይም የስሜት ወይም ስነልቦናዊ ደህንነታችን አደጋ ላይ የሚጥል ክስተት፣"

ሰቀቀን ከስድብ፣ በልጆች ላይ ከማሾፍ፣ በጨለማ ዉስጥ ከማስደንገጥ፣ በእባብ ወይም በሸረሪት ከማባረር፣ ስም ከማጥፋት፣ በልጅነት ወላጅን ከማጣት፣ ለጾታዊ ግኑኘነት ከመገደድ ሊመጣ ይችላል፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች እንዳንዴ እንደ ቀስቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ ፣በተለይ አንድ ሰው ከዚህ በፊት አንደዚህ ዓይነት አእምሮ የሚያስጨንቅ ክስተት ያጋጠመው ከነበረ፡፡ አካላዊ አደጋዎች ጠባሳ እንደሚጥሉ ሁሉ ሰቀቀንም ለአመታት የሚቆይ ጠባሳ ሊተዉ ይችላል፡፡

ለረጅም ግዜ ያልታከመ ሰቀቀን የተወሰኑ ዉጤቶች

- የሰዎችን ልማዶች እና ለሕይወት ያለንን አመለካከት አሉታዊ በሆነ መልኩ ይለውጣል፡፡
- በቤተሰብ እና በግል ግንኙነቶች ላይ ጫና ያስከትላል፡፡
- አካላዊ ምልክቶችን እና በሽታዎችን ያስከትላል፡፡
- ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ችግሮች ያስከትላል፡፡
- መገለልን ያስከትላል፡፡
- ራስን ጎጂ የሆነ ባህሪን ያበረታታል፡፡

ካለይ የተገለፁት ምልክቶች ከሰቀቀን ሁኔታ ጋር የተያያዙ ብቻ አይደሉም ፡፡ ያልታወቁ ጉዳዮች ካሉ ምርመራ ማድረግ እንዲችሉ እባክዎትን የባለሙያ እርዳታ ይጠይቁ፡፡ ሰቀቀን የሚያስከትሉ ሁነቶች ዉስጥ ካለፉ ለተፅእኖቻቸዉ ትኩረት መስጠት እና እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡

የሰቀቀን ምክንያቶች

የሰቀቀን አንዳንድ ምክንያቶች

- አካላዊ ጥቃት ለምሳሌ የቤት ዉስጥ ጥቃት (ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት)።
- ወሲባዊ ጥቃት ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር፣ ከስጋ ዘመድ ጋር ጾታዊ ግንኙነት፣ ወሲባዊ ጥቃት በህፃናት ላይ።
- ስሜታዊ ጥቃት።
- በልጅነት እንክብካቤ አለማግኘት ለምሳሌ በልጅነት ከአሳዳጊ በግድ መለየት፣ በአሳዳጊ የልጅን ስሜት አለመረዳት።
- የጦርነት / የውጊያ ልምዶች።

- ሌሎች ላይ ጥቃት ሲፈፀም መመልከት ለምሳሌ ሌላ ሰው በጭካኔ ሲደበደብ ወይም ሲሰቃይ መመልከት።
- ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ማንኛውም ጉልህ ጉዳት።
- ለህይወት አስጊ የሆነ በሽታ ለምሳሌ ካንሰር፣ የኩላሊት ስራ ማቆም፣ ኤችአይቪ ኤድስ።
- ከፍተኛ የስነልቦና / ማህበራዊ ቀዉስ ለምሳሌ ኪሳራ፣ አሰቃቂ የቤተሰብ ሞት፣ ዉድ የሆነ ንብረት ማጣት፣ የወዳጅ ድንገተኛ ሞት።
- ተፈጥሮአዊ አደጋ (የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳት፣ ጎርፍ፣ አዉሎንፋስ ወዘተ)።
- እንደ መኪና ፣አዉሮፕላን ወይም ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ከባድ አደጋዎች።

የአእምሮ ጤና እና ማህበራዊ ሚድያ

ሰቀቀን + የጥላቻ ንግግር

ማህበራዊ ሚዲያ የማንነት ነፃነትን ይፈቅዳል ፣ ስለዚህም ለሰዉ ልጆች እራሳችንን እንድንገልፅ እድል ይሰጡናል ፣ ነገር ግን በድብቅ፡፡ ይህ የሚጎዱ ነገሮችን ለመፈወስ እንደ መንገድ ሊታይ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ህመም ወደ አሉታዊነት ይመራል ምክንያቱም የሌላ ሰዉን ሥቃይ ማየት ለራሳችን ያለን አመለካከት ለሰቀቀን መልሶ ማገገም ወሳኝ ክፍልን ይሰጣል፡፡

ከ ሰቀቀን ላገገሙ ሰዎች ማንነትን መገንባት አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንድ ሰዉ እንደ መልእክት ላኪ ወይም ተቀባይ በይነ መረብን እንዴት ለፈዉስ መጠቀም እንዳለበት ሚረዳዉ ከማንነት ነዉ፡፡ ከበይነመረብ አሉታዊነት እና ከሳይበር ጥቃት የተጠበቀ የማንነት እድገት መንገዶች አንዱ ጠንካራ የማህበራዊ ድጋፍ ስርአት በመመስረት ነው፡፡

የማህበራዊ ድጋፍ አስፈላጊነት

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች ሰቀቀን ሚፈጥሩ ሁኔታዎች ዉስጥ ሲያልፉ እና ልምዳቸዉን ለሌሎች ሲያካፍሉ የጤና ሁኔታቸዉ ይሻሻላል፡፡ ምንም እንኳን ስለ አስጨናቂ ክስተት ማውራት ለጊዜው ሰዎችን ቢረብሽም ፣በረዥም ግዜ ግን ያረጋጋቸዋል፡፡

የማኅበራዊ ድጋፍ ስርዓቶች የግለሰቦች ጭንቀትን የመቋቋም ፣ አቅም ለማጎልበት የስነ-ልቦና እና ቁሳዊ ሀብቶች ያቀርባሉ ፡፡

ማህበራዊ ድጋፍ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በባልደረባ፣ በቡድን ሕክምና ጊዜዎች፣ ሰቀቀን መልሶ ማገገም ኢኒሼቲቮች የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡ ፡ ማህበራዊ ድጋፍ ማንኛዉንም አይነት ቅርፆች ሊይዝ ይችላል ለምሳሌ መዋቅራዊ ድጋፍ(የግለሰቡ ማህበራዊ ኔትወርክ መጠን እና ስፋት፣ የማህበራዊ ግንኙነት ድግግሞሽ) ተግባራዊ ድጋፍ (ምቾትን የሚያዳብሩና ግለሰቡ/ቡዋ በሌሎች እንደሚወደድ/ እንደምትወደድ፣ እንደሚከበር/ እንደምትከበር፣ ግድ እንደሚሰጠዉ/ጣት የሚያዳብሩ ባህርያት) የመሳሪያ / ቁሳቁስ ድጋፍ (ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ እቃዎች እና አገልግሎቶች) እና የመረጃ እና የእዉቀት ድጋፍ (ግለሰቦች ወቅታዊ ችግሮችን እንዲቋቋሙ፣ ችግሩን እንዲረዱ እና ለተፈጠረዉ ለዉጥ እራሳቸዉን እንዲያዘጋጁ አስፈላጊ መረጃ መስጠት)፡፡

የመጠበቅያ መንገዶች

ማንነትን ከበይነመረብ ጉዳቶች መጠበቅ

ድጋፍ

- ☐ ጠንካራ ማህበራዊ ድጋፍ ስርአት መገንባት እና ከሰዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መኖር

መንፈሳዊነት

- ☐ እምነትን እና ተስፋን ማጠንከር ለማንኛዉም ስነልቦናዊ ጉዳይ ወሳኝ መጠበቅያ መንገድ ይሆናል

ማንነት

- ☐ ከምን ወይም ከማን ጋር ራስዎትን እንደሚገልፁ መማር
- ☐ ይህ ለራስ ያለን አመለካከት ይገነባል በጊዜ ሂደትም በራስ መተማመንን ለመገንባት ይረዳል

አካላዊ ጤንነት

- ☐ ይህ አእምሮን ብቻ ሳይሆን የሰዉነትንም ጤና ንቁ እና አዲስ አርጎ ይጠብቃል

መዝናኛ/ ራስን መንከባከብ

- ☐ እምቅ ፍላጎትን እና ችሎታን ማወቅ እንደ አዎንታዊ መቋቋምያ ያገለግላል።የሄም ማንነትን ለመገንባት በራስ ለመተማመን እና ራስን ለማወቅ መሰረት ነዉ::

ሁለተኛ ደረጃ (ወይም ቀጥተኛ) ያልሆነ ሰቀቀን

ተንከባካቢዎች እና ሌሎች ሰብአዊ ድጋፍ ሠራተኞች ራሳቸውን በደንብ መንከባከብ አለባቸው::

ሁለተኛ ደረጃ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ሰቀቀን፡- ሰቀቀን ከሚያስከተሉ የሕይወት ክስተቶች ከተረፉ ሰዎች ጋረ አብረው የሚሰሩ ሰዎች ሊያጋጥማቸው የሚችል ጭንቀት ነው:: ለቀጥተኛ ሰቀቀን ዉጤቶች በአሰቃቂ ምስሎች እና ክስተቶች አማካኝነት ተጋላጭ መሆን እነዚህን ተፅእኖዎች ሊያባብስ ይችላል:: ሰቀቀን አማካሪዎች እና ተንከባካቢዎች ስነልቦናዊ እንክብካቤ እና ድጋፍ ሊያስፈልጋቸዉ ይችላል:: ይህም ቀጣይ ትምህርት ፣ ድጋፍ እና ሪፈራል ለማቅረብ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

አሰቃቂ ምስሎችን እና ክስተቶችን በማውጣቱ ለቀጥተኛ ሰቀቀን ውጤቶች መጋለጥ እነዚህን ውጤቶች ሊያስከፉ ይችላል።

እንደተንከባካቢ ለራስዎ ትኩረት እንዲሰጡ ይበረታታሉ

አካላዊ ደህንነት

- ☐ በቂ እንቅልፍ ይተኙ
- ☐ ጤናማ ምግብ ይመገቡ (በቂ የተመጣጠነ ምግብ)
- ☐ አረፍት
- ☐ በመደበኛነት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያድርጉ
- ☐ ይተንፍሱ

አእምሮአዊ ደህንነት

- ☐ አዎንታዊ አመለካከት እና አዉድን ማስተካከል
- ☐ እንቅፋቶችን እንደ መማርያ እና ማደግያ እድል ይመለከቱ
- ☐ ከችግሮች እንፃር መፍትሄ ተኮር ይሁኑ
- ☐ ዘና ማለት/ ሜድቴት (ጥሞና) ማድረግ

ስሜታዊ ደህንነት

- ☐ ቋሚ የሆነ የማህበራዊ ድጋፍ ይኑሮት
- ☐ ከቤተሰብ ፣ ከጓደኞች እና ከሥራ ባልደረቦች ጋር ድጋፍ ሰጪ ግንኙነቶች
- ☐ ስሜቶት በተገቢዉ ይጋፈጡት፡ በንዴት ግዜ አዎንታዊ መዉጫ ወይም መቋቋምያ ስነ ዘዴ ያዳብሩ

ግንኙነቶች

- ☐ ጠንካራ ግንኙነቶችን ያሳድጉ እና እርሶን ከሚቀበሉ ስለ እርሶ ግድ ከሚላቸዉ እና ከምታምኑአቸዉ ሰዎች ጋር ግዜ ያሳልፉ።
- ☐ ዉጤታማ ተንከባካቢዎች ፍላጎቶቻቸዉን ሊያዉቁ እና እርዳታ ሊጠይቁ ይገባል።
- ☐ ለደንበኞች / ከሰቀቀን ለተረፉ የሪፈራል ኤጀንሲዎች (ህግ፣ ህክምና፣ ምግብ)።
- ☐ በብዙ የስራ ሃላፊነት ምክንያት ተያይዘዉ ሚመጡ ድካምን ለመቀነስ ይህ መረጃ በቀላሉ የሚገኝ መሆን አለበት።
- ☐ እንደ ተንከባካቢ ቀጥተኛ ያልሆነ ሰቀቀንን እና ድካምን ለማስወገድ ብቸኛዉ መንገድ እራስዎን መንከባከብ ነዉ።

ዋቢዎች

02 ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚዲያ

ሰላም በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን

- **Building Peace through Journalism in the Social/Alternate Media, Dr. Rukhsana Aslam, Media and Communication, 2016, Volume 4, Issue 1, Pages 63-79 Doi: 10.17645/mac.v4i1.371**
- **https://www.cogitatiopress.com/mediaandcommunication/article/viewFile/371/371**

08 ከሰቀቀን መልሶ ማገገም

ምንጭ እና ምንጮች

- State of New Jersey: Department of Human Sciences, Trauma Assessment (July: 2015)
  http://www.ctc@georgetown.edu
- Dr. S. Ndegwa: Psychology Notes, Unit Psy 418 – PTSD (September: 2015) How does social support enhance resilience in the trauma – exposed individual (2015)
  http://www.ecologyandsociety.org/vol20/iss4/art10/
- Ugur Gunduz: The Effect of Social Media on Identity Construction (September: 2017)
  www.mcser.org
- Chapter 3: Understanding the Impact of Trauma
  https://www.ncbi.nlm.nih.gov/books/NBK207191/
- Trauma symptoms, Causes and Effects
  https://www.psychguides.com/trauma/

ለአመቻቾች ማስታወሻ

ስልጠናን እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?

ለመስጠት ላሰቡት ሥልጠና የተሻለ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እነዚህን ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነዉ።

ስነ ዘዴ

ምርጥ አሰልጣኝ ለመሆን ቀድሞ መዘጋጀት እና ለሰልጣኞችዎ ማስተላለፍ ሚፈልጉትን መልዕክት በሚገባ ማወቅ ነዉ። ለአቻ ለአቻ ዉይይት ዋጋ እንደሚሰጥ ማህበረሰብ ሌሎች እንዲማሩ ለማመቻቸት እና ለመደገፍ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ማወቅ አስፋላጊ ነዉ።

የእዉቀት ሽግግርን ከግምት ዉስጥ ማስገባት

ለእዉቀት ሽግግር ጥሩ መንገዶችን ማወቅ አስፈላጊ መነሻ ነዉ።

ማድረግ ስለምንፈልገዉ ነገር እዉቀት አለን? መረጃ ያቀብሉ ፣ ያስተምሩ ፣ ነገሮችን እንደሚፈለገዉ ያስኪዱ - ግን እንዴት?

እንዴት? ሚለዉ ጥያቄ እስፈላጊ ነዉ ፤ ምክንያቱም ያለ ትክክለኛ ስነ ዘዴ ፣ መረጃ ማጋርያ መንገድ እና አቀራረብ ፣ ነገሮች ከቁቁጥጥር ዉጪ ሊሆኑ ይችላሉ።

- ☐ መጀመርያ ርዕሱን ይምረጡ።
- ☐ በመቀጠል የግል እውቀትዎን እና ለዚህ ክፍል በተሻለ ሊስማማ የሚችል የክፍለ-ጊዜ ዓይነት ይገምግሙ። ስለሚያነሱአቸዉ ርዕሶች እና ተያያዥ ጉዳዮች የሰልጣኞችዎን የእዉቀት ደረጃ እና ክህሎት ለማወቅ ምርምር ያድርጉ። ለሰልጣኞች ለማገዝ እውቀትዎን ማሻሻሎን ይቀጥሉ እና ቀድመዉ ይገኙ።

ማቴርያል እና ይዘት ዝግጅት

- ☐ ይዘቱን ቅርፅ ለማስያዝ ጥናት ያድርጉ እና እውቀትዎን እንዴት በተሻለ ማጋራት እንደሚችሉ ይወስኑ። እንደ መስክ መምርያ አይነት ትምህርታዊ መርጃዎችን ይሰብስቡ።
- ☐ ከተዘጋጀዉ ይዘት እና እውቀትዎን ለማጋራት ፍቃደኝነት በሆላ አመቻች የሆነዉ ሰዉ ያቀራረብ ክህሎት ላይ ያተኩሩ።
- ☐ የተናጋሪውን ልህቀት እና ተዓማኒነት ለመለየት ታዳሚው በሁሉም ረገድ ጠንቃቃ ሊሆን ይችላል። ከእድማጮችዎ ጋር በጥሩ የሰዉነት እንቅስቃሴ፣ በትክክለኛ ተግባባቦት፣ በተረጋጋ ንግግር፣ እና በራስ መተማመን እምነትን ይፍጠሩ።

ክፍለ ግዜዎችን ማዘጋጀት

- ☐ የድርጊት ጥሪዎ ምንድነው? / የውጤት መስፈርቶችዎስ?
- ☐ የሚፈለገዉ ዉጤት ምንድነዉ? አድማጮችዎ እንዲያዉቁ/ እንዲማሩ/ እንዲረዱ ሚፈልጉት ምንድን ነው?
- ☐ ምን ያህል ግዜ አልዎት?
- ☐ ምን ያህል ግዜ ያስፈልግዎታል?
- ☐ ምን አይነት ክፍለግዜ ለእርስዎ እና ለእድማጮችዎ የበለጠ ይስማማል?
- ☐ ምን አይነት ቁሳቁሶች አሎት?
- ☐ የእርስዎ ክፍለ ጊዜ በየትኛው ቦታ ይካሄዳል?
- ☐ የእርስዎ ርዕስ ምን ያህል ቴክኒካዊ ነው? ውስብስብስ ነው?
- ☐ ምን ያህል ተሳታፊ አለ?

- ☐ የተሳታፊዎች ቁጥር ሦስት እጥፍ ቢያድግ ወይም ግማሽ ቢሆን እንዴት ያደርጋሉ?
- ☐ ከተሳታፊዎች ምን ይጠብቃሉ?

ስለ ማህበረሰብዎ ያስቡ

- ☐ ገለፃ ማዘጋጀት አለብዎት?
- ☐ ከመስክ መመሪያዉ ማቴሪያል እንዴት ነዉ ሚጠቀሙት?
- ☐ ለታሳታፊዎች ወረቀት ያስፈልጋል?
- ☐ ከከአጠቃላይ ስርአተ ትምህርቱ ወይም ካለው የግዜ ሰሌዳ ጋር ይሄዳል?
- ☐ የክፍለ ጌዜያቶች መግለጫ ቅፅ አሎት?
- ☐ ምን መተግበር ወይም ዉጤት ማምጣት ይፈልጋሉ፤ መጨረሻ ላይ ለማተም ይፈልጋሉ?
- ☐ መልመጃ ማዘጋጀት ያስፈልጎታል?
- ☐ ማህበራዊ ሚድያ ስትራቴጂ ወይም ዘመቻ ያስፈልጎታል?
- ☐ የማስተማሪያ መምርያ ያስፈልጎታል?
- ☐ የብሎግ ልጥፎች፣ የሬድዮ ቃለ መጠይቅ፣ ለመገናኛ ብዙሃን ህትመት የሚቀርብ ጽሑፍ (በይነመረብ ወይም በህትመት) ያስፈልጎታል?
- ☐ የትምህርትዎ ማጠቃለያ እና ቀጣይ እርምጃዎችዎስ?

አሰልጣኙ በትንሹ የሚከተሉትን ማዘጋጀት ይኖርበታል

- ☐ ለተሳታፊዎች ሚላክ ርዕስ እና መግለጫ (ከተሳታፊዎች እና ከአሰልጣኝ ሚጠበቅ ነገርን ማስቀመጥ)።
- ☐ የክፍለ ግዜ ዝርዝር (ደረጃ ፣ መሣሪያዎች ፣ ብቃቶች ፣ ዓላማዎች ፣ ግምቶች ፣ ችግሮች ፣ ታዳሚዎች)።
- ☐ የምንጭ ዝርዝር - የጥያቄ ወረቀት ወይም ገለፃ (እንደ ክፍለ ጊዜዎ ዓይነት)።

አንዳንድ ሊያዘጋጁአቸዉ የሚችሉ ነገሮች

- ☐ ለተሳታፊዎ አስፈላጊ ብለዉ ሚያስቡአቸዉን ምንጮችን ይዘርዝሩ።
- ☐ አባባሎች ሲጠቀሙ ለባለቤቶች እዉቅና መስጠትዎን ያረጋግጡ ፡፡
- ☐ ሚጠቀሙዋቸዉ ምስሎች፣ ሙዚቃዎች፣ ቪዲዮዎች ተገቢዉ ፍቃድ እንዳላቸዉ ያረጋግጡ እና ሁል ግዜ ለፀሀፊዎችን እዉቅና ይስጡ ፡፡
- ☐ አዉነታዎችን እና ፍቃዶችን ደግመዉ ያረጋግጡ፡፡
- ☐ ፎስ ሶፍትዌርን (FOSS software) እና የፈጠራ ሥራዎች ፈቃድ (Creative Commons) ይዘት ያስታዉሱ።

ክፍለ ግዜዎችን ማቀድ

- ☐ ግዜ ይዉሰዱ
- ☐ ማቴሪያሉን ያጥኑት
- ☐ የራሶትን ቃላት ይጠቀሙ
- ☐ የልምምድ ትምህርትን ያካቱ
- ☐ አጠቃላይ መግብያ እና አላማዎች
- ☐ የትምህርት እቅድ ይፃፉ - የሥርዓት ትምህርት መመሪያ እና አሰጣጥ

አማራጭ ክፍለ ግዜዎች

- ☐ ምን አይነት ክፍለ ግዜዎችን እንደምታቀርቡ ይወስኑ ምክንያቱም በአሰጣጥ ስነ ዘዴ ዎች ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር።

- ☐ በአጭር ጊዜ መጽሐፍ በትብብር ሚፃፍበት ይሁን፣ የፓናል ውይይት ፣ አውደ ጥናት ፣ ቁልፍ ማስታወሻ ፣በትብብር የኮምፒተር ፕሮግራም ሚሰራበት ፣ ላብ ፣ ኮንፈረንሶች ፣ ስብሰባ ፣ የሳይንስ አውደ ርዕይ ፣ መደበኛ ያልሆነ ውይይት ወይም ክርክር።
- ☐ የክፍለ-ጊዜ ቅርጸት ሊያስተላልፉት የሚፈልጉትን እዉቀት ይዘት እና አቅርቦት ላይ ተፅእኖ አለው፡፡

ጥሩ ክፍለ ግዜዎችን ማረጋገጥ

- ☐ የተሳታፊዎችን ፍላጎት ዳሰሳ ያድርጉ፣ በጣም ንቁ ከሆኑ ተሳታፊዎችን ያካቱ
- ☐ ሚጠበቁ ነገሮችን ያስቀምጡ በገሀዱ አለም ግንዛቤ ይዘጋጁ
- ☐ የክፍሉ አቀማመጥ (ጠረጴዛዎች፣ ስርአት፣ ለቡድን ያለዉ አነቺነት)
- ☐ መሳሪያዎች፣ የስነምግባር ደንብ፣ የግዜ ሰሌዳ

የቃል ገለፃ

- ☐ እርስዎን የሚረዱ ስልቶችን ይማሩ - የማስታወስ ችሎታ ፣ የንግግር ዘዬ (ከመደበኛ ንግግር ይልቅ መደበኛ ያልሆነ)፡፡ ሲናገሩ ይጨነቃሉ? ጭንቀቶን ለማሸነፍ መስታወት ፊት በመቆም ንግግር ይለማመዱ ወይም የአተነፋፈስ ልምምድ ማድረግ ይችላሉ፡፡
- ☐ ማቴሪያሎን ይወቁ
- ☐ መተንፈስ ያስታዉሱ
- ☐ አቀማመጥ ወይም አቆቆም ይረዳል
- ☐ ይለማመዱ
- ☐ መልዕክቱ ላይ ያተኩሩ
- ☐ ተሳታፊዎችን ይወቁ
- ☐ እራስዎን ያረጋጉ
- ☐ ንቁ ይሁኑ
- ☐ የጭንቀትን ኃይልዎን ይቆጣጠሩ እና ወደ ግለት ይቀይሩት
- ☐ የራስዎን ዘይቤ ይጠቀሙ
- ☐ ዘና ይበሉ

ግንዛቤ ለማሳካት የንግግርን ተስማሚ ባህሪያትን ከግምት እናስገባ፤ የሃሳቦችዎን ግልፅነት ፣ የቋንቋ አጠቃቀም ፣ ስሜትን (Passion) ማጋራትን እንዲሁም የሰውነትዎን ቋንቋ፡፡

Feb 3rd 2017
Marina Modi, FIRST PUBLISHED in MEDIUM by KAPITAL

ማስታወሻ:

____

____

____

____

____

____

1

የሚታደሉ
የመልመጃ ወረቀቶች
እና መልመጃዎች

ማህበራዊ ሚድያ
እና ግጭት

#defyhatenow | 1 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ማህበራዊ ሚድያ እና ግጭት

የበይነመረብ ላይ ያሉ የጥላቻ ንግግር ተፅእኖዎች ላይ ግንዛቤ ማሳደግ ፣ አደገኛ ንግግሮችን መቃወም እና አመፅ ማነሳሳትን የሚቀንሱ ስትራቴጂዎች።

#DEFYHATENOW የጥላቻ ንግግር ግንዛቤ ስልጠና እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል

ለአመቻቾች የማረጋገጫ ዝርዝር — ከወርክሾፑ አስቀድመው ያረጋግጡ

- ☑ አቴንዳንስ ወረቀት
- ☑ የትራንስፖርት ክፍያ ወረቀት (አስፈላጊ ከሆነ)
- ☑ የግብረመልስ ጥናት ቅፅ
- ☑ የመልመጃዎች ሪፖርት ማድረግያ ቅፅ
- ☑ ፎቶዎች/ ቪዲዮዎች (ፎቶ እንሺ፣ ድምፅ ቀጂ)
- ☑ ፕሮጀክተር (አስፈላጊ ከሆነ)
- ☑ ፍሊፕ ቻርት እና እስክሪፕቶ
- ☑ ተርጎሚ (አስፈላጊ ከሆነ)
- ☑ ማስታወሻ ያዥ

የ#defyhatenow ተነሳሽነት መግብያ

ቁልፍ ነጥቦች፥

- ☐ #defyhatenow ከሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር በአጋርነት የሚሰራ በ Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH አስፈጻሚነት በአዉሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ በሚተገበረዉ የምእራብ ኢትዮጵያ - ምስራቅ ሱዳን አገር አቋራጭ ትብብር ፕሮጀክት መዋቅር ስር ያለ ተነሳሽነት ነዉ።
- ☐ በሚድያ ፣ በውጭ ኃይሎች ኃይል እና ሰዎች እንዴት ነዉ ቴክኖሎጂን በኢትዮጵያ ለልማት እየተጠቀሙ ያሉት ሚለዉ ላይ ፍላጎት አለ።
- ☐ የጥላቻ ንግግር ባለፈዉ ዘመን ጀርመንን ወደ ጥቃት እና የዘር ማጥፋት መርትዋታል (ሁለተኛዉ የአለም ጦርነት)።
- ☐ ጀርመን እንደ ሀገር፡ የጥላቻ ንግግር እስከ አሁን ድረስ ከትትል ይደረግበታል፤ በተለይም በማህበራዊ እና ባህላዊ ሚዲያ፡፡
- ☐ የወርክሾፑ አላማ በጥላቻ ንግግር እና ጥቃት ማነሳሳት መካከል ያለን ግንኙነት በኢትዮጵያ ግንዛቤ ያላቸዉን ሰዎች ለማገናኘት እንዲሁም ጥቃትን እና የጥላቻ ንግግር ለመቃወም መንገዶችን ለመፈለግ ነዉ፡፡

☐ የፕሮጀክቱ ትኩረት በኢትዮጵያ ዉስጥ ነዉ፤ ነገር ግን ዲያስፖራዎችንም ያሳትፋል እንዲሁም በእነዚህ ሁለት ቡድን ዉስጥ ያሉ የማህበረሰብ እንቂዎችን ለማቀራረብ እና ግጭት ሚያባብሱ አሉታዊ የማህበራዊ ሚድያ ግንኙነቶችን መቃወሚያ ስነ-ዘዴዎችን እና መሳርያዎችን ለማሳየት ይጥራል፡፡

የመጨረሻ ግቡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እርምጃ መዉሰድ እና ማህበረሰቡን በመሳተፍ የበይነመረብ የጥላቻና ፣ አደገኛ ንግግሮች ተፅእኖ ላይ ግንዛቤ ማሳደግ ነዉ። በተጨማሪም ግጭት ሁኔታዎችን እና አመፅ ማነሳሳትን መቀነስ ፣ የባህል ልዉዉጥ መፍጠር እንዲሁም መተማመን እና መገንባት ያካትታል።

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

1. ቡድኑ ዉስጥ ያሉትን ሁሉንም እራሳቸዉን እንዲያስተዋዉቁ እና ስለ ጥላቻ ንግግር ያላቸዉን አረዳድ ወይም ትርጉም ይጠይቁ። የትርጉሞቹን ወሳኝ ነጥቦች በፍሊፕ ቻርት ላይ እሚፅፍ አንድ ሰዉ ይምረጡ፣ ቡድኑ እንዲያየዉ ይለጥፉት።

ከመግብያ በሆላ ሚጨመር ጥሩ ማጣቀሻ የሚከተለዉ የሱዛን ቤኔሽ (በዓለም ሰላም ኢንስቲትዩት ፣ አደገኛ የንግግር ፕሮጀክት, Senior Fellow, based at World Peace Institute) የአደገኛ ንግግር ትርጉምን ይጠቀሙ።

“የጅምላ አመፅ ከመከሰቱ በፊት አመፅ የሚያነሳሱ የሕዝብ ንግግሮች በተከታታይ ይኖራሉ፡፡ እንዲያውም ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ይጠቆማል። የገዳዮች ቡድን በራስ ተነሳሽነት አይፈጠርም፡፡ በአብዛኛዉ ሁኔታዎች ጥቂት ተደማጭነት ያላቸው ተናጋሪዎች ቀስ በቀስ ቡድንን ወደ አመፅ ያነሳሳሉ፡፡

በማንኛውም መንገድ በዚህ ሂደት ጣልቃ በመግባት አመፅን ልንከላከል እንችላለን፡ ንግግሩን በማገድ፣ ስርጭቱን በመገደብ ፣ የተናጋሪውን ተዓማኒነት አጠያያቂ መሆኑን በማሳየት ወይም በንግግሩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ወይም አደገኛ እንዳይሆን አድማጮቹን ማሳመን።”

2. ዉይይቱን ተከትሎ የወርክሾፑ መሪ የጥላቻ ንግግርን ለመተርጎም አንዳንድ ዘዴዎችን ሊዘረዝር ይችላል። በባለፈዉ ወርክሾፕ በበይነመረብ ላይ ወደ አደገኛ ንግግር የሚያመሩ ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች ፣ ስሜታዊ ገጽታዎች ፣ የፖለቲካ እና የማንነት ትስስሮች ላይ ውይይት ተካሂዷል።

በበይነ መረብ ላይ እና በሚድያ የአደገኛ ንግግር ክስተቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶች እና የዚህ ዓይነት ንግግሮች ወደ ጥቃት የመምራት እድልን ልብ ይበሉ (ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካ እና ሩዋንዳ) እንዲሁም ሀሳብን በነፃ ነት መግለፅ እና የጥላቻ ንግግር መካከል ስላለ ልዩነት።

መልመጃ ፡ የጥላቻ ንግግር በበይነመረብ

☐ ስለጥላቻ ንግግር እና አደገኛ ንግግር ለመወያየት የጥላቻ ንግግር ክፍፍሎችን ፖስተር ይጠቀሙ።

☐ የጥላቻ ንግግርን አጋጥሞት ከነበረ የራስዎን ምሳሌዎች መርጠዉ ማሳየት ይችላሉ።

☐ ለጥቃት ሚያነሳሱ የጥላቻ ወይም አደገኛ ንግግሮችን ሰዎች ሲያጋሩ ያዩት ምሳሌዎችን ያሳዩ።

☐ ይሄንን ማቴሪያል እና ፖስተሩን በመጠቀም የተለያዩ የጥላቻ ንግግር አይነቶችን እና የጥላቻ ንግግሮች እንዴት ከአደገኛ ንግግሮች እንደሚለይ ይወያዩ፡፡

☐ የአደገኛ ንግግር እና ለጥቃት ማነሳሳት ምን ምን እንደሚይዙ ያብራሩ - ለእርምጃ ግልፅ የሆነ ጥሪ አለ - ሁል ግዜ የጥላቻ ንግግርን አያካትትም።

☐ የተመረጡ የጥላቻ ንግግር ምሳሌዎችን ይዘት እና አላማ ይወያዩበት።

☐ የቃላት ትርጎሜዎችን እና በትርጎሜያቸዉ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት ከግምት ያስገቡ።

☐ ከሰዎች ጋር በበይነመረብ ወይም ከበይነመረብ ዉጪም ስትገናኙ ቃላቶችን በጥንቃቄ መምረጥ አስፈላጊ ነዉ።

☐ በይነመረብ ላይ ፅሁፍ ከመፃፍ፣ ልጥፍ ከመለጠፍ፣ ፅሁፎችን ከማጋራቶ በፊት ስለሚጠቀሙአቸዉ ቃላት እንዲያስቡ ይመከራል ይህ ሰዎችን ሊያስቀይም ስለሚችል።

እራስዎትን ይጠይቁ፡ “የሚጠቃዉ ቡድን አባል ብሆን ምን ይሰማኛል?”

የቃላቶችዎ ተፅእኖ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ይመዝኑ ፣ የፃፉትን ወይም መግለጫዎችን መልሰዉ ለማንበብ ግዜ ይዉሰዱ ካስፈለገ እረፍት ወስደዉ ሲረጋጉ ይመለሱ።

ፔሳቼክ (PESACHECK)፣ የምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያዉ እዉነታ መመርመሪያ ተነሳሽነት

ፔሳቼክ የእዉነታ መመርመሪያ ተነሳሽነት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተለጠፉ ዜናዎች እና ምሳሌዎች ሚያረጋግጥ ተነሳሽነት ነዉ።

ከፌስቡክ እና የመሳሰሉ ማህበራዊ ሚድያዎች ጋር በአጋርነት በመስራት ፣ እንደ ፔሳቼክ ያሉ ሶስተኛ ወገን እዉነታ ማረጋገጫ ድርጅቶች እዉነታን ከልብ ወለድ ለመለየት ይረዳሉ። ይህንን የምናደርገው ለህብረተሰቡ በማኅበራዊ ሚዲያዎቻቸዉ ግርግዳዎች ላይ ለሚመለከቷቸው ልጥፎች የበለጠ ጥልቅ ማስተዋል እና አውድ በመስጠት ነው።

ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች

- የጥላቻ ንግግሮች ቃላት እና አላማዎች መረዳት::
- ምን ማለት እንደሆነ እና አንድ ሰው ሳያውቅ የት እያሰራጨው ሊሆን እንደሚችል::
- በይነመረብ እና በገሀዱ አለም ምንጠቀማቸውን ቃላት የማሰላሰል አስፈላጊነት::
- ጥንቃቄ የመዉሰድ እና እራስን በይነመረብም ሆነም በገሀዱ አለምም ከርህራሄ እና መቻቻል አንፃር ጥያቄዎችን መጠየቅ::

የቡድን ዉይይት

3. ዉይይቱ በጥያቄ ወይም በአስተያየት የተዋቀረ ክፍለ ግዜ መሆን ይችላል:: ከአጋር ቡድኖች ሊተረጉሙ ወይም መልስ ሊሰጡ ሚመጡ የተወሰኑ ሰዎች መኖር አለባቸዉ:: ካልሆነ ቡድኑ እራሱ እርስ በእርስ አስተያየት መስጣጠት እና መመላለስ ይችላሉ፤ ነገር ግን የወርክሾፑ መሪ ዉይይቶቹ ዉጤታማ አርን ማስቀጠል አስፈላጊ ነዉ:: (የሚናገሩትን ይቀያይሩ፣ በጣም ፖለቲካዊ ላለመሆን ይሞክሩ እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች አጠቃላይ ውይይቱን እንዲቆጣጠሩት ላለመፍቀድ ይሞክሩ)::

ተጨማሪ መረጃ

4. ዉይይቱ ሊያልቅ ሲል የወርክሾፑ መሪ ሚድያዎች (ባህላዊ እና ማህበራዊ) በጥላቻ ንግግር ዙሪያ ያላቸውን ሚና ማዉራት መጀመር አለበት::

☐ ቡድኑን በባህላዊ ሚድያ እና በማህበራዊ ሚዲያ መካከል ያለዉን ልዩነት እንዲመረምሩ ይጠይቁ::

☐ በልዩነቱ ላይ መወያየት ወይም በኢትዮጵያ እና በዲያስፖራ ወይም እንደ ኬንያ ባሉ ጎረቤት ሀገሮች መካከል በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም መካከል ስላለው ልዩነት መጠየቅ ይፈልጉ ይሆናል::

☐ ቡድኑን በሁለቱም ሚዲያዎች ላይ ያሉ የጥላቻ ንግግር ምሳሌዎችን እነዲሰጡ ይጠይቁ፡፡

☐ በባህላዊ እና ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ግጭት ለመፍጠር ጥቅም ላይ ስለዋሉ አሳሳች ምስሎች እና ሐሰተኛ መረጃዎች ዉይይት ውስጥ ያካቱ፡፡ይህ በየተዛባ መረጃ እና ማረጋገጫ ምዕራፍ ውስጥ ይመረመራል፡፡

ማረጋገጫ ዝርዝር - በመጨረሻ እነዚህን ይሰብስቡ እና ለሁሉም ቡድን ያጋሩ

☑ የተሟላ አቴንዳንስ ወረቀት

☑ የተሟላ የትራንስፖርት ክፍያ ወረቀት (አስፈላጊ ከሆነ)

☑ የተሟላ የግብረመልስ ጥናት ቅፅ

☑ የተሟላ ሪፖርት ቅፅ

☑ ፎቶዎች/ ቪዲዮዎች (ፎቶ እንሺ መኖሩን ያረጋግጡ)

☑ ፍሊፐቻርት ላይ የተፃፉ ወይም የሚጣበቁ ማስታወሻዎች ላይ የተፃፉ ማስታወሻዎች ፎቶግራፍ ማንሳት እና በፅሁፍ መገልበጥ አለባቸው

☑ የተሰበሰቡ የቡድን ዉይይት ማስታወሻዎች

☑ ከተሳታፊዎች በድምፅ የተቀዱ አስተያየቶች

3, 2, 1 (የግብረ መልስ ክፍለ ግዜ)

ይህ ክፍለ ግዜ በመጀመርያዉ የስልጠና ቀን ሲጠናቀቅ የሚጠይቁበት የግብረ መልስ ክፍለ ግዜ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ የተማሯቸውን ሶስት(3) ነገሮች ፣ ሁለት(2) በስራቸው ወይም በሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች እና አሁንም ጥያቄ የሆነባቸዉን አንድ(1) ነገር በተሰጣቸዉ ወረቀት እነዲፅፉ ይጠየቃሉ፡፡

1. **ዛሬ የተማርካቸዉን/ሻቸዉን ሶስት ነግሮች ጥቀስ/ሽ**
2. **በግል ወይም በሙያዊ ሕይወትዎ ውስጥ የትኞቹን ሁለት ነገሮች በእርግጠኝነት ይጠቀሙባቸዋል**
3. **የስልጠናውን የመጀመርያ ቀን ከተካፈሉ በኋላ አሁንም ያለዎትን አንድ ጥያቄ ይፃፉ**

☐ አሰልጣኙ ተሳታፊዎች ስማቸዉን ሳይገልፁ የፃፉአቸዉን አስተያየቶች ይሰበስባል፡፡

☐ እባክዎን ሁሉንም ወረቀቶች የአሰልጣኞች ገለፃ ላይ ያንብቡ።

☐ የሁለተኛ ቀን ዋናውን ፕሮግራም ከመጀመርዎ በፊት ፣ ክለሳ ሲያደርጉ ጥያቄዎቻቸውን ይመልሱ፡፡

ማስታወሻ:

2

የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚድያ



#defyhatenow | 2 ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚድያ

ሰላም ግንባታ እና ማህበራዊ ሚድያ

የማኅበራዊ ሚዲያ ስትራቴጂ እንዴት ይኖሮዎታል?

ለአመቻቾች ጠቃሚ ምክሮች

ጠንካራ የማኅበራዊ ሚዲያ ግብይት ስትራቴጂ መፍጠር ሳምንታት መውሰድ አያስፈልገውም። ሶስት ቁልፍ ነገሮች በወረቀት ላይ ካሰፈሩ ይበቃል።

1. ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለነዉ ለምንድነዉ?

ማህበራዊ ሚድያዎች ላይ ለመገኘት ያህል ብቻ በማህበራዊ ሚዲያ ሰርጦች ላይ ንቁ መሆን ጠቃሚ ጊዜን እና ሀብቶችን ለማቃጠል በጣም ፈጣን ከሆኑ መንገዶች አንዱ ነው። በመጀመሪያ ንግድዎ "ለምን" ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተገኘ እና ምን ማከናወን ነው የሚፈልጉት ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ይስጡ።

2. እንዴት ስኬታማ እንሆናለን?

ቀጣዩ ጥያቄ "እንዴት" ነዉ። የተወሰኑ ማህበራዊ ሰርጦች ሊሆኑ ይችላሉ ፣ የተከፈለ የማስታወቂያ ፣ በጀት ቪዲዮ ወይም ምስል መፍጠር ከተፅእኖ ፈጣሪዎች ጋር በአጋርነት መስራት።

3. ስኬታችንን እንዴት እንመዝናለን?

ሊያሳኩዋቸዉ የሚፈልጓቸውን ግቦች በቀናት ፣ በሳምንታት ፣ በወራት እና በዓመት ከፋፍሎ ማስቀመጥ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲያተኩሩ እንዲሁም ትልቁን ግብ በአዕምሮ ውስጥ እንዲያስቀምጡ ያስችልዎታል።

ከጎላ ድምፅ ጋር መወዳደር

ድርጅቶች ማህበራዊ ሚዲያ ላይ መገኘት እየቀጠሉ ሲሄዱ ተጠቃሚዎች ብዙ አማራጮችን እያገኙ ነዉ፡፡ የማህበራዊ ሚድያ አደባባዮች እየተጨናነቁ ነዉ፤ እያንዳንዱም የራሱን አሻራ ማሳረፍ ይፈልጋል፡፡ ፉክክሩ ፊት ለፊት ላይ መቆየት እና ጎልቶ መታየት ከመቼዉም በላይ ከባድ ነዉ፡፡

ለተወሰኑ የንግድ ምልክት መለያዎች ጎልቶ ለመታየት ቀላል አቋራጭ ዘዴ የበለጠ መለጠፍ ነዉ፡፡ ምንም እንኳን ይህ ስነ ዘዴ ለአንዳንዶቹ ሊሠራ ቢችልም ፣ ለብዙዎች ተከታዮቻቸዉን የማበሳጨት አዝማሚያ አለው፤ በተለይ የልጥፉ ይዘት ጥልቀት ከሌለው፡፡ ብዙ በለጠፈ ሳይሆን ጥሩ ይዘት ሲለጥፉ ከጊዜ በኋላ ሰዎች ምርትዎን ይከታተላሉ፡፡

ማህበራዊ ሚድያን ለማስተዳደር በቂ ግዜ አለማግኘት

የማህበራዊ ሚድያ ገፅን በየግዜዉ ላለማሻሻል በተደጋጋሚ የሚቀርብ ምክንያት ግዜ ማጣት ነዉ፡፡

ጀማሪ ድርጅት ሆነም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፤ ብዙ የስራ ጫና ይኖራል፤ ከፕሮጀክት ዘመቻዎች ጀምሮ እስከ በመስመር ላይ ታይነትዎን ለማሳደግ እና ለመከታተል፤ እንዲሁም በሠራተኞች ቁጥር አነስተኛ መሆን ምክንያት፣ ለማህበራዊ ሚዲያ ስትራቴጂ በቂ ጊዜ አይኖርም። ይህንን ጫና ለማቃለል እንዲረዳ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፤

ማህበራዊ ሚድያ አስተዳዳሪ መቅጠር

ማህበራዊ ሚዲያ አስተዳደሩን ተመሳሳይ ወይም ሚዛመዱ ሥራዎችን የመስራት ልምድ ላለው ለሚታወቅ ኤጀንሲ መስጠት ወይም በቢሮዎ ውስጥ ማህበራዊ ሚዲያ አስተዳዳሪ መቅጠር ይችላሉ፡፡ የትርፍ ሰዓት ማህበራዊ ሚድያ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከማህበራዊ ሚዲያ-ግብይት ኤጀንሲ መቅጠርን ያስቡ ፡፡

ማህበራዊ ሚዲያዎችን ለማስተዳደር አንድ ሰዓት ይመድቡ

እንደ ሆትሱት እና በፈር (Hootsuite and Buffer) ያሉ ማህበራዊ ሚዲያ ማስተዳደተርያ መሳርያዎች ልጥፎችዎን በበርካታ አውታረመረቦች ላይ የጊዜ ሰሌዳ እንዲያዘጋጁ ይረዳዎታል። የማህበራዊ ሚድያ ገፅዎን በመከታተል እርስዎም በኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉ ልምዶችን ለማወቅ ይረዳዎታል። በመጀመሪያ ስለድርጅትዎ አስተያየቶችን ያዳምጡ እና በቀጥታ ከዒላማ ታዳሚዎች (Target audience) ጋር ይወያዩ፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች ላይ ስለ ድርጅቱ አፈፃፀም የትንታኔ ዘገባዎችን ያቀርባሉ፡፡

በጣም ውጤታማ የሆኑትን የማህበራዊ ሚድያዎች ይምረጡ

ሚፈልጉአቸዉን ታዳሚዎች ለመድረስ በጣም ውጤታማ የሆኑ ሁለት ወይም ሶስት ማህበራዊ ሚድያዎችን ብቻ ይጠቀሙ፡፡ ሚፈልጉአቸዉ ታዳሚዎች ሚጠቀሙአቸዉን ማህበራዊ ሚድያዎች ያጥኑ፣ በዛ መሰረትም አንድ በዋናነት መሪ ሀሳቦን ለመግለፅ ሚጠቀሙበትን ማህበራዊ ሚድያ ይምረጡ፤ ሌሎቹን እንደ ተጨማሪ ይጠቀሙአቸዉ፡፡

ስትራቴጂ ይንደፉ

የማኅበራዊ ሚዲያ ጥረቶችዎን ለማስተካከል ተፎካካሪዎቾ የሚጠቀሙዋቸዉ ስትራቴጂዎች ከመጠቀም ይልቅ፤ የራስዎን ጠቃሚ እና እስፈላጊ ስትራቴጂዎችን ይንደፉ፡፡ የተግባቦት ግቦችዎን ያዘጋጁ፣ የባለሙያ ዕውቀትን ያክሉ፣ ከዚያም ስትራቴጂ ይቅረፁ።

ጥላቻን ማቆም - ትሮሎችን (TROLLS) ያስወጡአቸዉ

በሚዲያ ዳይቨርስቲ ኢንስቲትዩት ለጥላቻ ንግግር እንዴት በቲውተር ላይ ምላሽ መስጠት እንደምንችል የተዘጋጀ መመሪያ።

አይሳደቡ

- ☐ የእርስዎ ቃላት እና የሚያጋሯቸው ማናቸውም ይዘቶች ኅጠኝነትን፣ ጅምላ ፍረጃን፣ ወይም ጥላቻን እንደማያሰራጩ ወይም ህገ-ወጥ ይዘት እንደሌላቸው ያረጋግጡ።

ጥላቻቸዉን አያሰራጩ

- ☐ ጥቂት ተከታዮች ላሉአቸዉ ለአፈንጋጭ ግለሰቦች ትኩረት መስጠት ውጤት ላያስገኝ ይችላል፡፡ የሚመኙትን ትኩረት እና ዝና ልትሰጣቸው ትችላለህ።

በፍጥነት ይመልሱ

- ☐ ግዜ ላለፈበት መመለስ ውይይቶችን እንደገና በመቀስቀስ እና የጥላቻ ንግግሮችን ከዚህ በፊት ላላዩ በማዳረስ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ጊዜ ወሳኝነት አለው።

ስለ ዓላማዎ ያስቡ

- ☐ የጥላቻ ንግግር ከሚናገር ሰው ጋር ለመሳተፍ ይፈልጋሉ? ለምን?
- ☐ በተጠቃሚዎች ላይ የጥላቻ ትዊት ውጤቶችን ለመቀነስ ይፈልጋሉ?
- ☐ በጥቃት ላይ ለሆነ ቡድን ወይም ማንነት ድጋፍ ለመስጠት ይፈልጋሉ?
- ☐ ግቦትን ማሰብ ምላሾትን እና የሚጠቀሙትን ቋንቋ ለመምረጥ ይርዳዎታል።

ተፅእኖ ፈጣሪ ደጋፊዎችን ለመመዝገብ ይሞክሩ

- ☐ ታዋቂ ሰዎች፣ ፖለቲከኞች፣ የሲቪክ መሪዎች ለእርሶ ተቃራኒ ትርክት፣ ትኩረት እና ክብደት ለማምጣት ይረዳሉ። ስለዚ ስማቸዉን ትዊት ዉስጥ ይጨምሩ።

የነበሩ ሀሽታጎች ላይ ይሳተፉ

- ☐ ይህ መልስ ከፃፉለት ግለሰብ በላይ መልዕክቶ ሚታይበትን እድል ይጨምራል። የአሉታዊ ሀሽታግ ዉይይቶችን ቃና ለመቀየርም ሊረዳዎ ይችላል። በተጨማሪም ሌሎች ዝም እንዳይሉ እና እነሱም እንዲቀላቀሉ ይረዳቸዉ ይሆናል።

አዲስ ሀሽታጎችን ያስተዋዉቁ

- ☐ ከጥላቻ ንግግሮች ጋር ከተያያዙት ጎን ለጎን አዲስ ሀሽታጎችን ያስተዋዉቁ። ይህ ቃናውን ወደ አዎንታዊ እና አካታች አቅጣጫ እንዲቀይር እና ሌሎች ለመቀላቀል ምቾት የሚሰማቸው ቦታም እንዲሰማቸው ያበረታታል፡፡

ትርክት ይገንቡ

- ☐ በጊዜ ሂደት ትርክት ይገንቡ፡፡ ተቃራኒ ትርክትን እንደ ረዥም ግዜ ሂደት ይመልከቱ።
- ☐ የእርሶን መገለጫዎች እና ብዙዎችን የማሳተፍ አቅምዎን ለማሳደግ በወጥነት ይለጥፉ፡፡
- ☐ አላማዎ የሆነን ሰዉ አመለካከት ለመቀየር ከሆነ ምልልስ ያለበት ዉይይት ዉስጥ ለመሳተፍ ይዘጋጁ፡፡ ነገር ግን አሳሳቾችን እንዳያበረታቱ ይጠንቀቁ፤ እነሱ የሚፈልጉት ይህን ነዉና፡፡
- ☐ የመርጃ ባንክ ለተቃራኒ ትርክቶችን መልስ ለመስጠት ማዘጋጀት። ለምሳሌ፤ ስታቲስቲክስ፣ መረጃዎች፣ ሊንኮች የመሳሰሉትን፡፡
- ☐ ስለርዕሰ ጉዳዩ እውቀት አስፈላጊ ነው፡፡ በጥላቻ ንግግር ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ብዙ አሳሳች የመረጃ ምንጮችን የታጠቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ☐ በአድልዎ ሊከሰስ በማይችል ገለልተኛ እና መልካም ስም ካለው ምንጭ በሚመነጭ ማስረጃ ተቃወሙአቸዉ።

ምስል ይጠቀሙ

- ☐ ምስሎች፤ በጥንቃቄ የተመረጡ ምስሎች እና ቪዲዎች፣ በመልእክትዎ ፍላጎትን እና ተሳትፎን ለማስነሳት ይርዱ።

ሙሉ መምርያዉን እዚህ ያዉርዱ፡ //www.getthetrollsout.org/

ማስታወሻ:

3

የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ማህበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ

#defyhatenow | 3 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ማህበራዊ ሚዲያ ግንዛቤ

ስነ ዘዴ ፣ #DEFYHATENOW

የበይነመረብ የተሳሳተ መረጃ እና ጥላቻ ንግግር የክትትል ሪፖርት
#እዉነታዎችዋጋአላቸዉ ፌሎሺፕ (#FACTSMATTER)

የሪፖርቱ ዋና ክፍሎች

- የሪፖርቱ ርዕስ
- የክትትል ግዜ
- ፀሀፊ
- ዋቢዎች እና ሊንኮች

መግብያ

- ከክትትሉ ዉጤት ዋና ሀሳቡን ይለዩ

የሪፖርቱ አካል

- ጥቃቶች እንደ አስፈላጊነቱ በቅደም ተከተል
- ጥቃት ስንል ፥ የቡድን፣ የብሄር ፣ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ጾታዊ... ወዘተ
- በቡድን መተንተን ፣ ማጠቃለያ እና ምሳሌ

ማጠቃለያ

- በምልከታዉ ክትትል ጊዜ የተገኘ አጠቃላይ ሀሳብ ማጠቃለያ እና ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶችን መተንተን።

ምክረ ሀሳብ

- እዚህ ይህንን ችግር በብቃት ለመታገል በክትትል ወቅት ላይ በተመለከቱት መሰረት አርታኢዎች ምን እንደሚመክሩ ልብ ይበሉ።

አባሪ

- ማህበራዊ ሚድያ ታሪኮች እና ልጥፎች ለማስረዳት የተወሰኑ ቅጽበታዊ ገጽ እይታዎችን (screenshots) ማካተት፡፡
- የቃላት መፍቻ፣ በጥናቱ ወቅት በጣም ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት እና ምህፃረ ቃላት፡፡

መልመጃ

የተሳሳተ መረጃ እና የተዛባ መረጃ እንዴት ይለያል

☐ ሐሰት ሊሆን ሚችል ምን ታሪክ እና አሉባልታ ሰምተዋል?

☐ ከየት ነዉ የሰሙዋቸዉ፥ በማህበራዊ ሚድያ፣ በአካል፣ በስልክ፣ በባህላዊ ሚድያ ሪፖርት ተደርገዉ (ዜና ሳይቶቸች፣ ሬድዮ፣ ቲቪ)?

☐ ታሪኩ እዉነት ወይም ሐሰት እንደሆነ እንዴት ወሰኑ?

☐ ታሪኩ ፕሮፖጋንዳ ነበር? ከሆነስ በማን እንደሆነ መለየት ይችላሉ?

☐ ማንን ይጠቅማል? ማንን ይጎዳል?

☐ የተቀበሉትን መረጃ እዉነትነት ለማረጋገጥ ምን አይነት መሳርያዎች አሉት?

☐ የተሳሳቱ መረጃዎች፣ የተጭበረበሩ ታሪኮች እና አሉባልታዎች በእርሶ ላይ እና ማህበረሰብ ላይ እንዴት ተፅእኖ አደረጉ?

☐ ለሆነ ዓላማ የተዘጋጁ ፕሮፖጋንዳ ሊሆኑ ሚችሉ ታሪኮችን ያዉቃሉ?

☐ ምንጮቹ እነማን እንደሆኑ እና አላማቸዉ ምን እንደሆነ እንዴት ይለያሉ?

አፍሪካ ቼክ - ጠቃሚ ምክሮች

☐ በቅርቡ በማህበራዊ ሚድያ ሲጋራ ያዩትን ዜና ወይም አሉባልታ ይለዩ፡፡

☐ የሚከተሉትን መሳርያዎች በመጠቀም ማስረጃ እና የመጀመርያ ምንጩን ለማግኘት ይሞክሩ፡፡

☐ እዉነታዎችን መፈተሽ አይዘንጉ፡፡ ሁሉንም ጥያቄዎች ከሌሎች ምንጮች ያጣሩ፡፡

ሁሉም ሰዉ የሀሰተኛ ዜናን፣ አሉባልታን እና ፕሮፖጋንዳ ለማቆም ማገዝ ይችላል!

አፍሪካ ቼክ
እዉነታን ከልብወለድ መለየት
www.AfricaCheck.org

መረጃ ፈላጊ (INFO FINDER)
የሚነሳ ጥያቄን መፈተሽ ከባድ ሚያደርገዉ ተአማኒ የሆነ መፈተሻ መረጃ ማግኘት ነዉ፡፡ ይሄን እንዲያደርጉ ልንረዳዎ ይህንን ጥናት ስናካሄድ የተጠቀምንባቸዉን ምንጮች የመረጃ ቋት አዘጋጅተናል፡፡
https://africacheck.org/infofinder/#/

1. ፍላጉት ያሎትን ቦታ ይምረጡ

☐ መረጃ ሚፈልጉበት ሀገር ይምረጡ (አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ)

2. ፍላጎት ያሎትን ርዕስ ይምረጡ

☐ የርዕስ ዝርዝሮችን ይምረጡ፡፡

☐ ፍላጎት ስላሎት ርዕስ መረጃ ከሌለን ርዕሱን info@africacheck.org በዚህ አድራሻ ይጠቁሙን፡፡ ለሁሉም መልዕክቶች መመለስ አንችልም ነገር ግን ሁሉንም እናነባቸዋለን፡፡

የሚድያ አድሎ/እዉነታ ቼክ ክሮም ኤክስቴንሽን
ጉግል ክሮም ኤክስቴንሽ የገፆች ፖለቲካዊ መድሎ ምልክትን ያሳያል።
https://mediabiasfactcheck.com/

አጠራጣሪ ምስሎችን ተገላቢጦሽ ምስል ፍለጋ በማድረግ ያረጋግጡ፣ ወይም ከሚከተሉት አንዱን ይሞክሩ፣

ምስሎቼን ማን ሰረቀ?
https://addons.mozilla.org/en-US/firefox/addon/who-stole-my-pictures/

ቤሊንግካት ምስል ማረጋገጫ መድረክ
https://www.bellingcat.com/

ቤሊንግካት ሪፖርት የተደረጉ ክስተቶችን ያጠናል እያንዳንዱን ፎቶ፣ ቪዲዮ እና የእኛን ትንታኔ ለማሳወቅ የምስክር መለያን ያረጋግጣል።

ቤሊንግካት በይነመረብ ምርመራ አፍሪካ
https://www.bellingcat.com/category/news/africa/

ምስል መጫን እንደሚችሉ ያስታዉሱ ፣ የካሜራዉን ምልክት ይጫኑ ወይም በ URL ይፈልጉ

ተገላቢጦሽ ምስሎችን በሞባይል፣ በታብሌት ወይም በአንድሮይድ መተግበርያ ይጠቀሙ።
https://images.google.com/
https://reverse.photos/
https://tineye.com/

© Copyright Africa Check 2020
ሪፖርቱ በአፍሪካ ቼክ ወገንተኛ ያልሆነ አዉነታ አጣሪ ድርጅት ነዉ የተፃፈዉ።

ዋናዉን ከድረገፃቸዉ ይመልከቱ፥
https://africacheck.org/factsheets/guide-how-to-spot-fakes-and-hoaxes-online/

ማስታወሻ:

4

የሚታደሉ
የመልመጃ ወረቀቶች
እና መልመጃዎች

ሲቪል ማህበረሰብ
እና ማህበራዊ ሚድያ

#defyhatenow | 4 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ሲቪል ማህበረሰብ እና ማህበራዊ ሚድያ

ስነምግባር ያለዉ ጋዜጠኝነት

ለመቻቻል የማረጋገጫ ዝርዝር

1. የጥላቻ ንግግር ሊያካትቱ ታሪኮችን በሚመለከቱበት ጊዜ ስሜት ቀስቃሽ አለመሆን በጣም አስፈላጊ ነው፥

- ☐ ስነምግባር ያለዉ ጋዜጠኛ እነዚህን ይጠይቃል፥
- ☐ ቀልብ ሚይዝ ሊሆን ችላል ነገርግን ለዜናነት ይመጥናል?
- ☐ የተናጋሪዉ አላማ ምንድነዉ?
- ☐ የእትሙ ተፅእኖ ምን ይሆናል?
- ☐ ስሜትን የማቀጣጠል እና ወደ አመፅ ማነሳሳት አደጋ አለ?
- ☐ ንግግሩ እዉነታ ላይ የተመሰረተ ነዉ? እና ጥያቄዎቹ ተጣርተዋል?

2. አወዛጋቢ ማቴሪሎችን በማሰባሰብ እና በማረም ግዜ ጋዜጠኞች ለማተም መቸኮልን ማስወገድ አለባቸዉ። የታሪኩን ይዘት ለመመልከት ለአፍታም ቢሆን ማቆም ቆም ብሎ ማሰብ ጠቃሚ ነዉ ፥

- ☐ አላስፈላጊ አሉባልታዎችን እና የተሳሳተ አመለካከት አስወግደናል?
- ☐ ሁሉንም አስፈላጊ እና ጠቃሚ ጥያቄዎች ጠይቀናል?
- ☐ ለታዳሚዎቻችን ጥንቃቄ አድርገናል?
- ☐ በቋንቋ አጠቃቀም መለስተኛ ሆነናል?
- ☐ ምስሎቹ ወደ ጥቃት እና በሌሎች ስቃይ ወደመደሰት ሳይወስዱ ታሪኩን ይነግራሉ?
- ☐ የተለያዩ ምንጮችን ተጠቅመናል እንዲሁም የሚመለከታቸዉን በቁጥር አናሳ ቡድኖችን ድምፅ አካተናል?
- ☐ በኤዲቶሪያል እና በሥነ ምግባር ደንቦች የተቀመጡትን ደረጃዎች ያሟላል?

3. ሁል ጊዜ ለማተም ከመጫኖ በፊት አንድ የመጨረሻ እይታ እና የማሰብያ ጊዜ መዉሰድ ጠቃሚ ነው፥

- ☐ ጥሩ ስራ ነዉ የሰራነዉ?
- ☐ የሚረብሹ ጥርጣሬዎች አሉ?
- ☐ እና በመጨረሻም ባልደረባዬን መጠየቅ አለብኝን?

የጋዜጠኝነት ሥነምግባር አውታረመረብ (Ethical Journalism Network)
https://ethicaljournalismnetwork.org/

ማስታወሻ:

5

የሚታደሉ
የመልመጃ ወረቀቶች
እና መልመጃዎች

ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ

#defyhatenow | 5 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ሰላም ግንባታ እና ቴክኖሎጂ

#ከመጫኖበፊትያስቡ #THINKB4UCLICK የማህበራዊ ሚድያ ዘመቻ ያዘጋጁ

#ከመጫኖበፊትያስቡ (#ThinkB4UClick) የተሳሳተ መረጃ ፣ ሐሰተኛ ዜና እና የጥላቻ ንግግር አደገኛነት ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር በ#defyhatenow የሚመራ የግንዛቤ ዘመቻ ነዉ፡፡ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ #defyhatenow እና አጋሮች ህብረተሰቡን ስለጥላቻ ንግግሮች እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የበይነመረብ እና በገሀዱ አለም ቦታዎች ለዜጎች ለመፍጠር የጥላቻ ንግግር እንዴት በግለሰባዊ እርምጃዎች እንደሚቀነሱ ያስተምራል፤ እንዲሁም ዜጎች እርስ በእርስ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጤናማ እና በእውቀት ላይ በተመሰረቱ መልኩ እንዲወያዩ ያደርጋል፡፡

አላማዎች

- ☐ የተሳሳተ መረጃ፣ ሐሰተኛ ዜናዎች እና የጥላቻ ንግግሮች አደገኛነት ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ግንዛቤ መፍጠር፡፡
- ☐ ዜጎች ጥላቻን ለመቃወም አነስተኛ ግን ጉልህ እርምጃዎችን እንዲወስዱ እና በበይነመረብ ላይ የተሳሳተ መረጃን ከማጋራት እንዲቆጠቡ ያበረታቱ፡፡

ኢላማ ያደረገዉ ታዳሚ

- ☐ በኢትዮጵያ የሚሰሩ የሚድያ ድርጅቶች።
- ☐ በኢትዮጵያ የህዝብ አመለካከት ቀራጮች እና ተጽዕኖ ፈጣሪዎቹ።
- ☐ ሀገር ዉስጥም፣ በዉጪም ያሉ ኢትዮጵያዉያን።
- ☐ የኢትዮጵያ በይነመረብ ማህበረሰቦች፣ ፌስቡክ ግሩፖች እና ማህበራዊ ሚድያ ተጠቃሚዎች።
- ☐ የተፈናቀሉ እና ስደተኛ ኢትዮጵያዉያን።

ሳምንታዊ ጭብጦች

ዘመቻዉ በሳምንታዊ መልዕክቶች የተከፋፈሉ አራት ጭብጦች አሉት፥

ሳምንት 1

ምንጩን ይፈትሹ እና መረጃውን ያረጋግጡ፡፡

ሳምንት 2

ሐሰት በፍጥነት ሩቅ ይጓዛል፤ እርማቶች እና ይቅርታዎች ግን ቶሎ ወደ ህዝብ አይደርሱም፡፡

- ☐ አለም በሙሉ የሚለጥፉትን እየሰማ ነዉ፡፡ እባክዎ ዉሸት እና የተሳሳተ መረጃ አያጋሩ፡፡ በአንድ እርማት የሰሩትን ስህተት በሙሉ ማስተካከል አይችሉም፡፡

ሳምንት 3
የአዉድ አስፈላጊነት

☐ ምላሽ ከመስጠትዎ በፊት አውድ ይኑርዎ፡፡

☐ ከአዉድ ዉጪ የሆነ መረጃ ብዙ ሰዎችን የማሳሳት አቅም አለዉ፡፡

ሳምንት 4
ትንንሽ እርምጃዎች ዋጋ አላቸዉ፣ ትልቅ ተፅእኖ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡

☐ #ከመጫኖበፊትያስቡ (#ThinkB4UClick) የሚለው ጭብጥ ለእርምጃ የተደረገ ጥሪ ነው ፤ይህም ዜጎች የጥላቻ ንግግሮችን እና አመፅ ማነሳሳትን ለመቀነስ አነስተኛ እርምጃዎች እንዲወስዱ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡

☐ በነዚህ ጉዳዮች ላይ በቤት፣ በትምህርት ቤት እና ስራ ቦታዎች ብዙ ዉይይቶች ያስፈልጉናል፡፡

☐ እያንዳንዱ ግለሰብ ማህበራዊ ሚድያን በህላፊነት የመጠቀም እና የጥላቻ ንግግሮችን እና ሐሰተኛ መረጃዎችን በይነመረብ ሪፖርት ማድረግያ ስነ ዘዴ ዎችን የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

☐ #ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ እንድትኖረን እንስራ፡፡ #HateFreeEthiopia

ደህንነት እና ግላዊ ሚስጥር

የእራስዎን ደህንነትን በገሐዱ አለም እንደሚጠብቁ ሁሉ፤ በዲጂታልም አለምም እራስዎን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ዲጂታል ደህንነትን መማር ከመጠን በላይ ከባድ ነገር እንደሆነ ሊሰማዎ ይችላል ነገርግን ደህንነትን እንደ አንድ የሚለማመዱት ነገር አርገን ማሰብ፤ እያንዳንዱን ሁኔታ እንዴት መገምገም እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እርምጃ እንደምንወስድ ለማወቅ ይረዳናል፡፡

ራስዎን የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች፥

- ምን መከላከል እፈልጋለሁ?
- ከማን ነዉ መከላከል ምፈልገዉ?
- የእኔን የግላዊነትን ሚስጥር ለማግኘት ምን ማድረግ ይችላሉ?
- ከተሳካላቸዉ ምን ይፈጠራል?
- ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮች ለመከላከል ምን ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ?

የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ የመረዳት ሂደት የስጋት ሞዴሊንግ ይባላል፡፡ ይህ **የስጋት ሞዴሊንግ** የደህንነት እቅድ እንዲያዘጋጁ ይረዳዎታል፡፡

ምን መከለከል እፈልጋለሁ?

ከጥቃት መከላከል/መጠበቅ የሚፈልጉት ንብረት ይባላል፤ ይህም ብዙውን ጊዜ መረጃ ወይም የዲጂታል መሣሪያ ነው።

- የበይነመረብ ማንነቴን
- ያለሁበትን አካባቢ
- በኮምፒዉተሬ ላይ የተጫኑ ዳታዎች
- በምጓዝበት ጊዜ የዲጂታል መሣሪያዎቼን
- ይለፍ ቃሎቼን
- የአድራሻዎቼን ዝርዝር
- ከሌሎች ጋር ያለኝን ግንኙነት
- የምንጮቼን ማንነት
- የማህበራዊ ሚድያ አካዉንቶቼን
- የኢሜል አካዉንቶቼን
- በስራ ቦታዬ ያሉ ሰዎች

ከማን ነዉ መከለከል የምፈልገዉ?

እርስዎን ወይም መረጃዎን ኢላማ ማድረግ ሚፈልጉ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች እንደ ጠላት/ ተቃዋሚ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

- መንግስት
- የዉጭ ሀገር መንግስታት
- የበይነመረብ አገልግሎት አቅራቢዎች
- የሳይበር ወንጀለኞችን
- የሀገሬ ተፅእኖ ፈጣሪ ፖለቲከኞች
- የሀገሬ ተፅእኖ ፈጣሪ የቢዝነስ ሰዎች
- የሀገሬ ሀይማኖት መሪዎች
- ሽብርተኛ ድርጅቶች

የእኔን የግላዊነት ሚስጥር ለማግኘት ምን ማድረግ ይችላሉ?

- **አካላዊ ጥቃት፥** የሆነ ሰዉ ኮምፒተርዎን ሊሰርቅ ይችላል ወይም የደህንነት ሀይሎች የእጅ ስልኮትን ሊወስድቦት ይችላሉ፡፡
- **ማህበራዊ ጥቃት፥** የሆነ ሰዉ መለያዎቾን ሊያጠምድ ይችላል ወይም ከባልደረባዎ የይለፍ ቃሎን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
- **ህጋዊ ጥቃት፥** ሶስተኛ ወገን መረጃ እንዲያወጣ ማስገደድ ወይም የእርስዎ ምንጭ ሊታሰር ይችላል፡፡
- **ቴክኒካዊ ጥቃት፥** ሀክ ማድረግ፣ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሶፍትዌሮችን መጫን፣ የኤልክትሮኒክ ግንኙነቶችን መጥለፍ ወይም ኮዶችን መጣስ፡፡

ተግባር ተኮር ጥናት

የሶርያ መንግስት የተወሳሰቡ ጥቃቶች፥
https://www.eff.org/deeplinks/2011/05/syrian-man-middle-against-facebook

ፊልም ሰሪ እንዴት በአጋጣሚ ምንጮቹን ሰጠ፥
https://archives.cjr.org/feature/the_spy_who_came_in_from_the_c.php

ምን ያህል የመሞከር ዕድላቸው አላቸው?

ሁሉም ስጋቶች እዉነት ሊሆኑ አይችሉም ፣ እናም ከመጠን በላይ ሳይጨናነቁ ሊሆን ሚችለውን እና ሚሆነውን መለየት ጥሩ ነው፡፡ የተለያዩ አይነት “ጥቃቶች” እንዴት እንደሚከሰቱ ካወቁ ለአንዳንድ አደጋ የመጋለጥ እድልዎ አነስተኛ ነው። ስለዚህም ሌሎች ጥቃቶችንም እንዴት መቀነስ እንደሚቻል የበለጠ ያውቃሉ።

ከተሳካላቸዉ ምን ይፈጠራል?

አንድ ሰው መረጃን ወይም ሊጠብቁት የሚሞክሩትን መሣሪያ ማግኘት ከቻለ ሊፈጠር የሚችለውን በጣም የከፋ ነገር ግምት ውስጥ ማስገባት ጥሩ ነው፡፡

ሊከሰቱ የሚችሉትን ነገሮች ለመከላከል ምን ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ?

የደህንነት እርምጃዎች ጊዜ እና ገንዘብ የሚወስዱ ናቸው፤ ብዙ ጊዜም አመቺ አይደሉም፡፡ በጣም አስቸጋሪ፣ በጣም ቴክኒካዊ ወይም በጣም ውድ ከሆኑ፣ መደረግ ያለባቸዉ እርምጃዎች ላይደረጉ ወይንም ወጥነት በሌለው መልኩ ሊደረጉ ይችላል፡፡ ይህ ደሞ ለአደጋ ያጋልጥዎታል፡፡

ኤሌክትሮኒክ ፍሮንትየር ፋውንዴሽን ከግምት ውስጥ ልናስገባቸዉ ሚገቡ ሰባት ዋና የዲጂታል ደህንነት ፅንሰ ሀሳቦችን ይገልጻል፥
https://ssd.eff.org/en/module/seven-steps-digital-security

የደህንነት መሠረታዊ ነገሮች

ጥሩ የይለፍ ቃል ይምረጡ

ጥሩ ጠንካራ የይለፍ ቃል በሌሎች ለመገመት አስቸጋሪ እና ለእርስዎ ለማስታወስ ቀላል የሆነ ነው። የይለፍ ሐረጎች ከስድስት በላይ የዘፈቀደ ቃላት ስብስብ እና የማይረሳ የይለፍ ቃል ለማድረግ ጥሩ ዘዴዎች ናቸው፡፡

እነዚህን ያረጋግጡ፥

- የልደትዎ ቀን ወይም የዉሻዎ ስም አይነት የግል መረጃዎትን አይጠቀሙ
- በሚስጥር ይጠብቁት
- ለእያንዳንዱ አካዉንትዎ የተለያየ ያድርጉ
- ለማስታወስ ቀላል ያድርጉት
- ባለ ሁለት ደረጃ ማረጋገጫ ይጠቀሙ
- ዋትሳፕ ኢሜል ጨምሮ ለሁሉም ማህበራዊ ሚድያ አካዉንቶችዎት እና ኢሜልዎ ባለ ሁለት ደረጃ ማረጋገጫዉን ያብሩት፡፡
- የይለፍ ቃል ማስተዳደርያ ይጠቀሙ

ብዙ የይለፍ ቃሎችን ማስተዳርያ አንዱ መንገድ ደህንታቸዉ የተጠበቁ እንደ KeePassXC: **https://keepassxc.org/** ያሉ የይለፍ ቃል ማስተዳደርያ መሳርያዎችን መጠቀም ነዉ፡፡

ሊንኮችን ሲከፍቱ ይጠንቀቁ

በኢሜል ወይም በማህበራዊ ሚድያ በመልክቶች ጨምሮ የሚላኩ ሊንኮችን መክፈት የሚላክልዎትን ሰው ቢያውቁትም እንኳ የማህበራዊ ሚዲያ መለያዎችዎን ለመጠቀም ወይም የክፍያ እና የማንነት መረጃዎችን ለመውሰድ ሊያገለግል ይችላል ፡፡ እራስዎን ከወጥመድ ለመጠበቅ የእኛን የበይነመረብ የደህንነት እና ግላዊ ሚስጥር መመሪያ ይመልከቱ፡፡

አባሪዎችን ሲከፍቱ ይጠንቀቁ

ኢሜል በቀላሉ ሊጭበረበር እና አባሪዎች ተንኮል አዘል ሶፍትዌሮችን ሊይዙ ይችላሉ፡፡

ስልክዎትን ወይም ሀርድ ድራይቭዎን ይቆልፉ

የሆነ ሰው የዲጂታል መሣሪያዎችዎን የሚጠቀም ከሆነ መረጃዎ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደበቀ (encrypt) ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህ ማለት የይለፍ ቃልዎ የሌለው ሰው ሊያነበው አይችልም ማለት ነው።

ደህንነቱ የተጠበቀ መተግበርያ ይጠቀሙ

እንዲሁም ከኔትወርክዎ ጋር ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመገናኘት ከላኪዉ እስከ ተቀባይ የተደበቀ (encrypted) ኢሜል ወይም የመልዕክት መተግበሪያዎች (Chat apps) መጠቀም ይችላሉ፡፡

ቪፒኤን VPN ይጠቀሙ

ያሉበትን አካባቢ ለመጠበቅ አንዱ መንገድ ቪፒኤን (VPN) መጠቀም ነው፡፡

የዲጂታል መሣሪያዎን አካል ደህንነት ይጠብቁ

እርስዎ የሚወስዷቸው ብዙ የደህንነት እርምጃዎች አንድ ሰው የዲጂታል መሳሪያዎን መጠቀም ከቻለ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ መሳሪያዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይጠብቁ፡፡

የእራስዎን ደህንነት ለመጠበቅ ብዙ ተጨማሪ ነገሮች ማድረግ ይችላሉ፡፡ ለበለጠ እርዳታ የበይነመረብ መመርያችንን እና USB Stick [ፍላሽ] ላይ ይመልከቱ፡፡

የበይነመረብ የደህንነት እና ግላዊ ሚስጥር መመሪያ፥
https://defyhatenow.org/security-privacy-basics /

ምንጭ

Electronic Frontier Foundation's Surveillance Self-Defence
https://ssd.eff.org

Jonathan Stray's Security for Journalists, Part One: Basics
https://source.opennews.org/articles/security-journalists-part-one-basics/

Jonathan Stray's Security for Journalists, Part Two: Threat Modeling
https://source.opennews.org/articles/security-journalists-part-two-threat-modeling/

ማስታወሻ:

6

የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ማግኘት እና አውድ

#defyhatenow | 6 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ማንነት እና አዉድ

ሁላችንም የብዙ ቡድኖች አባል ነን

አላማ

ሁላችንም በተለያየ አዉድ ምንገልጠዉ ብዙ ማንነቶች አሉን፡፡ ለብዙዎች ማንነት ዉስብስብ ነዉ፤ ለጥቂቶች ማንነት የግጭት ምንጭ ነዉ፡፡ እንዲሁም ብዙ ግለሰቦች በመደበኛነት እንደ የኀብረተሰቡ አካል ተደርገው በማይወሰዱበት ጊዜ ማንነትን መሠረት ያደረገ ግጭት ይገጥማቸዋል፡፡

ይህ መልመጃ ተሳታፊዎች የማንነታቸውን ብዙ ገፅታዎችን እንዲመለከቱ ይጋብዛል ፣ ያልተለመዱ ገፅታዎችን ጨምሮ፡፡ መልመጃዉ የራስን ግንዛቤ ያዳብራል ፣ ይህም ግለሰቦች ዓለምን እንዴት እንደሚመለከቱ እንዲገነዘቡ ይረዳል፡፡

አላማዎች

- ብዙ ማንነቶቻችንን እንድንመረምር።
- በቡድኑ ውስጥ ተመሳሳይነቶችን እና ልዩነቶችን ለመለየት።
- የግል ልምዶችን በማካፈል እምነት እና ርህራሄ ለመገንባት።

ማቴርያሎች፡ ሁላችንም የብዙ ቡድኖች አባል ነን መልመጃ መስሪያ ወረቀት
ግዜ፡ 90 ደቂቃ
አካሄድ

1. የመልመጃዉን አላማ ያብራሩ፡፡ ለተሳታፊዎች ማንነታቸውን የሚገልጽባቸውን አምስት ቡድኖችን በመምረጥ የመልመጃ መስርያ ወረቀቱን እንደሚያጠናቅቁ ይንገሯቸው፡፡

   ለዚህ መልመጃ ዓላማ ቡድኖች ማለት፥ ዕድሜ ፣ ሃይማኖት ፣ ዘር ፣ ብሔር ፣ ጾታ ፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ መደብ ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ ፣ ሰፈር ፣ ወዘተ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልመጃ ቡድኖች እንደ ጀብደኛ ወይም ወዳጅነት ያሉ የግል ባህሪያትን ማካተት የለባቸውም። ማንነቶች ወጥ እንዳልሆኑ በግዜ ሊለወጡ እንደሚችሉ ያብራሩ፡፡ የአንድ ሰው አሁን ያለዉ ተቀዳሚ ማንነት ከአንድ ወር በሆላ የተለየ ሊሆን ይችላል። እንደ ምሳሌ አሰልጣኝ የእራሱን ማንነት እና ልምድ ሚጋራት አለበት፡፡

2. ለተሳታፊዎች መስርያ ወረቀቱን ስጧቸው ፣ ስማቸውን በማዕከላዊ ክብ ውስጥ እንዲያስቀምጡ እና በአምስቱ ክቦች ውስጥ ማንነታቸውን የሚገልጽባቸውን አምስት ቡድኖችን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ የመልመጃ መስርያ ወረቀቱ ላይ ከሁለት እስከ ሶስት ደቂቃ እንዲሰሩ ይፍቀዱ። ሲጨርሱ እነሱ የሚገኙበትን ከአምስቱ የማንነት ቡድኖች ውስጥ ተቀዳሚ ቡድን እንዲመርጡ እና እንዲያከቡት ያድርጉ፡፡ ተቀዳሚ ቡድን ማለት በአሁኑ ጊዜ ለእነሱ በጣም አስፈላጊ ሆኖ የሚሰማቸዉ ቡድን ነው፡፡

3. በቀጣዩ የመልመጃ ክፍል በመስሪያ ወረቀቱ ታችኛው ክፍል ላይ ባሉት አረፍተ ነገሮች መሰረት ምላሽ በመስጠት በአንዱ ማንነታቸው ያላቸዉን ልምድ እንደሚያካፍሉ ለተሳታፊዎች ይንገሩ፡፡ የተቀዳሚ ቡድንዎ አባል መሆን አስቸጋሪ ወይም ፈታኝ የሆነበትን ጊዜ ያጋራሉ፡፡ ይህንን ስለ ራስዎ ተቀዳሚ ቡድን ጉልህ የሆነ ታሪኮችን በማጋራት ከተሳታፊዎችዎ ጋር መተማመንን ይገንቡ፡፡ የእርስዎ ምሳሌ ተሳታፊዎች ለሚጋሯቸው ልምዶች ስነ ዘዴዉን ያሳያል፡፡ ከአንድ በላይ አሰልጣኞች ካላችሁ እያንዳንዳቹ ማንነቶቻችሁን እና ልምዶቻችሁን ማካፈል አለባችሁ፡፡

4. ተሳታፊዎችን ማንነታቸውን እንዲያካፍሉ በአራት ወይም በአምስት ቡድን ይከፋፍሏቸው፡፡ ቡድኖቻቸው ውስጥ ተሳታፊዎች የማንነት ቡድኖቻቸውን ለምን እንደመረጡ ያካፍሉ፡፡ ከዚያ ተሳታፊዎች ታችኛው ክፍል ላይ ላሉት አረፍተ ነገሮች ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

5. ተሳታፊዎች ልምዳቸዉን ማጋራት ከጨረሱ በኋላ መስርያ ወረቀቶቹን ከቡድኑ ውስጥ ይሰብስቡ፡፡ የተወሰኑ ቡድኖችን አንድ በአንድ እንደሚጠሩ ይንገሯቸው እና የሚጠሩት ቡድን ዉስጥ ሚገኙ ከሆነ እንዲቆሙ እና ከእነሱ ጋር አብረዉ የቆሙትንም ዞረዉ እነዲመለከቱ ይንገርዋቸዉ፡፡ የሚጠሩትን ቡድን በመስርያ ወረቀታቸዉ ላይ ባይጠቅሱትም ሚገኙበት ከሆነ መቆም አለባቸዉ፡፡ ይህ የራስ-ማንነት እንቅስቃሴ መሆኑን እና አንድ ቡድን ሲጠራ ለሌላ ሰዎች መቆም እንዳለባቸዉ እና እንደሌለባቸው መንገር ተገቢ እንዳልሆነ አስታዉሱዋቸዉ፡፡

6. በሰበሰቧቸው የብዙ ቡድኖች አባል ነን መስሪያ ወረቀቶች ላይ ከተዘረዘሩት ማንነቶች አንዳንድ ማንነቶችን ይጥሩ፡፡ ከሚጠሩዋቸው ማንነቶች ጋር የተገናኘ የሰው ስም አለመጥራቶን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ የተላያዩ ማንነትቶችን ለማካተት ይሞክሩ። የሚጠሩዋቸው ማንነቶች ብዛት የሚወሰነው ባሎት ጊዜ ላይ ነው ፣ ግን ብዙውን ጊዜ አስር በቂ ነው።

7. ከሚከተሉት ጥያቄዎች የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም ጥያቄዎች በመጠቀም አንድ የሙሉ ቡድን ውይይት ያካሂዱ፡፡

አካሄድ

☐ መስርያ ወረቀቱን መሙላት እንዴት ነበር? ቀላል/ከባድ ነበር? ለምን?

☐ በቁጭ ብድግ ወቅት ምን ዓይነት ሁኔታዎችን አስተዋልክ/ሽ?

☐ የብዙ ቡድን አካል በነበሩበት ጊዜ መቆም ምን አይነት ስሜት አለዉ?

☐ ብቻዎን ሲሆኑ ወይም በጣም ትንሽ ሆነዉ መቆም ምን ስሜት አለዉ?

☐ ተሳታፊዎች በት/ቤታችን ወይም በኅብረተሰባችን ዉስጥ ብቻቸዉን ቆመዉ ሊሰማቸው የሚችሉበት ሁኔታዎችን ማሰብ ይችላሉ?

☐ አንድ ሰው ብቻውን እንዳልሆነ እንዲሰማው ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላል?

☐ ቅደመ-ፍረጃን ለመፍታት የማንነት ሚና ምንድነው?

ማስታወሻ: ብቻ መቆም ለአንዳንድ ሰዎች ኩራት እና በራስ የመተማመን ስሜት ሊሰጣችው ለሌሎች ደግሞ ደኅንነት ያለማግኘት ወይም ፍርሃት ሊሰማቸው እንደሚችል ለተሳታፊዎች ያስታውሱዋቸዉ፡፡

☐ አንድ ሰው ፍርሃት ሊሰማው የሚችለው ለምንድን ነው?

☐ እነዚያን ብቻቸውን የቆሙ እና ደህንነት ያለማግኘት ስሜት ያላቸውን ሰዎች እንዴት ሊደግፉ ይችላሉ?

የሚታደል የመልመጃ ወረቀት

ሁላችንም የብዙ ቡድኖች አባል ነን

ይህ መልመጃ የማንነታችንን በርካታ ገጽታዎች ያጎላል ፡፡ ስለራሳችን አስፈላጊ የሆነውን የመግለፅ አስፈላጊነትን እና እንዲሁም ፈታኝ የሆኑ የተዛቡ አመለካከቶችን መገዳደርን አስፈላጊነት ይዳስሳል፡፡

አቅጣጫ ክፍል አንድ

ስምዎን ከታች መሃል ላይ ያስቀምጡ። በእያንዳንዱ ውጫዊ ክበቦች ላይ የእርስዎን ማንነት የሚገልጽ ቡድን ይጻፉ፡፡ ይህ ማንኛውንም ቡድን ሊያካትት ይችላል ፥እስያዊ ፣ ሴት ፣ እህት ፣ አትሌት ፣ ተሳታፊ ፣ ሙስሊም ፣ ሙዚቀኛ ወይም እርስዎ የሚገኙበትን ማንኛውንም ቡድን፡፡ እንደ ጀብደኛ ወይም ፈጠራ ያሉ የግል ባህሪያትን ከመጠቀም ይቆጠቡ።



አቅጣጫ ክፍል ሁለት

የእርስዎ ተቀዳሚ ቡድን ነው ብለው በሚስማማዎት ቡድን ዙሪያ ክብ ይሳሉ እና ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽዎን ያጋሩ፥

- የተቀዳሚ ቡድንዎ አባል መሆን ጥሩ ስሜት ስለነበረዉ ጊዜ አንድ ታሪክ ያጋሩ።
- የተቀዳሚ ቡድንዎ አባል መሆን ፈታኝ ወይም አስቸጋሪ ስለነበረበት ጊዜ አንድ ታሪክ ያጋሩ።

የጥላቻ ፒራሚድ

ስለስርአተ ጾታ መልዕክቶች

አላማ

በማንነት ዙሪያ የሚደረግ ውይይት ብዙውን ጊዜ ፅንሰ-ሀሳባዊ ነው፡፡ ለተሳታፊዎች በራሳቸው ጾታ ተምክሮዎቻቸዉ ላይ እንዲያንፀባርቁ እድል መስጠቱ ተጨባጭ እውነታዎችን በንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ መልመጃ ተሳታፊዎች ከጾታቸው አንፃር ስለራሳቸው እንዲያስቡ እና የእኩዮቻቸውን ታሪኮች እንዲያዳምጡ ይጠየቃሉ፡፡ ተሳታፊዎች ከጾታቸው አንፃር እንዴት እንዳደጉ በማሰላሰል ስለ ሌሎች ያላቸውን አመለካከት የሚቀርጹ ስውር መልእክቶችን እንዲያስቡ ይጠየቃሉ፡፡

አላማዎች

- በሥርዓተ-ጾታ ዙሪያ ያሉ ተሳታፊዎች ለሌሎች ያላቸዉን ግምቶች እና ለዓለም ያላቸዉን አመለካከት ሚቀርፁ ተሞክሮዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት፡፡
- በሥርዓተ-ጾታ ዙሪያ የተሞክሮ እና የአመለካከት ልዩነቶችን ለመመርመር፡፡

ግዜ፣ 45 ደቂቃ
ማቴርያሎች፣ በመልመጃ ወቅት አመቻቾች ሚነበቡ የጥያቄዎች ዝርዝር

አካሄድ

አማራጭ 1 (መተማመን ለፈጠሩ ቡድኖች)

1. የመልመጃዉን አላማ ያብራሩ፡፡
2. ተማሪዎችን የጋራ ማዕከል ወዳላቸዉ ክቦች (concentric circles) ይከፋፍሏቸው። 1:2 ፣ 1:2 እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ እርስ በእርሳቸው በሚተያዩበት ክብ ውስጥ የመጀመርያዎቹ (1) ትከሻ ለትከሻ ገጣጥመዉ ይቁሙ፡፡ ተማሪዎች እንዲዞሩ ይጠይቋቸው እና የተቀሩትን ተማሪዎች ጋር ፊት ለፊት እንዲተያዩ ያድርጉ፡፡ እያንዳንዳቸው 2 ቁጥር ያሉት እንዲነሱ እና ከ 1 ቁጥር ፊት ለፊት እንዲቆሙ እና እንዲተያዩ ያድርጉ፡ ፡ ሁሉም አጋር እንዳለዉ ለማረጋገጥ 1 ቁጥሮች አጋራቸዉን እጅ በማንሳት እንዲያረጋግጡ አድርጉ (መጨባበጥ በባህል ሚበረታታ ከሆነ መጨባበጥ ይችላሉ)፡፡ የተሳታፊዎች ብዛት ጎዶሎ ቁጥር ሚሆን ከሆነ የተቀረው ተማሪዎች መልመጃዉን እንዲከታተሉ እና ሲያልቅ ምን እንደተመለከቱ ያጋሩ፡፡
3. አረፍተ ነገሮችን እንደሚያነቡ ያስረዱ ከዛም የ1 ዎቹ (በውስጠኛው ክብ) ወይም የ 2 ዎቹ (ውጭ ክብ) ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ የሚናገር ሰው መልስ ለመስጠት አንድ ደቂቃ ይኖረዋል፡፡ የሚያዳምጠው ሰው ማውራት የለበትም፡፡ ተናጋሪው ሙሉውን ደቂቃ እንዲመልስ ለመፍቀድ ዝም ማለት አለባቸው፡፡ ነገር ግን እየተሳተፉ መሆናቸውን ለማሳየት የምልክት ቋንቋ መጠቀም ይችላሉ፡፡
4. ከአንድ ደቂቃ በኋላ ኢጋሮቹ ሚና እንዲቀያየሩ ያድርጉ፣ እየተናገረ የነበረዉ ሰዉ አሁን እንዲያዳምጥ፣ እያዳመጠ የነበረዉ ለአረፍተ ነገሮቹ ምላሽ እነዲሰጥ፡፡
5. ከአንድ ደቂቃ በሆላ የውጪው ክብ አንድን ሰው ወደ ቀኝ እንዲሽከረክር ያድርጉ፣ እያንዳንዱ ሰው አዲስ አጋር እንዲኖረዉ። ከላይ የተገለፁትን ደረጃ 3 እና 4 በመከትል ቀጣዩን አረፍተ ነገር ያንብቡ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ለቀዳሚው አረፍተ ነገር ሁለተኛ ላይ ምላሽ የሰጠው ሰው አሁን መጀመሪያ መልስ መስጠት አለበት፡፡ ሁለቱም አጋሮች ምላሽ ከሰጡ በኋላ የውስጠኛው ክበብ አንድን ሰው ወደ ቀኝ እንዲያንቀሳቅስ ያድርጉ፡፡
6. ከእያንዳንዱ አረፍተ ነገር በኋላ በመጀመሪያ ማን እንደሚናገር በመለዋወጥ እና ክቦቹ አንድን ሰው ወደ ቀኝ የሚሽከረከሩበትን ቅደም ተከተል በመለዋወጥ አረፍተ ነገሮቹን ይቀጥሉ።
7. አረፍተ ነገሮቹን ካነበቡ በኋላ ከአማራጭ 2 በታች የተዘረዘሩትን የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም የውይይት ጥያቄዎችን በመጠቀም ውይይቱን ይምሩ፡፡

አማራጭ 2 (በደንብ ለማይተዋወቁ ቡድኖች)

የአረፍተ ነገሮቹን ዝርዝር ለእያንዳንዱ ተሳታፊ ይስጡ እና ምላሾቻቸዉ ላይ አስተያየት እዲሰጡ ይጠይቋቸዉ፣ ከፈለጉ በወረቀት ላይ ማስታወሻ ይያዙ፡፡ ከ 5 – 10 ደቂቃ ይስጧቸዉ፡፡

አማራጭ 1 ላይ ባሉት ደረጃዎች ይቀጥሉ፡፡ ተማሪዎችን የጋራ ማዕከል ወዳላቸዉ ክቦች ይከፋፍሏቸው እና በዝርዝሩ ላይ ከሚገኙት አረፍተ ነገሮች

ውስጥ 5ቱን በጥንድ እንዲጋሩ ይምረጡ፡፡

5ቱን አረፍተ ነገሮች ካነበቡ በሆላ ከሚከተሉት ጥያቄዎችን ውስጥ ሁሉንም ወይም የተወሰኑ በመጠቀም ዉይይት ይምሩ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

- ☐ ከተለያዩ አጋሮች ጋር ስለራስዎ የግል መረጃን ማጋራት ምን ስሜት አለዉ?
- ☐ የትኞቹን ጥያቄዎች ለመመለስ በጣም ከባድ ነበሩ? ለምን?
- ☐ በዚህ መልመጃ ውስጥ ስለራስዎ ምን ተማሩ? ስለ ሌሎች ስለ ተመሳሳይ ጾታ እኩዮችህ/ሽ እና ስለ ተቃራኒ ጾታ እኩዮችህ/ሽ ምን ተማሩ?
- ☐ ሰለማንነት የምናገኛቸዉ መልዕክቶች ከየት ነዉ ሚመጡት?
- ☐ እነዚህ መልዕክቶች ለሌሎች ያለንን አመለካከት እና ከሌሎች ምንጠብቀዉን ነገር እነዴት ይቀርፃሉ?
- ☐ ለሌሎች ማንነቶች ያሉን ግንዛቤዎች እንዴት ወደ ግጭት ይመሩናል?

መልዕክት ስለ ሥርዓተ-ጾታ - አማራጭ 1

- ☐ ልጅ እያሉ ስለ የወንድ እና የሴት የሥርዓተ-ጾታ ሚናዎች የተቀበሉአቸዉን መልዕክቶች ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ ከተቃራኒ ጾታ ሰዎች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ እንዴት እንደተማሩ ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ ከእርስዎ ጾታ ሰዎች እንደ አርአያ እንዲያዩዋቸው ትበረታቱ ስለነበሩ ሰዎች ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ ከተቃራኒ ጾታ ሰዎች እንደ አርአያ እንዲያዩዋቸው ትበረታቱ ስለነበሩ ሰዎች ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ በጾታዎ ምክንያት ለማድረግ የተከለከሉትን አንድ ነገር ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ የሚረብሾ ስለ ጾታዎ ሚባል የተሳሳተ አመለካከት ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ ስለ ሌላ ጾታ ያለዎትን የተሳሳተ አመለካከት ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ በህብረተሰቡ የተሰጦትን የጾታ ሚናዎች የማይመጥኑባቸውን መንገዶች ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ የጾታ ልዩነቶች እለት ተእለት እንዴት እንደሚነካዎት ለባልደረባዎ ያጋሩ፡፡
- ☐ በስራ ቦታዎ ስለ ጾታዎ የተገነዘቡበትን ጊዜ ያጋሩ፡፡

መልዕክት ስለ ሥርዓተ-ጾታ - አማራጭ 2

- ☐ በሚከተሉት ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ላይ አስተያየት ለመስጠት ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ፡፡
- ☐ ስለ ጾታዬ ሰዎች እንዳምን የተበረታታሁባቸዉ ነገሮች፡፡
- ☐ ስለ ጾታዬ ሰዎች እንዳላምን የተበረታታሁባቸዉ ነገሮች፡፡
- ☐ ከእኔ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሰዎች እንደ ፍቅር እና ቁጣ ያሉ ጠንካራ ስሜቶችን ስለሚያስተናግዱባቸዉ መንገዶች የተማርኳቸው ነገሮች፡፡
- ☐ ትምህርት ቤትን/ ሥራን / ሙያን በተመለከተ የጾታዬ ሰዎች እንዴት መሆን እንዳለባቸዉ የተማርኩባቸዉ መንገዶች፡፡
- ☐ የእኔ ፆታ "ጥሩ" ሰዉ ባህርያት/ገጽታ ተብለዉ ስለሚቆጠሩ የተነገሩኝ እሴቶች።
- ☐ ከሌላ ጾታ ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት እንዲኖረኝ የተማርኩባቸው መንገዶች፡፡
- ☐ ስለ ተቃራኒ ጾታ ሰዎች የተማርኩአቸው ነገሮች፡፡
- ☐ ትምህርት ቤትን/ሥራን/ሙያን በተመለከተ የሌላ ጾታ ሰዎች እንዴት መሆን እንዳለባቸዉ የተማርኩባቸዉ መንገዶች፡፡
- ☐ የእኔ ጾታ እና ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች፤ እንደ አርአያ እንዳያቸዉ የተበረታታሁት፡፡
- ☐ ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል የትኛው በእናንተ ላይ በጣም ዘላቂ ተጽዕኖ ነበረው?
- ☐ ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል የትኛው በእናንተ ላይ አሉታዊ ውጤት ነበረው?

የሕይወት ወንዝ

አላማ

የሕይወት ወንዝ ዓላማ ተሳታፊዎች በሕይወታቸው ጉዞ ውስጥ ያሉትን አፍታዎች እንዲገነዘቡ ዕድል ለመስጠት ነው፡፡ እንዲሁም እነሱ ላይ እነዲያፀባርቁባቸው እና አቅጣጫ እንዲይዙ የሚያስችል ሂደት ለመፍጠርነው፡፡

ዓላማዎች

- በእራስ የሕይወት ጉዞ ላይ ለማንፀባረቅ፡፡
- የግል ልምዶችን በይፋ ለማካፈል እና የአመራር ምስላችን ለመፍጠር እንዴት መናገር እንደምንችል ለማሰብ የረዳናል።

ግዜ፡ 1 ሰአት

- 25 ደቂቃ በሕይወት ወንዝ ላይ በተናጥል ለመስራት፡፡
- 20 ደቂቃ ተሳታፊዎች ለአጋራቸዉ እንዲያካፍሉ (ለእያንዳንዳቸዉ 10 ደቂቃ)፡፡
- 15 ደቂቃ ዉይይት ለመዝጋት፡፡

ማቴርያሎች፡ ፍሊፕ ቻርት ወረቀት እና ማርከር

ዝግጅት

- ☐ የራስዎን የሕይወት ወንዝ ይፍጠሩ እና ለማቅረብ ዝግጁ ይሁኑ፡፡
- ☐ ፍሊፕ ቻርቶችን ያዘጋጁ፡፡

1. የሕይወት ወንዝዎን ፍሊፕ ቻርት ላይ ይሳሉ

ከዚህ በታች ባለው ወንዝ ላይ የሚካተቱ ነገሮች፥

- ☐ ወንዙ ከመጀመሪያው እስከ ዛሬ ድረስ ያሳለፉትን ሕይወት ይወክላል፡፡ ወንዙ ውስጥ በሕይወታቸው ውስጥ አስፈላጊ ቦታዎችን የሚወክሉ "ደሴቶችን" ይሳሉ (ለምሳሌ የተወለዱበትን ቦታ)፡፡
- ☐ በሕይወታቸው አስፈላጊ የነበሩ እና አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን የሚወክሉ "ሕይወት አድን" መሳል ይችላሉ።
- ☐ ከወንዙ በስተቀኝ በኩል ደስታን ፣ ስኬትን፣ ድምቀቶችን ወይም ሁነቶችን የሚወክሉ "ገባር ወንዞችን" ይሳሉ።
- ☐ በወንዙ ግራ በኩል በሕይወታቸው ውስጥ ያለፉ ፈታኝ ፣ ከባድ ፣ አስቸጋሪ ወይም አሳዛኝ ጊዜዎችን የሚወክሉ "ገባር ወንዞችን" ይሳሉ።

2. የሕይወት ወንዝዎን ያካፍሉ

ተሳታፊ"ሀ" አንድ ወይም ሁለት መልካም እና አንድ ወይም ሁለት ፈታኝ ልምዶችን ያካፍሉ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ተሞክሮ የተማረውን/ችዉን ያጋራሉ፡፡ ወንዝዎን ወደኋላ መለስ ብለው ሲመለከቱ፥

- ☐ ምን አይነት ተደጋጋሚ ባህሪዎችን ታያለህ/ሽ?
- ☐ የህይወት ትምህርቶች?
- ☐ በጣም የምትኮራበት/ምትኮሪበት ነገር ምንድን ነው?

ተሳታፊ "ለ" ይመልሳል

- ☐ እኔን ያንቀሳቀሰኝ ፣ የነካኝ ፣ የገረመኝ ወይም ያስገረመኝ ነገር...
- ☐ እንደ ጥንካሬ እና እሴት የሰማሁት ነገር...
- ☐ ከእርስዎ አመራር ወይም የግንኙነት ዘይቤ ጋር ሊዛመድ የሚችል የሰማሁት ነገር...

አካሄድ

የሕይወት ወንዝ እና ሞዴልን ይግለፁ

- ☐ ከክፍለ ግዜዉ በፊት የእርሶን የህይወት ወንዝ ይሳሉ፡፡

☐ የህይወት ወንዝን ለማብራራት የራስዎን ወንዝ ይጠቀሙ:: የኖሩባቸዉን ቦታዎች፣ በህይወቶ አስፈላጊ ሚሉአቸዉን ሰዎች፣ የተጋፈጡአቸዉን አስቸጋሪ ግዜያት እና የተቀበሏቸውን የዕድል አጋጣሚዎች አሳዩ::

ለተሳታፊዎች ማቴርል እና መመርያዎችን ይስጡ

☐ ባዶ ወረቀት ያሰራጩ (ማንኛውም መጠን ፖስተር / ፍሊፐ ቻርት በጥሩ ሁኔታ ይሠራል ፣ ግን መደበኛ ወረቀትም መጠቀም ይችላሉ)::

☐ ተሳታፊዎች ማርከሮችን ፣ እርሳሶችን ወይም እስክሪፕቶ በመጠቀም ከወረቀቱ ከላይኛው ጥግ ወደ ተቃራኒው የወረቀቱ ጥግ የሚፈስ ጥቂት ኢንች ስፋት ያለው ቀለል ያለ ወንዝ ይሳሉ::

ፍሊፐ ቻርት በመጠቀም ወረቀታቸዉ ላይ ምን እንደሚጨምሩ ግለፁላቸዉ

☐ ወንዝ

☐ "ደሴቶቹ"

☐ "ሕይወት አድን"

☐ ሊያጋሩአቸዉ ማይችሉአቸዉን ነገሮች ሚወክሉ ምልክቶች

☐ "ገባሮች" ታላላቅ የደስታ ሁነቶችን ፣ ስኬቶችን ወይም በዓላትን (በስተቀኝ) እና በሕይወታቸው ውስጥ ፈታኝ ፣ ከባድ ፣ አስቸጋሪ ወይም አሳዛኝ ጊዜያትን (በስተግራ) የሚወክሉ ገባሮች::

ተሳታፊዎች ራሳቸዉን የህይወት ወንዝ እንዲስሉ 25 ደቂቃ ደቂቃ ስጡአቸዉ

☐ ግዴታ ወንዝ መሆን የለበትም:: ሌላ ዓይነት ተንቀሳቃሽ የውሃ አካል ወይም ሌላ መዋቅር ሊሆን ይችላል::

☐ ይህ መልመጃ የጥበብ ችሎታ ሚጠይቅ አይደለም:: ተሳታፊዎች የሕይወታቸውን ታሪክ በሚታይ መልኩ በወረቀት ላይ እንዲያስቀምጡ ብቻ ይፈልጋል::

☐ ተሳታፊዎች ባለፉት ጊዜያት ተጽዕኖ ያሳደሩባቸውን ሁነቶች እና ሰዎች ምልክት ማድረግ አለባቸው።

የህይወት ወንዛቸዉን ለአጋራቸዉ እንደሚያካፍሉ ያብራሩ

☐ ግዴታ ወንዝ መሆን የለበትም:: ሌላ ዓይነት ተንቀሳቃሽ የውሃ አካል ወይም ሌላ መዋቅር ሊሆን ይችላል::

☐ ይህ መልመጃ የጥበብ ችሎታ ሚጠይቅ አይደለም:: ተሳታፊዎች የሕይወታቸውን ታሪክ በሚታይ መልኩ በወረቀት ላይ እንዲያስቀምጡ ብቻ ይፈልጋል::

ተሳታፊዎች ሁለት ሁለት ሆነው እንዲከፋፈሉ ይጠይቋቸው

☐ ተሳታፊ "ሀ" ለተሳታፊ "ለ" የወንዙን አጭር ጉብኝት ይሰጣል::

☐ አንድ ወይም ሁለት መልካም እና አንድ ወይም ሁለት ፈታኝ ልምዶችን እና ከእያንዳንዱ ተሞክሮ የተማረውን/ችዉን ፍሊፐ ቻርቱን ተጠቅመዉ እንደሚጋሩ ያብራሩ::

ሚናዎችን ይቀይሩ እና መልመጃውን እንደገና ያካሂዱ።

ዉይይት

1. ስለራስዎ ምን ተማሩ?
2. ስለአጋርዎ ምን ተማሩ?
3. ለእርስዎ የትኞቹ ጊዜያት ጎልተው ይታያሉ?
4. የወንዞ አጠቃላይ ታሪክ ምንድነዉ?

7

የሚታደሉ
የመልመጃ ወረቀቶች
እና መልመጃዎች

ጥበብ ለሰላም
#አርትቪስም
#Artivism

#defyhatenow | 7 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ጥበብ ለሰላም #አርትቪስም #Artivism

ጥያቄዎች ለቡድን ዉይይት

- የተለያዩ ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ለሰላም ግንባታ ምን ያህል አስተዋፆ እንደሚያበረክቱ በጥልቀት ይመልከቱ?
- በእነዚህ ተግባራት መካከል እንደ አንድ የጋራ ዓላማ ወይም አካላት ምን ይመለከታሉ?
- ስለ ሰላም ካሎት ግንዛቤ ጋር እንዴት ሊያገናኙት ይችላሉ?
- የሰላም ግንባታን ዓላማ እውን በማድረግ ስኬታማ የሚሆኑ ይመስልዎታል?
- በእርስዎ ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን ከሰላም ግንባታ ጋር ለማገናኘት የሃሳቦችዎን ንድፍ ይሳሉ፡፡

ለሰላም ግንባታ የራስዎን ተነሳሽነት እየጀመሩ ነዉ፤ እራስዎን ይጠይቁ

- ይህ ተነሳሽነት ወዴት እያመራ ነው?
- ኃይለኛ ግጭትን ይከላከላል?
- ለሰላም አስተዋጽኦ ያደርጋል?
- ድህረ-ግጭት ላይ የሆነ ማህበረሰብን ለማዳበር እንዴት ይረዳል?

የቡድን መልመጃዎች፡ ሰላም ግንባታ አላማዎች

☐ ለሰላም ግንባታ እንቅስቃሴዎች፣ ዓላማዎች ወይም ግቦች የሚያሳዩ የስዕላዊ መግለጫ ክቦች (ዲያግራም) ይንደፉ።

☐ ቀስቶች ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴ / ክቦች ወደ የተለየ ፅንሰ-ሀሳብ ይጠቁሙ።

ምሳሌ፡

☐ በተለያዩ ሰዎች መካከል የግንኙነት ክፍተቶችን ማገናኘት ፡፡

☐ ሰላምን ግላዊ ማድረግ ፣ ከሰዎች ጋር መገናኘት እና ተሳትፎ ማድረግ።

☐ የሰላም ዘላቂነት እና የራስ ትምህርት።

☐ ብዝሃነት ፣ አብሮ መኖር እና ወደ ጥቃት ሳይወስዱ ግጭቶችን መፍታት አስፈላጊነት፡፡

☐ በሕዝብ ዘርፍ ውስጥ ግልጽነት እና ሁሉን አካታችነት፡፡

☐ ስዕላዊ መግለጫው በተጨማሪ እነዚህ ነጥቦች እንዴት ፈሳሽ እንደሆኑ እና እርስ በእርስ ሊጣመሩ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

☐ በስዕሉ ላይ ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ነጥቦቻቸውን ለመጨመር እና ለማገናኘት ለተሳታፊዎች ቦታ ይተው፡፡

☐ አመቻቾች ተሳታፊዎች ከላይ ባለው ንድፍ ላይ በፃፉአቸዉ ነጥቦች በማስፋት የራሳቸውን እንቅስቃሴ እንዲያወጡ እና ከሰላም ግንዛቤ ጋር እንዲያያይዙት መድረኩን እንዲከፍቱ ይበረታታሉ፡፡

ለእርምጃ ቁልፍ መወያያ ነጥቦች

☐ በማህበረሰብዎ ውስጥ ምን ዓይነት የሰላም ግንባታ ባህላዊ ልውውጥን መለየት ይችላሉ?

☐ ዝግጅት የት ያዘጋጃሉ? ምሳሌ፡ ትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ ቦታዎች፡፡

☐ የባህል ልውውጥን ፣ የሰላም ግንባታ እንቅስቃሴዎችን ለማመቻቸት በቡድኑ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሀሳቦች ዝርዝር ይያዙ፡፡

- ☐ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን አሁን ለመተግበር ከቡድኑ ጋር ይወስኑ፡፡
- ☐ ያቀዱት እንቅስቃሴ ሁሉንም ያካተተ እና ለተለያዩ ማህበረሰቦች እና የዕድሜ ክልሎች ክፍት መሆኑን ያረጋግጡ፡፡
- ☐ ቦታ ይፈልጉ፣ ቀኑን ያዘጋጁ. የማህበረሰብ መሪዎችን እና አስተማሪዎችን ያሳትፉ፡፡
- ☐ ዝግጅቱን እንዲሳተፉ ሽማግሌዎች እና ወጣቶች ፣ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ክፍሎች እንዲያውቁ ያድርጉ ይጋብዙዋቸዉ፡፡
- ☐ የፌስቡክ የሁነት ገጽ ይክፈቱ ፣ በራሪ ወረቀቶችን ያሳትሙ ፣ የማህበረሰብ ማስታወቂያዎችን ፣ የሬዲዮ ቃለመጠይቆችን ያዘጋጁ ፡፡

ማስታወሻ:

8

የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ከሰቀቀን መልሶ ማገገም

#defyhatenow | 8 የሚታደሉ የመልመጃ ወረቀቶች እና መልመጃዎች

ከሰቀቀን መልሶ ማገገም

ከሰቀቀን ማገገም ስልጠና ተነሳሽነት

ስለ ሰቀቀን እዉቀት እና መሪዎች ለሰቀቀን መልሶ ማገገም እንዴት የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ

ፕላትፎርም አፍሪካ (PLATFORM AFRICA)

መግብያ

የዚህ ስልጠና አላማ ህብረተሰቡን በተለይም መሪዎችን መሰረታዊ የማማከር እና የመጀመርያ ደረጃ እርዳታ እዉቀት ለማስተማር ሲሆን፤ ለማንኛውም ከአሰቃቂ ክስተቶች ለተረፉ ሰዎች እንዴት ተስፋን ማፍለቅ እንደሚቻል፣ ዘላቂ መፍትሄ ለማበረታታት እና አሰቃቂ ሰቀቀን ከሚያስከትሉ ክስተቶችን የመከላከያ ዘዴዎችን ለማስጨበጥ ነው። ይህም መሪዎች ምልክቶችን እንዲገነዘቡ፤ መቋቋምያ መንገዶችን፣ አዳዲስ ሰቀቀን ማገገሚያ መንገዶችን በጋራ ለመፈለግ ወይም ለመፍጠር እንዲሁም ሰቀቀንን እየታገሉ ያሉ ሰዎችን እንዴት መለየት እና ለመርዳት እንደሚችሉ ነው።

ብዙ ጊዜ ድርጅቶች እና ኮርፖሬሽኖች ለአእምሮ/ለስሜቶች/ለሀሳቦች ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት አይመለከቱም፤ በተለይ አሳዛኝ ክስተት ሲኖር። ለውይይቶች ቦታዎችን በማመቻቸት እና ሰዎች ህመማቸውን እንዲያካፍሉ በመፍቀድ፣ ብዙ ሰዎች በበለጠ ሁኔታ እንዲያገግሙ እና ነገሮችን በመረዳት ይቅር ባይ እንዲሆኑ ይረዳዎታል። እንዲሁም የሚያድግ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡

አለማዎች

ይህን ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ክህሎቶች ያዳብራሉ፥

- ሰቀቀንን ከባህላዊ እና ሙያዊ እይታ አንፃር ይረዳሉ፣ ይገልፃሉ፡፡
- ሰቀቀን ሚያስከትሉ ሁነቶች (ሞት፣ ጥቃት፣ ግጭት) ዉስጥ ያለ ማንኛውንም ሰው የሚረዳ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ለማድረግ ተግባራዊ ክህሎቶች ይኖራቸዋል፡፡
- ማህበረሰባቸዉ ዉስጥ ስለ ሰቀቀን ፣ አሰቃቂ ሰቀቀን ስለሚፈጥሩ ሁነቶች እና ተፅእኖዎች ላይ ዉይይት እንዲኖር ደህንነታቸው የተጠበቀ ቦታዎችን/ሁኔታዎችን መፍጠር መቻል፡፡ በዚህ አዲስ አዎንታዊ የመቋቋም ስነ ዘዴዎችን መማር ይችላሉ፡፡
- እንደ መሪ እራሳቸዉን ከመጠን ያለፈ ድካም መጠበቅ ይማራሉ፡፡
- የቡድን የቴራፒ ክፍለ ግዜዎችን ማዘጋጀት ይማራሉ፡፡

ሚያስፈልጉ ነገሮች

- ☐ ሰሌዳ ወይም ወረቀት ፣ ማርከር እና ተለጣፊ ማስታወሻዎችን፡፡
- ☐ ቻርጅ የተደረገ ካሜራ፣ ከመጠባበቅያ ባትሪ ጋር፡፡
- ☐ ተሳታፊዎች ከ2:30 – 11:00 ለሚደርገዉ የ 1 ቀን ስልጠና ይገኙ፡፡
- ☐ በሁሉም ክፍለ ግዜዎች ይሳተፉ፤ በተለይ የተግባር ልልምዶች እና የቡድን ዉይይት፡፡
- ☐ መሰረታዊ የተግብቦት ክህሎት እና ስሜታዊ ብልህነት ይኑርዎት።

ምንጭ፡ መሪ አሰልጣኝ ፕላትፎርም አፍሪካ ሳይኮሎጂስት **(Platform Africa)**፥ ሻርሎት ኣይነብዮኦና ኪገዝኦ፣ አሩዋ ፣ ኡጋንዳ

ፕሮግራም (አንድ ቀን)	(ምሳሌ ብቻ)
ሰዓት	ርዕስ
08:30 - 09:00	የሰቀቀን መግቢያ እና ሰቀቀንን መገንዘብ
9:00 - 10:00	መንስኤዎች እና አጋላጭ ምክንያቶች
10:00 - 11:00	ምልክቶች እና የመቋቋም ዘዴ ዎች(አዎንታዊ እና አሉታዊ)
11:00 - 11:30	የሻይ እረፍት
11:30 - 13:00	ቀጥተኛ ያልሆነ ሰቀቀን
13:00 - 14:00	የምሳ እረፍት
14:00 - 14:30	እንደ መሪ ያለን ሚና
14:30 - 15:30	የመከላከያ መንገዶች
15:30 - 15:45	እረፍት
15:45 - 17:00	የማህበራዊ ድጋፍ ስርአት አስፈላጊነት
17:00 - 17:30	አስተያየቶች እና ወደ ፊት እንዴት እንቀጥል

አዉቅና

#defyhatenow ተነሳሽነትን በሀሳብ፣ በግዜ፣ በአዎንታዊ ድጋፍ፣ በፈጠራ ትብብር ላይ የሰላም ግንባታ እርምጃ በደቡብ ሱዳን፣ ካሜሮን፣ ኢትዮጵያ ፣ ዩጋንዳ እና ኬንያ በማገናኘት ፣ አስተዋፆ ላደረጋችሁ በሙሉ እናመሰግናለን፡፡

#defyhatenow ይህን የመስክ መመርያ የትም ሆነዉ ሰላማዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ለሚሰሩ ደቡብ ሱዳናዊያን እና ኢትዮጵያዉያን መታሰቢያነት ይሰጣል፡፡

ኢትዮጵያ ተነሳሽነት 2019-2020

ምስጋና፥ #defyhatenow ሀሳቡ በ 2014 መጀመሪያ እ.ኤ.አ. በ 2013 መገባደጃ ላይ ለተነሳው የደቡብ ሱዳን ግጭት ምላሽ ለመስጠት ከተነሳ ጀምሮ ተነሳሽነቱን ለመገንባት የረዱ ተሳታፊዎች፣ ወርክሾፕ አመቻቾች እና ዘጋቢዎች እናመሰግናለን፡፡

በአመቱ ሁሉም ቀናት ሰላምን ማስተጋባት ይቀጥሉ !

በሕይወትዎ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለሰላም በንቃት ይሳተፉ፡፡ በውስጣችሁ ሰላምን መገንባትን ቀጥሉ፡፡ ሰላምን በልቦ ዉስጥ ያግኙ ፣ ሰቀቀንን ለማሸነፍ የባለሙያ እርዳታ ይጠይቁ፡፡ ያስታዉሱ በየቀኑ ሰላምን የመምረጥ እድል አለዎት፡፡ በራስዎ ልምዶች እና ግንኙነቶች መግባባትን ፣ ርህራሄን እና እርቅን ያራምዱ፡፡የፖለቲካ አጀንዳ ያለው ማንኛውም ሰው ጥረትዎን እንዲያደናቅፍ ወይም ከሰላማዊ ዓላማዎች እንዲለያይዎት አይፍቀዱ ፡፡

ዓለምን ሰላም የሰፈነባት እንድትሆን ስለ ቀና ጉልበት እና አስተዋፆ እናመሰግናለን፡፡
#ፍቅርያሰራጩ (#SpreadLove) #ከጥላቻየፀዳችኢትዮጵያ (#HateFreeEthiopia) #defyhatenow
#ለሰላምእርምጃይዉሰዱ (#Act4Peace)

#defyhatenow
@defyhatenow
https://defyhatenow.org/
facebook.com/defyhatenow
twitter.com/defyhatenow

የሆላ ገፅ ፎቶ፡ መሳርያ ሳይሆን ብዕር ያስፈልጋል! ቦር፣ደቡብ ሱዳን

የ2020 ኢትዮጵያ እትም የ #defyhatenow የማህበራዊ ሚድያ የጥላቻንግግር ቅነሳ መስክ መመሪያ በr0g_agency በ Deutsche Gesellschaft für International Zusammenarbeit (GIZ) GmbH ድጋፍ “የምእራብ ኢትዮጵያ-ምስራቅ ሱዳን አገር አቋራጭ ትብብር” ፕሮጀክት መዋቅር ስር በአዉሮፓ ህብርት በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ፡፡

agency for open culture & critical transformation
Co-funded by the European Union
german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

r0g_agency
ISBN 978-3-9819895-5-7
9 783981 989557